# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ሰኞ 82ኛ ዓመት ቁጥር 177 የካቲት 27 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!



የለገዳዲ የውሃ ማጣሪያ ጣቢያ

# አዲስ አበባ

## በቀን 1 ነጥብ 1 ሚሊዮን ሜትር ኪዩብ ውሃ ቢያስፈልጋትም እያመረተች ያለችው 725 ሺህ ብቻ ነው

**አዲሱ ገረመው**

አዲስ አበባ፡- በአዲስ አበባ ከተማ በቀን ከሚያስፈልገው አንድ ነጥብ አንድ ሚሊዮን ሜትር ኪዩብ ውሃ አሁን ላይ እየተመረተ ያለው 725ሺህ ሜትር ኪዩብ ብቻ መሆኑን የአዲስ አበባ ከተማ ውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን አስታወቀ፡፡ በ570 ሚሊዮን ብር በጀት ተጨማሪ 75ሺህ ሜትር ኪዩብ ውሃ እየለማ እንዳለ ተገልጿል፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ ውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን የኮሙኒኬሽን ዳይሬክተር ወይዘሮ ሥርካለም ጌታቸው ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳስታወቁት፤ በአሁኑ ወቅት ከተማዋ በቀን አንድ ነጥብ አንድ ሚሊዮን ሜትር ኪዩብ ውሃ የምትፈልግ ቢሆንም በቀን የማምረት አቅም

አዲስ አበባ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## ክልሉ ለ215 ባለሀብቶች የኢንቨስትመንት ፍቃድ ሰጠ

**መዓዛ ማሞ**

አዲስ አበባ፡- ባለፉት ስድስት ወራት ለ215 ባለሀብቶች የኢንቨስትመንት ፍቃድ መስጠቱን የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል አስታወቀ፡፡

የክልሉ ኢንቨስትመንትና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ ኃላፊ አቶ ሐልጌዮ ጂሎ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፣ በክልሉ ባለፉት ስድስት ወራት የኢንቨስትመንት ፈቃድ ለጠየቁ 215 ባለሀብቶች የኢንቨስትመንት ፈቃድ ተሰጥቷል፡፡ ከነዚህ ውስጥ በግብርና 88፣ በአገልግሎት 67 እንዲሁም በኢንዱስትሪ ዘርፍ 60 መሆናቸው ታውቋል፡፡ እነዚህ ባለሀብቶችም በአጠቃላይ ከ9ነጥብ3 ቢሊዮን ብር ካፒታል ያስመዘገቡ

ክልሉ ለ215 ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## ስንዴን ወደ ውጭ ገበያ መላክ ጠንካራ ኢኮኖሚን ለመገንባት ዕድል ይሰጣል

**ፍሬሕይወት አወቀ**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ በበጋ መስኖ በስፋት ያለማችውን ስንዴን ኤክስፖርት ማድረግ መጀመሯ ጠንካራ ኢኮኖሚን መገንባት የሚያስችላት ትልቅ ጅማሮ እንደሆነ የምጣኔ ሀብት ምሁር ገለጹ፡፡

በሐረማያ ዩኒቨርሲቲ የኢኮኖሚክስ መምህርና በ‹‹ፍሮንቲየርአይ (Frontieri)›› ጥናትና አማካሪ ድርጅት ከፍተኛ ተመራማሪ ዶክተር ሞላ አለማየሁ ለኢፕድ እንደተናገሩት፤ አሁን ላይ በአገር ውስጥ ያለው የዋጋ ግሽበት እንዳለ ሆኖ ስንዴን ወደ ውጭ ገበያ መላክ የአገሪቷን ኢኮኖሚ በጠንካራ መሠረት ላይ ማኖር የሚያስችልና ዘለቄታዊ መፍትሔን የሚሰጥ እንደሆነ አስረድተዋል፡፡

ለአንድ አገር ኢኮኖሚያዊ ዕድገት መረጋገጥ የወጪ ገቢ ንግዱን ማመጣጠን የግድ መሆኑን ያነሱት ዶክተር ሞላ፤ አገራት ለውጭ ንግድ ከፍተኛ ትኩረት ሰጥተው

ስንዴን ወደ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


ዶክተር ሞላ አለማየሁ





















## በአዲስ አበባ 17 ሺህ አሽከርካሪዎች ላይ የአልኮል መጠን ምርመራ ተደርጓል

- 294 አሽከርካሪዎች ከተፈቀደው በላይ የአልኮል መጠን በትንፋሻቸው ተገኝቷል

**ታደሰ ብናልፈው**

አዲስ አበባ፡- በአዲስ አበባ ከተማ በጠጥቶ ማሽከርከር የሚደርሰውን የትራፊክ አደጋ ለመግታት ባለፉት ሁለት ወራት ከ17 ሺህ በላይ በሚሆኑ አሽከርካሪዎች ላይ የአልኮል ምርምራ ተደርጎ በ294 አሽከርካሪዎች ላይ ከተፈቀደው በላይ የአልኮል መጠን ተገኝቷል ሲል የትራፊክ አስተዳደር ኤጀንሲ ገለጸ፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ የትራፊክ አስተዳደር ኤጀንሲ የኮሚኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክተር አቶ ብርሀኑ ኩማ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በመዲናዋ ጠጥቶ በማሽከርከር በሰው ልጅ ሕይወትና በንብረት ላይ የሚደርሰውን የትራፊክ አደጋ ለመቀነስና ለመከላከል በተጠኑ የመዲናዋ አካባቢዎች በአሽከርካሪዎች ላይ የአልኮል የትንፋሽ ምርመራ እየተደረገ ነው፡፡

ባለፉት ሁለት ወራት ከ17 ሺህ በላይ አሽከርካሪዎች ላይ የትንፋሽ የአልኮል መጠን ምርመራ መደረጉን የጠቆሙት አቶ ብርሀኑ፤ ምርምራ ከተደረገባቸው ከ17 ሺህ በላይ አሽከርካሪዎች ውስጥ በ294 አሽከርካሪዎች ላይ ከተፈቀደው በላይ የአልኮል መጠን የተገኘ ሲሆን በ576 አሽከርካሪዎች ላይ መጠነኛ የአልኮል መጠን በትንፋሻቸው ተገኝቷል ብለዋል፡፡

ከመጠን በላይ የአልኮል መጠን በትንፋሻቸው በተገኘባቸው 294 አሽከርካሪዎች የገንዘብ ቅጣትና ሕጋዊ እርምጃ የተወሰደባቸው ሲሆን መጠነኛ የአልኮል ለተገኘባቸው በ576 አሽከርካሪዎች የግንዛቤ ማስጨበጫ በመስጠት በማስጠንቀቂያ መታለፋቸውን አቶ ብርሀኑ ተናግረዋል፡፡

ይደረግ የነበረው የአልኮል መጠን ምርመራ በኮቪድ 19 ምክንያት ለሁለት ዓመታት ተቋርጦ እንደነበር ያስታወሱት ዳይሬክተሩ፤ ካለፈው ታኅሣሥ ወር ጀምሮ ምርመራውና ቁጥጥሩ ተጠናክሮ መቀጠሉን አብራርተዋል፡፡

በመዲናዋ በብዛት የሚደርሰው የትራፊክ አደጋ ጠጥቶና በፍጥነት በማሽከርከር የሚከሰት መሆኑን ጠቅሰው፤ አደጋውንም ለመቀነስና ለመከላከል የአልኮል የትንፋሽ ምርምራና የፍጥነት ቁጥጥር እየተደረገ ነው ብለዋል፡፡

የአልኮል የትንፋሽ ምርምራ በአሽከርካሪዎች መደረጉ የትራፊክ አደጋውን በመቀነስ በኩል ጉልህ ሚና ተጫውቷል ሲሉም አብራርተዋል፡፡

በጠጥቶ ማሽከርከር እየተከሰተ ያለውን የትራፊክ አደጋ ለመቀነስና ለመከላከል በመዲናዋ በሚገኙ 11 ክፍለ ከተማዎች በተለያየ ሰዓትና ቀን ጥናት በማድረግ በትኩረት እየተሠራ ነው ብለዋል፡፡

ባለፉት ሁለት ወራት በአዲስ አበባ ከተማ እየደረሰ ያለው የትራፊክ አደጋ መቀነሱን ጠቅሰው፤ ከማኅበረሰቡ ጋር በቅንጅት በመሥራትና የግንዛቤ ማስጨበጫ በመስጠት አደጋውን ለመከላከልና ለመቀነስ እየተሠራ መሆኑንም አመላክተዋል፡፡

# ዞኑ 200 ሺህ ኩንታል ስንዴ ለውጭ ገበያ ለማቅረብ እየሠራ ነው

**ዳግማዊት አበበ**



አዲስ አበባ፡- በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የምሥራቅ ጎጃም ዞን 200 ሺህ ኩንታል ስንዴ ለውጭ ገበያ ለማቅረብ እየሠራ መሆኑን የዞኑ ግብርና መምሪያ አስታወቀ፡፡

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የምሥራቅ ጎጃም ዞን ግብርና መምሪያ ኃላፊ አቶ አበበ መኮንን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ዞኑ በ2015 በመስኖ ስንዴ ምርት በአንደኛው ዙር 20 ሺህ 508 ሄክታር መሬት በመስኖ ማልማት አቅዶ 22 ሺህ ሄክታር የሚጠጋ መሬት በዘር መሸፈኑን ገልጿል፡፡

እንደ አቶ አበበ ገለጻ፤ ከተዘራው መካከል በአርሶ አደሩ 19 ሺህ 770 ሄክታር፣ በወጣቶች አንድ ሺህ 876፣ በባለሀብቶች 252 ሄክታር እንዲሁም በተቋማት 62 ሄክታር በአጠቃላይ 22 ሺህ ሄክታር የሚጠጋ መሬት መዘራቱን ገልጸዋል፡፡

ዞኑ ከተዘራው መሬት 922 ሺህ 860 ኩንታል የስንዴ ምርት ለማግኘት እየተሠራ ነው ያሉት መምሪያ ኃላፊው ከዚህ ውስጥም 200 ሺህ ኩንታል ስንዴ ምርት ለውጭ ገበያ ለማቅረብ ታቅዷል ብለዋል፡፡ ይህም በርካታ አርሶ አደሮችን ተጠቃሚ የሚያደርግ እና በ2014 ከተገኘው አማካኝ ምርታማነት ከ36 ኩንታል ወደ 45 ኩንታል የሚያሳድግ ነው ብለዋል፡፡

እንደ ዞን ዓላማ ተደርጎ እየተሠራ ያለው የስንዴ ልማት፤ ኢትዮጵያ የምግብ ክፍተትን ለመሙላት ለስንዴ ግዥ የምታወጣውን የውጭ ምንዛሬ ማስቀረት ነው፡ በተጨማሪም የስንዴ ሰብልን በስፋትና በጥራት በማምረት ለውጭ ገበያ ኤክስፖርት ማድረግ እና ስንዴን በግብዓትነት ለሚጠቀሙ የአገር ውስጥ አግሮ ኢንዱስትሪዎችን ማሟላት እንዲሁም አርሶ አደሩን ተጠቃሚ ለማድረግ እንደሆነ አቶ አበበ ገልፀዋል፡፡

በአመራሩና በባለሞያው መካከል መደማመጥ መኖሩ፣ ክልሉ በቂ የሆነ ሀብት መመደብ መቻሉ፣ የግብርና መምሪያው ክትትል እና ድጋፍ ሥርዓት ጠንካራ መሆኑ፣ የአቅም ግንባታና የንቅናቄ መድረኮች እንዲሁም የውሃ ማቆር ሥራዎች ቀድመው መሠራታቸው ለዞኑ የመስኖ ስንዴ ልማት መሳካት ምቹ ሁኔታ የፈጠሩ መሆኑን ኃላፊው ጠቅሰዋል፡፡

እንደ አቶ አበበ ገለጻ፤ በሰብል ቀን መቁጠሪያ መሠረት አለመመራት፣ በአንዳንድ ወረዳዎች አመራሩ ከመምራት ባለፈ ለወረዳዎች ድጋፍ የማድረግ ውስንነት እና ባለሀብቶች ፈጥኖ ወደ ሥራ አለመግባት በስንዴ ልማት ሥራው የታዩ ችግሮች ናቸው፡፡

# ማህበሩ በ52 ፓርኮች ከ24 ሚሊዮን በላይ ችግኞችን እየተንከባከበ ነው

## - 6 ሚሊዮን ችግኞችን ለመትከል እየተዘጋጀ ነው

**ቃልኪዳን አሳዬ**

አዲስ አበባ፡- በ52 ፓርኮች ከ24 ሚሊዮን በላይ ችግኞችን መትከል መቻሉን የኦሮሚያ ልማት ማህበር አስታወቀ፡፡ ማህበሩ በመጪው ክረምት ስድስት ሚሊዮን ችግኞችን ለመትከል የዝግጅት ሥራ እያከናወነ መሆኑንም አስታውቋል፡፡

የኦሮሚያ ልማት ማህበር ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ ደጀኔ ኢቲቻ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለፁት፤ ማህበሩ ከ2003 ዓ.ም ጀምሮ በየዓመቱ ብዛት ያላቸውን ችግኞች በመተከልና በመንከባከብ የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ሥራ በበጎ ፍቃደኝነት እየሠራ ይገኛል።

ማህበሩ በኦሮሚያ ልዩ ዞን ሰበታ ወረዳ በደበል ተራራ ከ600 ሄክታር በላይ የተራቆተን መሬት በተፈጥሮ ልማት ሥራ መልሶ እንዲያገግም የሚያስችል ሥራ መሠራቱንም አቶ ደጀኔ ገልፀዋል።

በተጨማሪም በወረዳው በዲማና ሀሮጂ ቀበሌዎች፣ በአቃቂ በእንዝላሌ ተራራ እንዲሁም በተለያዩ አካባቢዎች ላይ የአካባቢ ጥበቃ ሥራዎችን ማከናወኑን ተናግረዋል።

የልማት ማህበሩ ከተቋቋመበት ዓላማ አንዱ የአካባቢ እንክብካቤ ሥራ እንደሆነ ገልፀው፤ የተተከሉ ችግኞች እንክብካቤ አግኝተው በአግባቡ እንዲያድጉ በቋሚነት ሠራተኞችን ቀጥሮ እያሠራ ነው ብለዋል።

ሰበታ በሚገኘው የደበል ተራራ ከስምንት በላይ ሠራተኞች ቤት ተዘጋጅቶላቸው በተራራው ላይ የተተከሉትን ችግኞች እንስሳትና ሰዎች እንዳያበላሹ ጥበቃና እንክብካቤ እያደረጉ መሆኑን



**አቶ ደጀኔ ኢቲቻ**

አስታውቀዋል።

ሥራው በተጀመረ በመጀመሪያ ወቅት ችግኞች ቢተከሉም ውጤት ሊገኝ እንዳልቻለ አስታውሰው፤ የአረንጓዴ አሻራ እንቅስቃሴ ከተጀመረ በኋላ የዜጎች አስተሳሰብ በመቀየሩ ማኅበረሰቡ የሚተከሉ ችግኞች ፀድቀው ለተፈለጉበት ዓላማ እንዲውሉ ከልማት ማህበሩ ጋር በጋራ እየሠራ ይገኛል ብለዋል።

አቶ ደጀኔ እንደገለጹት፤ ማህበሩ በተለያዩ ስፍራዎች በዋናነት የሚተክላቸው ችግኞች አገር በቀል ናቸው። ችግኞቹም ጸድቀው ለንብ ማነብ፣ ለአካባቢ ጥበቃና ለተለያዩ አገልግሎት እንዲውሉ በጥብቅ ቁጥጥር የታገዘ የእንክብካቤ ሥራ እያከናወነ ይገኛል።

ልማት ማህበሩ ሥራውን በማጠናከር በመጪው ክረምት ስድስት ሚሊዮን ችግኞችን ለመትከል በዝግጅት ላይ እንደሚገኝ የገለፁት አቶ ደጀኔ፤ በአዲስ አበባ ከተማ ዙሪያ ባሉ ፓርኮች ላይ በሰፊው እንደሚሠራ ጠቁመዋል።

በረሃማነትን ለመከላከልና አረንጓዴ ልማትን ለማስፋፋት ችግኝ ከመትከል ባለፈ መንከባከብ ላይ ያተኮረ ሥራ መጠናከር አለበት ያሉት አቶ ደጀኔ፤ ለሰው ልጅ ኑሮ የተመቻቸ የአየር ንብረት በዘላቂነት ለመገንባት ሁሉም ዜጋ የአረንጓዴ ልማት ሥራውን ከመኖሪያ አካባቢው መጀመር እንዳለበት ገልጸዋል።

ከልማት ማህበሩ ጎን በመሆን በተለያዩ የልማት ሥራዎች ላይ በጋራ እየሠሩ ያሉትን ሥራ ለአገር አቀፍ ደን ሽፋን እድገት አስፈላጊ በመሆኑ ምስጋና አቅርበዋል።

የአረንጓዴ ልማት እንቅስቃሴ በውጤታማነት ለማከናወን የኃይማኖት አባቶች፣ የአገር ሽማግሌዎችና አባገዳዎችና ኅብረተሰቡ የሚያከናውኑትን ቅንጅታዊ ሥራ ማጠናከር አለባቸው ሲሉ መልዕክት አስተላልፈዋል።

# ቻይና ለኢትዮጵያ ከቀረጥ ነፃ ንግድ መፍቀዷ የውጭ ምንዛሬ እንዲያድግ ይረዳል

**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ በቻይና ገበያ ምርቶቿን ከቀረጥ ነፃ ለማቅረብ ፈቃድ ማግኘቷ ያለባትን የውጭ ምንዛሬ ክምችት ክፍተት ለመሙላት ያስችላታል ሲሉ የምጣኔ ሀብት መምህር ዶክተር ይንገስ አለሙ ተናገሩ።

በጎንደር ዩኒቨርሲቲ የምጣኔ ሀብት መምህር ዶክተር ይንገስ አለሙ በተለይ ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ እንደገለጹት፤ በአሁኑ ጊዜ በማደግ ላይ ያሉ አገሮች በተወሰነ መልኩ እንዳይቸገሩ ከቀረጥ ነፃ በሆነ መንገድ ምርታቸውን የሚሸጡበት ሂደት እየተፈጠረ ነው። ይህ ዓይነት አካሄድ ለፈቃጁና ለአቅራቢው አገር ኢኮኖሚያዊ ትስስርን ይፈጥራል። የአገራትን ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነትም ያጠናክራል።

ኢትዮጵያ በቻይና ገበያ ምርቶቿን ከቀረጥ ነፃ ለማቅረብ ፈቃድ ማግኘቷ በአገራቱ መካከል ከሚፈጥረው ዲፕሎማሲያዊና ኢኮኖሚያዊ ትስስር ባሻገር ከፍተኛ ጥቅም አለው ያሉት ዶክተር ይንገስ፤ ኢትዮጵያ ከፍተኛ ትርፍ በማግኘት ያለባትን የውጭ ምንዛሬ ክምችት ክፍተት መሙላት እንድትችል እና የውጭ ምንዛሬ ክምችቷ በከፍተኛ ደረጃ ከፍ እንዲል ምክንያት ይሆናል ብለዋል።

እንደ ዶክተር ይንገስ ማብራሪያ፤ ከቀረጥ ነፃ በሆነ መንገድ ምርቶችን እንድታቀርብ ቻይና ለኢትዮጵያ መፍቀዷ ቻይና የምትፈልገውን የሸቀጥ ዓይነት በቀላሉ እንድታገኝ ያደርጋታል። ይህ በተራውም ቻይና ከኢትዮጵያ ከምታስገባቸው ምርቶች እና ሸቀጦች



ቻይና ከቀረጥ ነፃ ንግድ መፍቀዷ በተለይ ለኢንዱስትሪ ፓርኮች ትልቅ ዕድል የሚሰጥ ነው

ላይ ዕሴት ጨምራ ኤክስፖርት ለማድረግ ጠቀሜታ ይኖረዋል።

ኢትዮጵያ ሸቀጦችን ያለ ቀረጥ መላኳ የውጭ ንግድ ግንኙነቷ እንዲሰፋ ዕድልን ይፈጥራል ያሉት የምጣኔ ሀብት ምሁሩ፤ ከፍተኛ ትርፍ በማግኘት ያለባትን የውጭ ምንዛሬ ክምችት ክፍተት በከፍተኛ ደረጃ ከፍ እንዲል ምክንያት ይሆናል ሲሉ አስረድተዋል። ኢትዮጵያ ከቻይና፣ ከደቡብ ኮሪያ፣ ከሩሲያ እና ከሌሎች የምዕራባውያንና የአፍሪካ አገሮች ጋር ያላትን ግንኙነት በማጠናከር የውጭ ምንዛሬ ክምችቷን ከፍ ማድረግ እንደሚያስፈልግም ገልጸዋል።

እንደ መምህሩ ገለጻ፤ ኢትዮጵያ በርካታ ምርቶችን አምርታ በቻይና ገበያ ያለ ቀረጥ ለመሸጥ ዕድል ከተሰጣት በኢትዮጵያ ያለውን የኢንቨስትመንት ፍላጎትን ከፍ ያደርገዋል። በዚህ መልክ የሸቀጦች ልውውጥ ሲፈጠር ባለሀብቶች በቀላሉ በተፈጠረው የገበያ እንቅስቃሴ ገብተው ገበያውን ያነቃቁታል። ለአምራች ዘርፉም ከፍተኛ መነሳሳትን በመፍጠር ኢንቨስትመንት እንዲበዛ ከማድረጉም በላይ የሥራ ዕድልም በከፍተኛ ሁኔታ ይፈጠራል።

በሌላ በኩል ኢትዮጵያ ከቀረጥ ነፃ ምርቶቿን በቻይና ገበያ እንድትሸጥ ቻይና ለመፍቀድ ማሰቧ ከአገራዊ ሁኔታዎች አንፃር የሚደገፍ ቢሆንም በዘላቂነት የሚመረጥ አለመሆኑን ዶክተር ይንገስ ጠቁመዋል። ከቀረጥ ነፃ የንግድ ፈቃዱ ኢትዮጵያ ራሷን እስክትችል ጠቀሜታ ቢኖረውም ሁልጊዜ ከቀረጥ ነፃ ገበያ ተጠቃሚነትን መጠበቅ አስፈላጊ አይደለም ብለዋል።

በአገር ውስጥ ያለውን የፖለቲካ ልዩነትን፣ ትኩሳትን በመፍታትና አንድነትን ከፍ በማድረግ ከፍተኛ ምርት በማምረት ካደጉ አገሮች ተርታ መሰለፍ እንደሚያስፈልግ የጠቆሙት የኢኮኖሚ ምሁሩ፤ ይህ ዓይነት አካሄድ ከጉዳቱ ጥቅሙ የሚያመዝን በመሆኑ ከጊዜያዊ ጥቅም ወጥቶ ምርትና አገልግሎትን በመገንባት ወደ ዘለቄታዊ ራስን የመቻልና ተወዳዳሪነት መግባት አስፈላጊ ነው ብለዋል።

አሜሪካ ኢትዮጵያን በሰብአዊ መብት ጥሰት አሳባ ከአጎዋ ተጠቃሚነት እንዳገደቻት ወደፊት ቻይናም በተራዋ የሰጠችውን ዕድል ልትዘጋ እንድምትችል ማሰብ ጥሩ ነው ሲሉም መክረዋል። ኢትዮጵያ በተፋጠነ መልኩ ራሷን እንድትችል ለማድረግ የውስጥ የፖለቲካ ትኩሳትን ጤናማ ማድረግና የተጀመረውን የበጋ ስንዴ ምርትን አጠናክሮ መቀጠል እና በሌሎች ዘርፎችም ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ እንደሚገባ ጠቁመዋል።



# በአዲስ አበባ ሁሉንም ባቡሮች ወደሥራ ለማስገባት እየተሠራ ነው

## - በዘርፉ የሚፈጸሙ ወንጀሎችን ለመከላከል ለፖሊሶች ስልጠና እየተሰጠ ነው

**ሞገስ ተስፋ**

አዲስ አበባ፡- በሚቀጥሉት ሰባት ወራት 41ዱንም ባቡሮች ወደ ሥራ ለማስገባት እየተሠራ መሆኑን የአዲስ አበባ ቀላል ባቡር አገልግሎት አስታወቀ። በባቡር መሠረተ ልማት ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎችን ለመከላከል ለአንድ ሺ 500 ፖሊሶች ስልጠና እየተሰጠ ነው።

የአዲስ አበባ ቀላል ባቡር ትራንስፖርት አገልግሎት ድርጅት ዋና ሥራ አስኪያጅ ኢንጂነር ሙሉቀን አሰፋ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ከዚህ በፊት በባቡር መሠረተ ልማት ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች ከፍተኛ ነበሩ። ባለፉት አምስት ወራት አዲስ አበባ ፖሊስ በባቡር መስመር ላይ የሚፈጸሙ ዝርፊያዎችን በመቆጣጠር ከፍተኛ ሥራ ሠርቷል።

በዚህም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ትንንሽ ወንጀሎች ከመከሰታቸው በስተቀር ከዚህ በፊት እንደነበረው ትልቅ ችግር ሆኖ አልቀጠለም። በከተማ አስተዳደሩ ፖሊስ በተሠሩ ሥራዎች ተጨባጭ ለውጥ መጥቷል። ይህም የሆነው ከፖሊስ፣ ከመብራት ኃይል፣ ከባቡር ጋር የተዋቀረው ግብረኃይል ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ ውጤት በመምጣቱ ነው ብለዋል።

እንደ ኢንጂነር ሙሉቀን ገለጻ፤ ባቡሮቹ በራስ አቅም የሚጠገኑበት ሃያትና ቃሊቲ መዳረሻዎች ላይ የጥገና ሱቆች አሉ። በተለይ የባቡር ጎማና አንዳንድ መለዋወጫዎች ወደ ቻይና ሄደው ጥገና ይደረጋሉ። ለዚህም ከቻይና መንግሥት ጋር የተደረሰ ስምምነት አለ። የባቡር «ስፔር ፓርቶች» ወደ ቻይና ተልከው መሠራት የሚገባቸው በፍጥነት እየተጠገኑ እንዲመጡ እየተደረገ ነው። በሚቀጥሉት ስድስት ሰባት ወር ውስጥ ባቡሮችን ሙሉ ለሙሉ ወደ ሥራ ለማስገባት እየተሠራ ነው።

የባቡር ጎማ ለብቻ አውልቆ ለማስገባት ችሎታን ይጠይቃል ያሉት ዋና ሥራ አስኪያጁ፤ በስድስት አመት የሚመጡ ጥገናዎች አሉ። በአገር ውስጥና ወደ ቻይና ተልከው መጠገን ያለባቸው መለዋወጫዎች አሉ ብለዋል።


በሚቀጥሉት ሦስት ወራት ውስጥ ለባቡር ለብቻ ጥበቃ የሚያደርጉ አንድ ሺ አምስት መቶ ፖለሲ ስልጠና እየተሰጠ መሆኑን የገለጹት ኢነጂነር ሙሉቀን፤ ስልጠናው ዝርፊያን መከላከል ነው። ከዚህ በፊት የክፍለ ከተማ መገናኛዎች ላይ የተለያዩ ችግሮች ስለነበሩ ስርቆቱን መከላከል አልተቻለም። ነገር ግን የሚሰለጥኑት ፖሊሶች ወደ ሥራ ሲገቡ በክፍለ ከተማ ወሰን ሳይገደቡ የቀንና የማታ ጥበቃ ያደርጋሉ ብለዋል።

በሥራ ላይ 17 ባቡሮች እንዳሉ የገለጹት ዋና ሥራ አስኪጁ፤ 41ዱም ባቡሮች በአግባቡ የትራንስፖርት አገልግሎት ባለመስጠታቸው የትራንስፖርት ፈላጊዎች ላይ ያለው ከፍተኛ ጫና በሚቀጥሉት ሰባት ወራት ውስጥ ሙሉ ለሙሉ ወደ ሥራ ሲገቡ በትራንስፖርቱ ላይ ተጨባጭ ለውጥ ይመጣል። በባቡር ብልሽት ምክንያት የሚኖረው መቆራረጥና የሰዓት መጓተት ይቀንሳል ነው ያሉት።

# «በአህጉሪቱ ዘላቂ ሰላምና ኢኮኖሚያዊ ትስስር ለመፍጠር ፖለቲካዊ ቁርጠኝነት ያስፈልጋል»

**- አቶ ትዕግስቱ አወሉ**
**የምሥራቅ አፍሪካ የፖለቲካ ተንታኝ**

**መክሊት ወንድወሰን**



አዲስ አበባ፡- በአህጉሪቱ ዘላቂ ሰላምና ኢኮኖሚያዊ ትስስር ለመፍጠር ፖለቲካዊ ቁርጠኝነት ያስፈልጋል ሲሉ የምሥራቅ አፍሪካ ጂኦፖለቲክስ ተንታኝ አቶ ትዕግስቱ አወሉ ተናገሩ።

የምሥራቅ አፍሪካ የጂኦፖለቲካል ተንታኝ የሆኑት አቶ ትዕግስቱ አወሉ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ በአህጉሪቱ ዘላቂ ሰላምና ኢኮኖሚያዊ ትስስር ለመፍጠር ፖለቲካዊ መሪዎቹም የፖለቲካ፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ትስስር በመፍጠር ሕዝባቸውን ከድህነት ለማላቀቅ በቁርጠኝነት ሊቆሙ ይገባል፡፡

ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ትስስሩን የመፍጠር ሥራ ወደ ሕዝብ ሊወርድ ይገባል ያሉት አቶ ትግስቱ፤ ለዚህ ደግሞ አዋጭ የፖለቲካ ስትራቴጂ መቅረጽ እና ሀብት ማሰባሰብ ወሳኝ ነው ብለዋል፡፡

በተጨማሪም በአንዳንድ የአፍሪካ አገራት ያለው ብልሹ አሠራር፣ የኢኮኖሚ ጥገኝነት፣ ግጭት እና ሌሎችም ምክንያቶች አህጉሪቱ የሚፈለገውን እድገት እንዳታስመዘግብ አሉታዊ ተጽዕኖ አሳድሯል ብለዋል።

እንደ አቶ ትዕግስቱ ገለጻ፤ በቀጣናው ውስጥ ያሉት አብዛኞቹ የፖለቲካ፣ የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች የቅኝ ገዥዎች ውርስ ናቸው፡፡ አህጉሪቱን ወደ አለመረጋጋት፣ ወታደራዊ መፈንቅለ መንግሥት፣ የእርስ በርስ ጦርነት፣ የድንበር ውጥረቶችን እና ሌሎች ውጣ ውረዶችን የሚያደርሱትም እነዚሁ ጉዳዮች ናቸው ሲሉ ተናግረዋል፡፡

ሆኖም ምንም እንኳን አንዳንድ ፈተናዎች ቢኖሩም ለአፍሪካ ቀንድ አገራት ትልቅ ዕድሎችም አሉ ያሉት አቶ ትዕግስቱ፤ ይህን ከግምት ውስጥ በማስገባት የአፍሪካ መሪዎች ከቅኝ ግዛት ያተረፉትን መጥፎ ቅርስ ለመቀልበስ እና በማህበራዊና በኢኮኖሚያዊ የተሻለች አህጉር ለመገንባት የሚረዳዱበት ጊዜ አሁን ነው ብለዋል፡፡

ፓን አፍሪካኒዝምን ማጎልበት፣ አህጉራዊ ውህደትን መፍጠር፣ የውስጥ ችግሮችን በድርድር እና በሰላማዊ መንገድ መፍታት በአፍሪካ መለመድ እንዳለበት ጠቁመው፤ በሰሜናዊው የአገሪቱ ክፍል ለሁለት ዓመታት የዘለቀውን ግጭት ለማስቆም የፕሪቶሪያ የሰላም ስምምነት ለዚህ ጥሩ ማሳያ ነውም ብለዋል።

በተጨማሪም የአፍሪካ ኅብረት ወሳኝ ነጥቦች ማለትም ከጦር መሣሪያ ድምጽ የጸዳች አፍሪካን ለመፍጠር የአፍሪካ መሪዎች እና የሚመለከታቸው ዓለም አቀፍ አጋሮች ቁርጠኝነት የሚጠይቁ ናቸው ያሉት አቶ ትዕግስቱ፤ የአፍሪካ ኅብረት አላማዎችን ለማሳካት በአፍሪካ መሪዎች መካከል ጠንካራ ቁርኝት እና የባለቤትነት ስሜት ሊፈጠር እንደሚገባ ገልጸዋል፡፡

ዜና

# ተቋሙ ታራሚዎችን በመልካም ባህሪ ለማነጽ በትኩረት እየሠራ ነው

**አማን ረሺድ**

አዲስ አበባ፡- የሕግ ታራሚዎችን በመልካም ባህሪ ለማነጽ ቤተ መጽሐፍት ላይ በትኩረት እየሠራ መሆኑን የወላይታ ሶዶ ማረሚያ ተቋም አስታወቀ፡፡

የወላይታ ሶዶ ማረሚያ ተቋም ኃላፊ ኮማንደር ደጀኔ ዳርጮ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ማረሚያ ተቋሞች በተለያዩ ወንጀሎች በሕግ ተከሰው የእስር ቅጣት የሚፈረድባቸውን የሕግ ታራሚዎች ተረክበው የማነፅ፣ የማስተማርና አመለካከታቸውን በመልካም የመቀየር ኃላፊነት አለባቸው፡፡ ይህን ከባድ ኃላፊነት ለመወጣት ታራሚዎች ላይ ትኩረት ተደርጎ መሥራት ይገባዋል፡፡

በተለይ የታራሚዎችን ባህርይ ለማነፅ በማረሚያ ቤቶች ቤተ መጽሐፍት ላይ ትኩረት ተሰጥቶ መሠራት ይኖርበታል ያሉት ኮማንደር ደጀኔ፤ የወላይታ ሶዶ ማረሚያ ተቋም ታራሚዎቹን የማነፅ፣ የማስተማር እና አመለካከታቸውን በመልካም የመቀየር ሥራውን ለማፋጠን በግቢ ውስጥ ለታራሚዎች ቤተ መጽሐፍት አቋቁሞ እየሠራ እንደሚገኝ ተናግረዋል፡፡

የሕግ ታራሚዎች ከቤተሰብና ከማህበረሰቡ ተለይተው በማረሚያ ተቋም በሚቆዩበት ወቅት ለአዕምሮ ጭንቀትና ለተለያዩ ችግሮች እንዳይጋለጡና እራሳቸውን በዕውቀት እንዲያበለጽጉ ቤተ መጽሐፍት ትልቅ ሚና እንዳለው ጠቁመዋል፡፡


ወላይታ ሶዶ ከተማ

በቤተ መጽሐፍት ውስጥ እንዲካተቱ የተደረጉት መጽሐፍት ትምህርታዊ፣ ልቦለዶች እና የተለያዩ ግለሰቦች በማረሚያ ተቋም ቆይታቸው ካሳለፏቸው ተሞክሮዎች በመነሳት የፃፏቸው መጽሐፍት በመሆናቸው የታራሚዎችን አመለካከት ለማረም እንደሚረዳ ኮማንደር ደጀኔ አስረድተዋል፡፡

በቅርቡም የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቤተ መዛግብትና ቤተ መጽሐፍት ኤጀንሲ ለወላይታ ሶዶ ማረሚያ ተቋም መጽሐፍትን ማበርከቱን የተናገሩት ኃላፊው፤ ይህም የማረምና የማነጽ ሥራውን ለማሳለጥና በርካታ ታራሚዎች ወደ ንባብ እንዲመጡ ይረዳል ብለዋል፡፡

ሌሎች ማረሚያ ተቋማት ታራሚዎችን በአንድ ቦታ በመሰብሰብ ብቻ ለውጥ ማምጣት እንደማይቻል ተረድተው ከመንግሥትና መንግሥታዊ ካልሆኑ ተቋማት ጋር በመተባበር ቤተ መጽሐፍት ላይ በትኩረት ሊሠሩ ይገባል ብለዋል፡፡

በተጨማሪም ታራሚዎች የባህሪ ለውጥ እንዲያመጡ በተቋሙ ውስጥ የሥነልቦና፣ የሶሾሎጂና የሥነ ምግባር ባለሙያዎች በመኖራቸው ቀደም ሲል ከፈጸሙት ወንጀል እንዲማሩና መልካም ሥነ ምግባር በመላበስ ወደ ማህበረሰቡ እንዲቀላቀሉ ሙያዊ ድጋፍ እየተደረገላቸው መሆኑን አብራርተዋል፡፡

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቤተ መዛግብትና ቤተ መጽሐፍት ኤጀንሲ በቅርቡ ለወላይታ ሶዶ ማረሚያ ተቋም 100 ሺህ ብር ዋጋ የሚያወጡ መጽሐፍትን ማበርከቱ የሚታወስ ነው፡፡

# ክልሉ ለ215 ባለሀብቶች...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ናቸው፡፡

አቶ ሐልጌዮ እንደሚሉት ፈቃድ የተሰጣቸው ባለሀብቶች አስፈላጊውን ቅድመ ሁኔታ አሟልተው የቀረቡ ሲሆን፣ ወደሥራ ሲገቡ ለ8ሺህ 961 ዜጎች በቋሚነት እንዲሁም ለ21ሺህ 580 ዜጎች ጊዜያዊ በድምሩ ለ30ሺህ 541 ዜጎች የሥራ ዕድል ይፈጥራሉ ብለዋል፡፡

በክልሉ ወደ ሥራ ገብተው ማምረት የጀመሩ ኢንዱስትሪዎችም ባለፉት ስድስት ወራት ውስጥ ለ44ሺህ 621 ዜጎች ቋሚ እና ጊዜያዊ የሥራ ዕድል እንደፈጠሩና ከዚህ ውስጥ 16ሺህ 508 ሴቶች መሆናቸውን ኃላፊው ገልጸዋል፡፡

አዳዲስ ኢንቨስትመንቶች ወደ ክልሉ መሳብ ላይ ትኩረት ተሰጥቶ እየተሠራ በመሆኑም ከባለፈው ዓመት ጋር ሲነጻጸር በዚህ ዓመት በርከት ያሉ ባለሀብቶች ወደ ክልሉ መምጣታቸውን የተናገሩት ኃላፊው ከባለፈው አመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር የ700 ሚሊዮን ብር ብልጫ እንዳለው ጠቁመዋል፡፡

ክልሉ ኢንቨስትመንቶችን ከመደገፍ አንጻርም በየጊዜው የሚቀርበውን የመሬት ጥያቄ ለመፍታት ባለፉት ስድስት ወራት የመሬት ጥያቄ ካቀረቡት 96 ፕሮጀክቶች ውስጥ ለ86ቱ 6719 ሄክታር መሬት በክልሉ ካቢኔ ጸድቆ በምደባ እንደተሰጣቸው የቢሮ ኃላፊው ተናግረዋል፡፡

በሥራ ላይ ያሉትን ባለሀብቶች የመደገፍ እና የማበረታታት ሥራ ይሠራል ያሉት አቶ ሐልጌዮ በአግባቡ ለማይሰሩት ደግሞ ከማስጠንቀቂያ እስከ መሬት መንጠቅ የሚደርስ እርምጃ እንደተወሰደም ጠቁመዋል፡፡

አቶ ሐልጌዮ ጂሎ እንደሚሉት ባለፉት ስድስት ወራት 36 ፕሮጀክቶች ተለይተው ለ26ቱ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ፣ ለ5ቱ የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ፣ አንድ መሬት ቅነሳ እንዲሁም በሁለቱ ፕሮጀክቶች ላይ የውል እና ፍቃድ ስረዛ እርምጃ ተወስዷል፡፡

የሎጅስቲክስ እጥረት፣ መሬት በካቢኔ ከጸደቀ በኋላ ለርክክብ መዘግየት እንዲሁም ፍቃድ የወሰዱ ባለሀብቶች ቶሎ ወደ ሥራ ያለመግባት የባለፉት ስድስት ወራት ተግዳሮቶች እንደነበሩም ኃላፊው ጠቁመዋል፡፡

አቶ ሐልጌዮ እንደገለጹት፣ ቢሮው ከአገልግሎት አሰጣጥ አንጻር የአንድ መስኮት አገልግሎት እየሰጠ በመሆኑ ባለሀብቶች ባሉበት ሆነው አገልግሎት እንዲያገኙ እየተሠራ ነው፡፡ የክልሉ ተስማሚ የአየር ጸባይ ለኢንቨስትመንት ምቹ ነው ያሉት ኃላፊው የአገር ውስጥ እና የውጭ ባለሀብቶች በተፈጥሮ ወደ ታደለው የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል በመምጣት እንዲያለሙ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

# አዲስ አበባ በቀን 1 ነጥብ 1...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

725ሺህ ሜትር ኪዩብ ብቻ ነው። ይህ በአቅርቦትና ፍላጎት መካከል ልዩነት መኖሩን የሚያሳይ ነው።

በዚህ የተነሳ በተያዘው የበጀት ዓመት ተጨማሪ 75ሺህ ሜትር ኪዩብ ውሃ እየለማ መሆኑን የጠቀሱት ዳይሬክተሯ፤ የታሰቡ ፕሮጀክቶች ደረጃ በደረጃ ወደ ሥራ ሲገቡም አቅርቦቱ ይሻሻላል ብለዋል።

የከተማዋ እድገትና መስፋፋት፣ የሪል ስቴቶችና ሆቴሎች መበራከት፣ ውሃን እንደ ግብዓት የሚጠቀሙ ፋብሪካዎች መብዛት በውሃ ስርጭቱ ላይ ትልቅ ተጽዕኖ ፈጥረዋል ያሉት ዳይክተሯ፤ ተቋሙም ሆነ የከተማ አስተዳደሩ ችግሩን ለመቅረፍ ፍላጎት እንዳለውና የአጭር፣ የመካከለኛና ረጅም ጊዜ እቅድ አውጥቶ እየሠራ መሆኑን ገልጸዋል።

እንደ ወይዘሮ ሰርካለም ገለጻ፤ በውሃ አቅርቦት ዙሪያ የሚነሱ ቅሬታዎች መንስኤ የአቅርቦትና ፍላጎት አለመጣጣም ነው።

በዚህ ምክንያት ውሃ በፈረቃ እንዲሆን መደረጉን ጠቁመው፤ በፈረቃ ፕሮግራም ከተጀመረ ወዲህም ብዙ ጊዜ ሰዎች ቅሬታ የሚያቀርቡት የፈረቃ ውሃ ሳይደርሳቸው ሲቀር እንደሆነ አንስተዋል። ይህ በዋናነት በኤሌክትሪክ መቆራረጥና የመስመር ስብራት ሲኖር የሚያጋጥም እንደሆነ ጠቅሰዋል።

ተቋሙ ውሃ ለኅብረተሰቡ በፈረቃው መድረሱን የሚቆጣጠርበት ሥርዓት እንዳለው፤ በዋናነት በከፍታማ አካባቢና በጋራ መኖሪያ ቤት የመጨረሻው ወለል ላይ ያሉ ነዋሪዎች ፈረቃው ስለመድረሱ የሚቆጣጠር ቡድን መኖሩንና ሳይደርሳቸው ሲቀር ለባለሙያዎች በመንገር ችግሩ እንዲፈታ ይደረጋል ብለዋል።

ዳይሬክተሯ እንዳሉት፤ በተቻለ መጠን በወጣው የፈረቃ ፕሮግራም ለመጠቀም ጥረት ይደረጋል። አጋጣሚ ሆኖ የመስመር ስብራትም ሆነ የኤሌክትሪክ መቆራረጥ ረጅም ጊዜ በሚወስድበት ወቅት በቦቴ ተሽከርካሪ ውሃ ለኅብረተሰቡ ይቀርባል። አሁን ካለው የዋጋ ንረትና ከእያንዳንዱ የዕቃ አቅርቦት ጋር ተያይዞ ያለው ሁኔታም ትልቅ ፈተና ሆኗል።

የውሃ አቅርቦት ከፍላጎት ጋር አለመጣጣም ተቋሙ ፈልጎት ያመጣው አይደለም ያሉት ዳይሬክተሯ፤ ችግሩን ለማቃለል የከተማ አስተዳደሩ በተቻለ መጠን ከፍተኛ በጀት መድቦ እየተሠራ እንደሆነ አመላክተዋል። ለአብነትም በዚህ ዓመት በ570 ሚሊዮን ብር በመበጀት 75ሺህ ሜትር ኪዩብ ውሃ ለማልማት እየተሠራ እንደሆነ ገልጸዋል።

ይህንን በሚመለከት እስካሁን በተደረጉ ሥራዎች 20 የውሃ ጉድጓዶች መቆፈራቸውንና ከዚህ ውስጥም አንዱ ሙሉ ለሙሉ ወደ ሥርጭት መግባቱን ጠቁመዋል። ሌሎችም የፓምፕ ተከላ፣ የመስመር ዝርጋታና ከሲስተም ጋር የማገናኘት ሥራዎች እንደሚቀራቸው ተናግረዋል። ሌሎች ሰባት የሚደርሱ ጉድጓዶች ቁፋሮ ላይ መሆናቸውን ገልጸው፤ እስከ ሰኔ 30 ድረስ ተጠናቅቀው በውሃ እጥረት ምክንያት የሚነሳውን የመልካም አስተዳደር ችግር እንደሚፈቱ ተናግረዋል።

# ስንዴን ወደ ውጭ ገበያ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

የሚሠሩትም በዚሁ ምክንያት እንደሆነ አስረድተዋል።

በተለይም እንደ ኢትዮጵያ የዋጋ ግሽበት በተደጋጋሚ በሚያጠቃው ኢኮኖሚ ላይ የሚመረተው ስንዴ ለአገር ውስጥ ገበያ ብቻ ቢቀርብ ምናልባትም ግሽበቱን በጊዜያዊነት ሊያረጋጋውና ባለበት ሊያቆመው ይችላል። ነገር ግን የረጅም ጊዜ መፍትሔ ሆኖ ኢኮኖሚው ላይ መሠረታዊና ዘላቂ ለውጥ ሊያመጣ አይችልም ብለዋል።

የኤክስፖርት ውጤት በአጭር ጊዜ የሚታይ ባይሆንም ረዘም ያለ ጊዜ በመውሰድ የአገር ኢኮኖሚ አስተማማኝ መሠረት እንዲኖረውና የዜጎች ኑሮ እንዲሻሻል ያደርጋል ያሉት ዶክተር ሞላ፤ ከዚህ አንጻር ስንዴን ወደ ውጭ ገበያ መላክ ተገቢነት ያለውና የአገሪቷን ኢኮኖሚ በአስተማማኝ መሠረት ላይ ማኖር የሚያስችል ነው ብለዋል።

«በስፋት የተመረተውን የስንዴ ምርት በአገር ውስጥ ገበያ ማቅረብ አሁን ባለው ሁኔታ እሳት የማጥፋት ሥራ ነው። እሳት በማጥፋት ደግሞ የአጭር ጊዜ ችግርን መፍታት ይቻል ይሆናል፤ ነገር ግን በየጊዜው ለኢኮኖሚ ዕድገት ደንቃራ የሆኑ ችግሮችን መፍታት አያስችልም» የሚሉት ዶክተር ሞላ የውጭ ተሞክሮዎችም ይህንኑ ነው የሚያሳዩት ይላሉ።

እርሳቸው እንዳሉት፤ ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ ከፍተኛ የዋጋ ግሽበት ያጋጠማቸው አገራት ለአብነትም ጀርመን እና ጃፓን ችግሩን መፍታት የቻሉት ኤክስፖርት ላይ መሠረት ያደረገ ኢኮኖሚ መገንባት በመቻላቸው ነው።

በተመሳሳይ የእንግሊዞች ታሪክም ይህንኑ ተሞክሮ ያሳየናል ያሉት ዶክተር ሞላ፤ እንግሊዞች ‹‹ሁላችንም ለአንድ ዓመት እንራብ፤ ከዚያ በኋላ ግን ረሃብ አይነካንም›› በሚል ስትራቴጂ ተነሳስተው ኢኮኖሚያቸውን ማሳደግ እንደቻሉ አስታውሰዋል። በኢትዮጵያም ይህን መሰል ስትራቴጂ መከተል ካልተቻለ ጠንካራ ኢኮኖሚን መገንባት አይቻልም። ስለዚህ ጠንካራ ኢኮኖሚን ለመገንባት እንዲህ ዓይነት ልምድን ማዳበር ይገባል ብለዋል።

ኢትዮጵያ በበጋ መስኖ ስንዴ አልምታ ኤክስፖርት ማድረግ መጀመሯ የሚበረታታና ቀጣይነት ሊኖረው የሚገባ እንደሆነ የገለጹት ዶክተር ሞላ፤ አሁን ላይ በአገር ውስጥ የስንዴ እጥረት ቢያጋጥምም እንኳ ችግሩን ታግሶ ማለፍና እንደ ጀርመን፣ ጃፓንና እንግሊዞቹ ሁሉ ዘላቂ መፍትሔ ማምጣት ያስፈልጋል ነው ያሉት።

‹‹አሁን የተጀመረው የስንዴ ኤክስፖርት ንግድ ለኢኮኖሚያዊ ዕድገቱ መሠረት የሚጥል ነው›› ያሉት ዶክተር ሞላ፤ ይህን መሠረት ማጽናትና በቀላሉ እንዳይናጋ መሥራት ያስፈልጋልም ብለዋል። አሁን ላይ በየጊዜው ለሚፈጠሩ ችግሮች ጊዜያዊ መፍትሔ እየሰጡ መጓዝ መሠረቱ የጸና ኢኮኖሚ መገንባት አላስቻለም። በኢኮኖሚው ጠንካራ መሠረት ለመጣል የወጪ ንግድን ተወዳዳሪ ማድረግ፤ ዘመኑ የሚጠይቀውን ዕውቀትና ቴክኖሎጂ መጠቀም የግድ ነው ይላሉ።

ይህም ኢኮኖሚውን በአስተማማኝ መሠረት ላይ መጣል ከማስቻሉም ባለፈ በየጊዜው የሚፈጠሩ ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን መፍታት የሚያስችል እንደሆነ አስረድተዋል።

‹‹የኤክስፖርት ንግድ ቀጣይነት ከሌለው ውጤት አይኖረውም›› ያሉት ዶክተር ሞላ፤ ለቀጣይነቱ መረጋገጥ መንግሥት፣ ባለሀብቱና አምራቹ የድርሻቸውን መወጣት ይጠበቅባቸዋል ብለዋል። በተለይም ስንዴ አምራች የሆኑ አካባቢዎችን እየለዩ በዚያ ላይ እየጨመሩ መሄድና መረጃዎችን በማጥናት በዓለም ገበያ ምን ዓይነት ጥራትና ምርት ይፈለጋል፤ የማምረት ዘዴው በምን መልኩ ይሁን ወዘተ... የሚለውን በመለየት ለአርሶ አደሩ ግንዛቤ መፍጠር እንዲሁም የዕውቀትና የቴክኖሎጂ ሽግግር በማድረግ ቀጣይነቱን ማረጋገጥ የግድ እንደሆነም ጠቁመዋል።

የኤክስፖርት ንግዱን ለማጠናከር ከስንዴ በተጨማሪ ሌሎች ምርቶችንም ወደ ኤክስፖርት ማስገባት ጠንካራ ኢኮኖሚን ለመገንባት ብቸኛው አማራጭ እንደሆነ የገለጹት ዶክተር ሞላ፤ አሁን ላይ ያለውን ችግር ተቋቁሞ በማለፍ የወጪ ንግዱን ማሳደግ ከተቻለ የአገሪቱን ኢኮኖሚ አስተማማኝ መሠረት እንዲኖረው ማድረግ ያስችላል ብለዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ሀገራዊ ተግዳሮቶችን በብቃት ለመመከት ኅብረብሄራዊ አንድነታችን ይጠናከር!

ኢትዮጵያ ጥንታዊ ስልጣኔ እና ከአብዛኞቹ የዓለም ሀገራት ጋር ሲነጻጸር ረጅም የስርዓተ መንግስት ታሪክ ያላት ሀገር ነች፡፡ ይህች ጥንታዊት ሀገር በየዘመናቱ የሚያጋጥሟትን ፈተናዎች በማለፍ ያላትን ሉዓላዊነት ክብርና ሞገስ ጠብቃ ዛሬ ላይ ደርሳለች፡፡ ዓድዋን፤ መተማንና ካራማራን በመሳሰሉ የጦር አውድማዎች የሀገርን ሉአላዊነትና ዳር ድንበር አላስደፍርም ያሉ ጀግኖች ልጆቿም ደማቸውን አፍስሰው፤ አጥንታቸውን ከስክሰው ከነክብሯ ለዛሬው ትውልድ አስረክበዋል፡፡

የዛሬው ትውልድም የአያትና ቅድመ አያቶቹን አደራ በመረከብም በጦር ሜዳ ውሎውም ሆነ በልማት ዘርፉ የራሱን አሻራ በማሳረፍ ላይ ይገኛል፡፡ ለሀገሩ ሉዓላዊነት መታፈርና ለዳርድንበሩ መከበር በተጠራበት መስክ ሁሉ በመዋደቅ የቀደምት አያቶቹን ታሪክ ደጋግሞ ጽፏል፡፡ ከዚያም አለፍ ብሎ ኢትዮጵያ በዕድገት ጎዳና እንድትጓዝ የቻለውን ሁሉ እያደረገ ነው፡፡ ጀግንነት በጦር ሜዳ ብቻ እንዳልሆነ በመረዳትም የዓባይ ግድብ የመሳሰሉ ዘመን ተሻጋሪ ፕሮጀክቶቹን በራሱ ገንዘብና ዕውቀት በማገዝ ኢትዮጵያን ከብልጽግና ማማ ላይ ለማቆም በመጣር ላይ ይገኛል፡፡

በዚህ ትውልድ ጠንሳሽነት ግንባታው ከ84 በመቶ በላይ የደረሰው የዓባይ ግድብ በርካታ ፈተናዎችና አሜካላዎች ቢገጥሙትም በዚህ ትውልድ አይበገሬነት ዛሬ ከራስ አልፎ ለጎረቤት ሀገራት የኢኮኖሚ ነጻነት ብርሃን መሆን ችሏል። የኢትዮጵያን መበልጸግ የማይፈልጉ ሀገራት ግድቡን ለማሰናከልና የትውልዱንም ተስፋ አብሮ ለማጨለም ያልፈነቀሉት ድንጋይ ባይኖርም በፍትሃዊ አቋም፣ በዚህ ትውልድ በሳል አመራርና በሕዝብ ጽናትና የማያቋርጥ ድጋፍ የዓባይ ግድብ ወደፍፃሜ እየተቃረበ ነው፡፡ ኢትዮጵያውያንም የዓባይን ግድብ ለፍጻሜ በማቃረብ እንደ ዓድዋ ሁሉ ዛሬም ለአፍሪካ ሀገራት የኢኮኖሚ ነጻነት ብርሃን ሆነዋል፡፡

ከዚህም አልፎ ኢትዮጵያውያን ከ25 ቢሊዮን በላይ ችግኝ በመትከልም ሌላ የዘመኑን ታሪክ ጽፈዋል፡፡ በዓለም ደረጃ እየተስፋፋ የመጣውንና በቀጣይም የዓለም ሀገራት ስጋት ይሆናል ተብሎ የሚሰጋውን የበረሃማነት መስፋፋት ከወዲሁ ለመመከት ኢትዮጵያውያን እጃቸውን ከአፈር ጋር በማወዳጀት አረንጓዴና ምቹ ዓለምን ለመጪው ትውልድ ለማስረከብ ዜግነታዊ ግዴታቸውን በብቃት በመወጣት ላይ ይገኛሉ፡፡ ይህንኑ ተሞክሮም እንደ ኬንያ ያሉ በርካታ የአፍሪካ ሀገራት በመውሰድም አፍሪካን ለአየር ንብረት ለውጥ የማትበገር አህጉር ለማድረግ በመጣር ላይ ይገኛሉ፡፡ ይኼው የኢትዮጵያውያን ጥረት በቅርቡ በተካሄደው የአፍሪካ ኅብረት 36ኛው መደበኛ ስብሰባ ላይ አድናቆትን በማግኘት አንዱ የዚህ ትውልድ ደማቅ አሻራ ሆኗል፡፡

ኢትዮጵያ በዓድዋ ቅኝ ገዢዎችንና ወራሪዎችን በማሳፈር የድል እና የነጻነት ተምሳሌት ነች፡፡ ሆኖም በጦር ሜዳ የተገኘውን ድል በልማቱም መስክ በመድገም ሀገርን ከስንዴ ልመና ለማውጣት የሚደረገው ጥረት ግቡን ሳይመታ ዓመታት ተቆጥረዋል፡፡ አሁን ግን ታሪክ መቀየር ጀምሯል፡፡ይህ ትውልድ ከእርዳታ ጠባቂነት የሚያላቅቀውን ስንዴን አምርቶ ወደ ውጭ ሀገራት ለመላክ በቅቷል፡፡ በዚህ አመት ብቻ 32 ሚሊዮን ኩንታል ስንዴ ለውጭ ገበያ መቅረቡም የዚሁ ስኬት አንዱ ማሳያ ነው፡፡

ሆኖም የኢትዮጵያ ችግር በአንድና በሁለት ዓመታት የስንዴ ምርት የማይፈታና ተከታታይ በሆነ መልኩ ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ የሚጠይቅ ነው፡፡ ስለዚህም ባለፉት አራት ዓመታት የተደረጉ ለውጦች ኢትዮጵያን ከስንዴ ልመናና ገዢነት ወደ ስንዴ ላኪነት ለማሸጋገር አብቅቷታል፡፡ ይህ ስኬት ትጋትና ትዕግስት ከታከለበት ለዘመናት የተከማቹ ችግሮች በሂደት እየተራገፉ እንደሚመጡ አመላካች ነው፡፡

በተለይም የዛሬው ትውልድ ችግሮችን በመነጋገርና በውይይት መፍታት ከቻለ አሉ የሚባሉትን ችግሮች ሁሉ ወደ ምቹ አጋጣሚ መቀየር ይቻላል፡፡ ለዚህ አብነት የሚሆነው ደግሞ ለሁለት ዓመታት ያህል በኢትዮጵያ መንግስትና በሕወሓት መካከል ሲደረገው የቆውን ጦርነት የውጭ ኃይል ሳይገባበት በምክክርና በውይይት መፍታት መቻሉ ነው፤ ተግባሩም ኢትዮጵያን በአዲስ አስተሳሰብና ጎዳና እንድትራመድ አድርጓታል፡፡ ይህ ተግባር ሀገራችን የሚገጥሟትን ችግሮች ሁሉ በራሷ አቅም የመፍታት አቅም እንዳላትም አሳይቷል፡፡

በአሁኑ ወቅት በኦሮሚያ ቦረናና ጉጂ፤ በደቡብ ክልል በአንዳንድ ቦታዎች እንዲሁም በሶማሌ ክልል የተከሰተው የድርቅ አደጋን ለመመከት ኢትዮጵያውያን እያሳዩት ያለው አንድነትና ወንድማማችነት ኢትዮጵያውያን በየጊዜው የሚገጥሟቸውን ችግሮች በጋራ ክንድ መመከት እንደሚችሉ ጥሩ ማሳያ ነው!


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** :- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ለኢትዮጵያ የዲፕሎማሲ ማዕከልነት እርሾ የሆነው የዓድዋ ድል

**መላኩ ኤሮሴ**

ባህር አቋርጦ ከመጣው የጣሊያን ወራሪ ሰራዊት ጋር ኢትዮጵያዊያን ተፋልመው ድል ያደረጉበት የዓድዋ ጦርነት በዓለም ታሪክ ውስጥ ከሚጠቀሱ ጉልህ ክስተቶች መካከል አንዱ ነው። የአድዋ ጦርነት ድል አህጉራትን አቋርጦ በዓለም ዙሪያ ጉልህ ተጽዕኖን አስከትሏል። ይህ ድል የኢትዮጵያን ነጻነትና ሉዓላዊነት በጽኑ መሰረት ላይ እንዲተከል ከማድረጉ ባሻገር ለኢትዮጵያ ዲፕሎማሲ ማዕከልነት እርሾ የሆነ ነው፡፡ አዲስ አበባ ከኒዮርክ እና ጄኔቭ ቀጥሎ በዓለም ሦስተኛው የዲፕሎማሲ ሚሽኖች ማዕከል እንድትሆን የአድዋ ድል ሚናው የላቀ ነው፡፡

ከዓድዋ ድል ከብዙ አስርት ዓመታት በኋላ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ሲመሰረት ኢትዮጵያ የህብረቱ መቀመጫ እንድትሆን አንዱ ምክንያት የዓድዋ ድል ነው፡፡ ነጮች ብቻም ሳይሆኑ ጥቁሮች ራሳቸው ጭምር ከነጮች እኩል ነን ብለው ለማሰብ በሚቸገሩበት ዘመን ኢትዮጵያዊያን የተቀዳጁት የአድዋ ድል ነጮች በጥቁሮች ላይ የነበራቸውን የሃያልነት ትርክት ከመሰረቱ ቀይሯል። ይህ ለብዙዎች ጥቁሮች የነጻነት ትግል እንዲጀምሩ ጥሩ መሰረት የሆነ ነው፡፡ በዚህም ምክንያት ነው ኢትዮጵያ ለጥቁሮች የነጻነት ቀንዲል ተደርጋ የምትታየው። ኢትዮጵያ ለጥቁሮች የነጻነት ቀንድል መሆኗ ለአፍሪከ ህብረት ለመቀመጫነት እንድትመረጥ ምክንያት ሆኗል፡፡

በእርግጥ በፖለቲካዊ አንድነት ያለው የአፍሪካ ሀገራት ፌዴሬሽን በአስቸኳይ መፈጠር አለበት ሲል በነበረው የካዛብላንካ ቡድን እና ቀስ በቀስ በኢኮኖሚ ትብብር ላይ የተመሰረተ የላላ ትብብር ይኑር ሲል በነበረው የሞኖሮቪያ ቡድን መካከል የነበረውን የሀሳብ መከፋፈል በማስታረቅ ረገድ የኢትዮጵያ መሪዎች የተጫወቱት ሚና ኢትዮጵያ የቀድሞ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት፤ የአሁኑ የአፍሪካ ህብረት መቀመጫ እንድትሆን ዋና ሚና ቢጫወትም ኢትዮጵያ የዓድዋ ድል የራሱን ሚና ተጫውቷል፡፡

በአሁኑ ወቅት አዲስ አበባ የአፍሪካ ህብረት መቀመጫ ከመሆኗ ባሻገር ዓለም አቀፍ ተቋማትም መቀመጫ ነች፡፡ የአፍሪካ ህብረት መቀመጫ መሆኗ በርካታ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ተቋማትም መቀመጫቸውን እዚሁ አዲስ አበባ እንዲያደርጉ ምክንያት ሆኗቸዋል፡፡ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን፣ የተባበሩት መንግስታት የልማት ፕሮግራም፣ ዩኔስኮ በአዲስ አበባ መቀመጫ አላቸው፡፡

አዲስ አበባ ላለፉት 60 ዓመታት የአፍሪካ አንድነት ድርጅት/ የአፍሪካ ህብረት መቀመጫ መሆኗ ለሀገሪቱ ዘርፈ ብዙ ጥቅሞችን እያስገኘላት ሲሆን፤ አዲስ አበባ የአፍሪካ ህብረት መቀመጫ መሆኗ ወሳኝ በሆኑ አህጉራዊ ጉዳዮች ላይ ከሌሎች የአህጉሪቱ ሀገራት በተሻለ መልኩ ድምጽ እንድትሆን እድል ፈጥሮላታል፡፡ ከተማዋ የአህጉሪቱ መሪዎች መሰባሰቢያ መሆኗ በራሱ የሚሰጣት ክብርም አለ፡፡ ኢኮኖሚያዊ ጥቅሞችን መጥቀስ ይቻላል፡፡ ከተማዋ ዳጎስ ያለ ገቢ ከምታገኝባቸው ትላልቅ ኩነቶች መካከል የአፍሪካ ህብረት የመሪዎች ጉባኤ ተጠቃሽ ነው፡፡ ለበርካታ ኢትዮጵያዊያን በቀጥታና በተዘዋዋሪ የስራ እድል ፈጥሮላቸዋል፡፡

የዓድዋ ድል አዲስ አበባ የዲፕሎማሲ ማዕከል እንድትሆን ከማስቻሉም ባሻገር በተለያዩ ሀገራት ኢትዮጵያን ወክለው ለሚሰሩ ዲፕሎማቶቻችንም ትልቅ አቅም ሆኗቸዋል፡፡ አድዋ ኢትዮጵያ በየአገሮች የምትታወቅበት፣ የምትከበርበትና በተለያዩ የዓለም ሀገሮች ለተወከሉ የኢትዮጵያ ዲፕሎማቶች፣ ለኢትዮጵያዊያን እና ትውልደ ኢትዮጵያዊያን ዜጎች እስከ ዛሬም ድረስ የኩራት አክሊል ነው። ለሚመጣው ትውልድ ጭምር የኩራት አክሊል ሆኖ የሚያገለግል ነው፡፡ ይህ ለዲፕሎማሲያችን ትልቅ አቅም የሚሆን ነው፡፡

ድሉ ኢትዮጵያ ከየትኛውም የአፍሪካ ሀገራት ቀድማ በወቅቱ ሀያላን ከነበሩ የአውሮፓ ሀገራት ጋር በጋራ ጥቅም እና እኩልነት ላይ የተመሰረተ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት እንድትጀምርም ረድቷታል። በእርግጥ የኢትዮጵያ ነገስታት ከአድዋ ድል በፊትም ከተለያዩ የዓለም ሀገራት ጋር ግንኙነቶች ያደርጉ ነበር። ከአንዳንዶቹ ጋር ጤናማ ግንኙነት ሲኖራቸው፤ ከአንዳንዶች ጋር ደግሞ ጤናማ ያልሆኑ ግንኙነት እንደነበራት የታሪክ ድርሳናት የሚያወሱን ቢሆንም፤ ከአድዋ ድል በኋላ ኢትዮጵያ ዓለም አቀፍ ትኩረት መሳብ በመቻሏ ከኢትዮጵያ ጋር ይፋዊ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ለመጀመር የሚፈልጉ ሀገራት ቁጥር ከፍ እንዲል ትልቅ ሚና የተጫወተ ድል ነበር፡፡

ድሉ ነጮች በጥቁሮች ላይ የነበራቸውን የሃያልነት ትርክት ከመሰረቱ በመቀየሩ ምክንያት የነጮችን የበላይነት ሲያቀነቅኑ የነበሩ አውሮፓዊያን ጭምር የጥቁሮች ሀገር ከሆነቹው ኢትዮጵያ ጋር ይፋዊ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ለመጀመር፣ በኢትዮጵያ ውስጥ ቆንስላ ጽህፈት ቤቶችን ለማቋቋም እና ከንጉሰ ነገስቱ መንግስት ጋር በተለያዩ የጋራ ጉዳዮች ዙሪያ ስምምነቶችን ለመፈራረም መሯሯጥ የጀመሩት በድሉ ማግስት ነው፡፡

በዓድዋ ድል ማግስት ሀገራት በአዲስ አበባ ቆንስላ ጽህፈት ቤቶችን መክፈት የጀመሩ ሲሆን አዲስ አበባ የበርካታ ሀገራት ኤምባሲዎች ከሚገኙባቸው ከተሞች በግንባር ቀደምትነት ትጠቀሳለች፡፡

ኢትዮጵያን ቅኝ ለመግዛት ቋምጣ የመጣችው ጣሊያን ምኞቷ ሳይሳካ መቅረቱን ተከትሎ የዓድዋ ጦርነት ምክንያት የነበረውን የውጫሌ ስምምነትን ውድቅ የሚያደርገውና የኢትዮጵያን ነጻ ሀገርነት የተቀበለችበትን የአዲስ አበባ ስምምነትን እንድትፈርም ተገዳለች፡፡ በተለይም የአማርኛና የጣሊያንኛ ትርጉሙ ለየቅል የሆኑ አንቀጾች የተካተቱበት እና ለኢትዮጵያ ህልውና አደጋ የጋረጠው የውጫሌ ስምምነት በአዲስ አበባ ስምምነት መሻሩ ለኢትዮጵያ ትልቅ ድል ነበር፡፡

የኢትዮጵያ ዝና በመላው ዓለም ከፍ ማለቱን ተከትሎ ኢትዮጵያ በአፍሪካ ቀንድ ተዓማኒነቷ ከፍ ብሏል፡፡ ተዓማኒነቷ ከፍ ማለቱን ተከትሎ ከጀርባ ሆነው ጣሊያንን በርቺ ሲሏት የነበሩት የወቅቱ የአውሮፓ ሀያላን ሀገራት ከኢትዮጵያ ጋር ስምምነቶችን ለመፈራረም እንዲመጡ አድርጓቸዋል፡፡ ከአድዋ ድል በኋላ ባሉት አስራ ሁለት ዓመታት የኢትዮጵያ አዋሳኝ አካባቢዎችን ይገዙ የነበሩ የፈረንሳይ እና የብሪታኒያ መንግስታት ከኢትዮጵያ ጋር የተለያዩ ስምምነቶችን ተፈራርመዋል፡፡ በርካታ ሀገራት ወደ ንጉሰ ነገስቱ መልዕክተኞችን ለመላክ እና ከኢትዮጵያ ይፋዊ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት እንዲጀምሩ ምክንያት ሆኗል፡፡

የዓድዋ ድል ለአውሮፓዊያን ጭምር ከሀይል ይልቅ ዲፕሎማሲ እንደሚጠቅማቸው ትምህርት ሰጥቶ አልፏል፡፡ ከአድዋ ድል በፊት አውሮፓዊያን በወታደራዊ ሀይል እነሱን የሚገዳደራቸው ሀይል አለ ብለው አያምኑም ነበር፡፡ ዓድዋ አፍሪካ ውስጥ አውሮፓዊያንን የሚገዳደር ወታደራዊ ኃይል እንዳለ አሳይቷል። ለዚያውም የአውሮፓዊያንን ያህል ዘመናዊ መሳሪያ ሳይታጠቅ የአውሮፓ ወታደሮችን ማሸነፍ የሚችል ሀይል እንዳለ ጥሩ ትምህርት ሰጥቷቸዋል። በዚህም ምክንያት ከኢትዮጵያ ጋር በወታደራዊ አቅም ሳይሆን ጥቅማቸውን በዲፕሎማሲ ማሳካት እንዳለባቸው ጥሩ ትምህርት ሆኗቸዋል፡፡

የዓድዋ ድል ኢትዮጵያ ከሌሎች ሀገራት ጋር ያላት ግንኙነት በትብብር መንፈስ ላይ የተቃኘ እንዲሆን ያደረገ ሲሆን፤ ይህም እስከ ዛሬ ድረስ የኢትዮጵያ የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ አዕማድ ሆኖ እናገኘዋለን። ኢትዮጵያ በታላቁ የህዳሴ ግድብ ላይ ስትከተል የነበረው ፖሊሲ የዚህ ማሳያ የሚሆን ነው፡፡ የወንዙ ባለቤት ሆና ሳለች ወንዙን ብቻዬን ልጠቀም ሳይሆን በጋራ እንጠቀም ስትል ኖራለች፡፡

ኢትዮጵያ ከሀገራት ጋር በመከባበር ላይ የተመሰረተ፣ የጋራ ጥቅምን ባስጠበቀ፣ ሀገራዊ ሉዓላዊነትን ባስከበረ እና ለዜጎቿ ቅድሚያ በሚሰጥ የዲፕሎማሲ ፖሊሲ በመከተል የአድዋ ድልን ተከትሎ የመጡ የዲፕሎማሲ ትሩፋቶች ለማስቀጠል ዛሬም በትኩረት ልትሰራ ይገባል፡፡

# ፋሽን

## ዓድዋን በፋሽን

**ሙሉጌታ ብርሃኑ**

ምስጋና በዓድዋ ለተዋደቁ ጀግኖች እናት አባቶቻችን ይግባና፣ ኢትዮጵያን ነጻ አውጥተው ባያስረክቡን ኖሮ ዛሬ ላይ ሆነን የኢትዮጵያን ባህል.. የኢትዮጵያ ፋሽን እያልን ባላወራን ነበር። በጥቂቱ እየተበረዘ የሚያስቸግረን ይህ እሴታችን ዛሬ ምን አይነት ይሆን እንደነበር አስበነው እናውቃለን?፣ መቼስ ፈረጅ ፈረጅ እያሉብን መላቅጣችንንም ባሳጣን ነበር። የባህል የበኩር ልጅ የሆነው ፋሽን፣ የቅንጦት ጉዳይ እየመሰለን ንቀን ችላ ካልነው የመጀመሪያውና ትልቁ ስህተታችን የሚጀምረው እዚህ ጋር ይሆናል። ለምን? የሚል ካለ ምክንያቱን እንመልከት። የአንዲት ሀገር ሉአላዊነት ከሚለካበት ሶስት መሰረታዊ ነገሮች ፖለቲካ፣ ኢኮኖሚ እና ባህል ዋነኞቹ ናቸው። ፋሽን ደግሞ ከሁለቱ መሰረታዊ ነገሮች ጋር ቁርኝት አለው። ከኢኮኖሚና ባህል ጋር። የፋሽን ኢንዱስትሪያቸውን ያዘመኑ አገራት ያላቸውን ለአለም እያስተዋወቁና ምርታቸውን በባለቤትነት እየሸጡ ዛሬ ላይ ኢኮኖሚያቸውን ከፍ ማድረግ ችለዋል። ሌላው ደግሞ የልዩ ልዩ ባህሎች መገኛ የሆኑ እንደ ኢትዮጵያ ያሉ አገራት ባህላቸውን ለማስተዋወቅ መጀመሪያ የሚከተሉት ባህላዊ ፋሽኖቻቸውን ነው። የእኛ የፋሽን መገለጫዎች ከተቀረው አለም ለየት ባይሉና ባህላችን ከወረራ ባይድን ኖሮ ዛሬ ላይ ቱሪስቶች እዚህ ድረስ እየመጡ የሚጎበኙበት ምንም ምክንያት አይኖርም ነበር።

በዛሬ የፋሽን አምዳችን የዓድዋ ድል ካጎናፀፈን ትልቅ እድል መካከል አንዱ በሆነውና ትኩረት ባልሰጠነው የፋሽን እሴታችን ዙሪያ ይሆናል። ለዚህም ከአንዲት እንግዳ ጋር የስልክ ቃለምልልስ አድርገናል። ማርታ ሳምሶን ትባላለች፣ ከአመታት በፊት በምትኖርበት የካናዳ አገር በፋሽንና ዲዛይን ሙያ የመጀመሪያ ዲግሪዋን ተቀብላለች። በአሁኑ ሰዓትም በሀዋሳ ከተማ የራሷ የሆኑ የባህል አልባሳትን ዲዛይን በማድረግና በማዘጋጀት ለገበያ ታቀርባለች። ለባለሙያዋ ያነሳነው የመጀመሪያ ጥያቄ ከባህል ወረራ ጋር ተያይዞ በፋሽን ላይ የሚፈጠር ተፅእኖን የተመለከተ ነው።

ባለሙያዋ ለዚህ ሃሳብ ምላሽ ስትሰጥ፣ የባህል ወረራ ከፋሽን አንፃር ትርጉሙ እጅግ በጣም ሰፊ ነው ትላለች። ይህን ስታብራራም፣ ሁለት ምሳሌዎችን ታስቀምጣለች። የመጀመሪያውን ከአልባሳት አንጻር በሁለት መልኩ ልንከፍለው እንችላለን። የመጀመሪያው የእኛ ቱባ የባህል መገለጫ የሆኑ አልባሳት ያለ እኛ ፈቃድና እውቅና ሌሎች በዚያው ዲዛይንና መልክ አዘጋጅተው እንደራሳቸው በማድረግ የሚለብሱት ከሆነ የባህል ወይም የፋሽን ወረራ አካሄዱብን ማለት እንችላለን። ሁለተኛው ደግሞ የራሳችንን ወደጎን ጥለን በተለያዩ ሚዲያዎችም ሆነ መሰል መንገዶች ተመልክተን ብቻ፣ ከእኛ የባህል ስርዓት ጋር የማይሄዱ ፋሽኖችን ስናዘወትር የፋሽን ወረራ እንለዋለን። ፋሽን በባህሪው በቶሎ የሚዛመት በመሆኑ ባየናቸው ነገሮች በሙሉ አይናችንን የምንጥል ከሆነ ሳናስበው ወደዚያው እንገባና የእኛ የሆነውን እንረሳለን ስትል ታስረዳለች።

"ልዩ ልዩ የፋሽንና ባህል መገለጫዎች ባሏት እንደ ኢትዮጵያ ያለች አገር ውስጥ የባህል ወረራ ፋሽን ላይ የሚያሳድረው ተፅእኖ አሉታዊ ጎኑ እጅግ በጣም የከፋ ነው" የምትለው ማርታ፣ የባህል ወረራ ከፋሽን አኳያ የእኛ የሆነውን ነገር አስትቶ ፍላጎታችንን በመቀነስ በዘርፉ የተሰማሩ አምራቾች እየጠፉ እንዲሄዱ ያደርጋል የሚል እምነት አላት። በሌላ መልኩም አገር በቀሉን ፋሽን በሂደት ያጠፋዋል፣ባህሉም ይመናመናል ባይ ነች።

መነሻቸው ኢትዮጵያ ውስጥ የነበረ እኛ ግን የረሳናቸው በጣም ብዙ ፋሽኖች አሁን አሁን በተለያዩ የአለማችን ክፍሎች እንደ አዲስ እየታዩና በእኛ ፋሽን እነርሱ ሲታወቁበት እንመለከታለን። ባህሎቻችን ሰፊ ከመሆናቸው አንጻር ኢትዮጵያዊ ሆነን እንኳን ይህን ስንመለከት የእኛ ስለመሆኑ ፈጽሞ አናስተውለውም ወይም ደግሞ ከነ ጭራሹ አናውቀውም። ታዲያ የእኛ ነው ብለን ብንከራከር ማን ይሰማናል?። ቱሪስቶች ወደአገራችን በሚመጡበት ወቅት ከከተማው ይልቅ ወጣ ብለው ባህላዊ በሆኑ ነገሮቻችን ላይ ማተኮር የሚወዱት ለምን ድነው? በማለት ሃሳቧን በጥያቄ የምታብራራው ማርታ፣ ለዚህ ምክንያቱ ለእኛ ከእጅ ያለ ወርቅ ሆኑና ከምንም ያልቆጠርናቸውን ነገሮች በመውሰድ የራሳቸው ለማድረግ ስለሚፈልጉም ጭምር ነው ትላለች። ይህን ደግሞ በተግባርም እያየን መሆኑን በቁጭት ትናገራለች።

ማርታ የዓድዋ ጦርነት ላይ የተገኘው ድል ለባህልና ፋሽን አለም ተምሳሌት ሊሆን ይችላል የሚል እምነት አላት። ጀግኖች አባቶቻችን በደህናው ጊዜ ቀርቶ ያኔ ለጦርነቱ ከየአቅጣጫው ሲጎርፉ እንኳን የለበሱት የወታደር ልብስ አልነበረም። ለብሰው የዘመቱት ነጭ ተነፋነፍ ሱሪና በረባሶ ጫማ አልያም ባዶ እግራቸውን መሆኑ ለዚህ ማሳያ እንደሚሆን ትናገራለች። "በረባሶውን ምናልባት በወቅቱ ጫማ ስላልነበረ ነው ልንል እንችል ይሆናል። ያንን ልብስ የለበሱት ግን እነርሱ አገራቸውን የሚገልጹበትና የእነርሱ ብቻ የሆነ ባህላዊ መገለጫቸው ስለነበረ ነው። ፋሽን ትልቁ አላማው የማይታየውን የውስጥ ማንነት በሚታይ ነገር መግለጽ ነው። ልቡሱ ወኔያቸውን የሚቀሰቅስ የሞራል ስንቃቸው ነበር። እንደዚያ ለነብሳቸው ሳይሳሱ የተዋጉት ለአፈሩና ለጋራ ሸንተረሩ ብቻ ነው ካልን ሞኝነት ነው። ከዚያም በላይ እኛ ያላየናቸው ብዙ ነገሮችን አሻግረው አይተዋል። በነጻነቷ ውስጥ የራሷ ባህል፣ የራሷ ቋንቋ እንዲኖራት እንዲሁም ያሏት እሴቶች በሙሉ እንዳይወረሩና እንዳይጠፉ ነው" በማለትም ሃሳቧን ታጠናክራለች።

ፋሽን ስንል አልባሳቶቻችንን ብቻ አይደሉም። በፋሽን ውስጥ ያሉ በርካታ እሴቶች አሉን። ፋሽኖቻችን በወረራ ከጠፉ ብዙ ነገሮቻችን ከእኛ መውጣት ይጀምራሉ። ዛሬ ይህን ችላ ብለን የራሳችንን ነገሮች እየተውን በፋሽን ወረራ ውስጥ ከገባን የዓድዋንም ሚስጥር ከንቱ እናደርገዋለን ስትልም ታብራራለች።

'የፋሽን ወረራ ዘመናዊነት ነው ልንለው እንችላለን? ትውልዱስ እነዚህን ሁለት ነገሮች በምን መልኩ አስታርቆ መሄድ ይችላል?' ለባለሙያዋ የሰነዘርነው የመጨረሻ ጥያቄ ነው። የእሷም ምላሽ እንዲህ የሚል ነበር፣ "የፋሽን ወረራ በፍጹም የዘመናዊነት መገለጫ አይሆንም። ዘመናዊነትማ የራስን ጥሎ የሌላን መስረቅ አይደለም። በዘመናዊነት ውስጥ ትልቅ ስልጣኔ አለ። ይህ ስልጣኔ ደግሞ ያለንን ነገር እንድናዘምን የሌለንንም ነገር እንድንፈጥር ያደርገናል። አንድ ሰው መጽሀፍ ሲገዛ ስላየን ብቻ የተማረ ነው ልንል አንችልም፤ የተማረ ነው የምንለው መጽሀፉን ማንበብ ሲችል ነው። የሰለጡኑ ሰዎች የለበሱትን ስለለበስን ብቻ የሰለጠነ አሊያም ዘመናዊ አያስብለንም። መዘመንም የሌላውን እንደወረደ አምጥተን መከናነብ አይደለም። መዘመን የነበረውን ማሻሻልና ከጊዜው ጋር እንደሚሄድ ማድረግ እንጂ ምንም ታሪክ እንደሌለው ትውልድ የነበረውን በዜሮ አባዝቶ አንድ ብሎ መጀመር አይደለምና ዘመናዊ ነኝ ብሎ የሚያስብ ትውልድ መሰረቱን መትከል ያለበት በድሮው ላይ ነው። አባት እናቶቻችን የሄዱበት መንገድ የማይጠቅም ቢሆን ኖሮ ዛሬ ከዘመናት በኋላ ነጮቹ ባልፈለጉት ነበር። ዘመናዊነትን እየሰበኩን አሞኝተው የእጃችንን እያስለቀቁን መሆኑን ልናስተውል የግድ ነው።"

እኛም የራሳችንን ዓድዋ በድል ደግመን ታሪካችንን በቀጣዩ ትውልድ ማህደር ላይ እናስፍር! ስንል የባለሙያዋ ሃሳብ ላይ አከልንበት።

# ትዝብት/ ማረፊያ

## «ቅንነት ለዘላለም ይኑር»

**ቦጋለ አበበ**

ስለ ኢትዮጵያውያን የመረዳዳትና የመደጋገፍ አኩሪ ባህል ብዙ ተብሏል። ይህ አኩሪ ባህል "ድሮ ቀረ" እየተባለም ብዙ ጊዜ ታምቷል። በእርግጥ አሁንም ይታማል። እኔ ግን እየተሸረሸረ መጥቷል እንጂ ከቶውንም አልጠፋም ከሚሉት ወገን ነኝ። የመረዳዳት ባህላችን ጠፋ ሲሉት የሚበራ፣የለም ሲሉትም የሚጎመራ አይነት ነው። ለዚህ ደግሞ ሰሞኑን በቦረና የተከሰተው ድርቅ በሚሊዮን የሚቆጠሩ እንስሳትን ገድሎ በሰውም ላይ ጉዳት እንዳይደርስ ስጋት መፍጠሩ ከተነገረ በኋላ የታየው አስደናቂ ርብርብ ትልቅ ማሳያ ነው።

የቦረናን ሕዝብ ለመታደግ በተለያዩ ደጋግና ቅን ግለሰቦች የተጀመረው እርዳታ የማሰባሰብ ርብርብ እጅግ አስደናቂ ነው። ኢትዮጵያውያን የቱንም ያህል በፖለቲካ፣ታሪክና ሃይማኖታዊ ጉዳዮች ተወጥረን ስንነታረክ ብንከርምም የተቸገረን ለመርዳት፣የተራበን ለማጉረስ፣የተጠማንም ለማጠጣት ዛሬም ትልቅ የሞራል ልእልና እንዳልተለየን አረጋግጧል። ከዚህም በላይ ኢትዮጵያውያን ከተባበርን ምን መፍጠር እንደምንችል የጥቂት ግለሰቦች ጥረትና ተነሳሽነት ብቻ ትልቅ አቅም እንዳለን ከወሬ በዘለለ በተግባር አሳይቶናል። ጥቂት ግለሰቦች በጣት በሚቆጠሩ ቀናት እንዲህ ትልቅ አቅም ከፈጠሩ ብዙሃን ምን ሊፈጥሩ ይችላሉ? የሚል ቁጭት ግን አሳድሮብኛል። ይህም የመረዳዳት አኩሪ ባህላችን አንድ ችግር ሲገጥመን ብቻ ለምን ይሆናል? በማለት የምንረዳዳበትና የምንደጋገፍበትን ሁኔታ መለስ ብዬ እንዳጤነው አድርጎኛል።

ችግሮች ሲገጥሙን መረዳዳታችን መልካም ነው። ነገር ግን ለምን ችግር ሲገጥመን ብቻ ይሆናል?፣ ይህን የመረዳዳት አኩሪ ባህል ለምን ችግሮች ከመፈጠራቸው አስቀድመን አናደርገውም? ብለን ራሳችንን እንጠይቅ።

ዘግይቶም ቢሆን በችግር ጊዜ የመረዳዳት ባህሉ ካለን አላሰብንበት ይሆናል እንጂ ችግሮች ከመፈጠራቸው በፊት መረዳዳት፣መደጋገፍ አይከብ ደንም። ብዙ ጊዜ እንደምናስተውለው ግን ሰው በቁሙ እያለ ከመርዳትና ከመደገፍ ይልቅ ከወደቀ በኋላ መረባረብ ይቀናናል።

አንድ ሰው በችግር ሲንከላወስ ፈጥነን ችግሩን በመጋራትና ቀዳዳውን ባለን አቅም ለመድፈን ከመጣር ይልቅ ችግሩ አደባባይ እስኪወጣ የመጠበቅ ዝንባሌ እንዳለን መሸሸግ አይቻልም። እርግጥ ነው ሰው ከመቸገሩም አስቀድመው የሚችሉትን ብቻ አይደለም የማይችሉትንም ለማድረግ የሚጥሩ ብዙ ደጋጎች አሉ። ከነዚህ ደጋጎች ይልቅ ግን በማወቅም ይሁን ባለማወቅ ለሰዎች ችግር ዳተኛ የምንሆን እንልቃለን።

አሁን በቦረና በተከሰተው ድርቅ ብቻ ሳይሆን በጦርነትና ሌሎች ችግሮች በገጠሙን ወቅት የመረዳዳት ባህላችን ምን ያህል አስደናቂ እንደሆነ ደግመን ደጋግመን ታዝበናል። ይህ መልካም ነው። በነዚህ ችግሮች ወቅት ለመረዳዳት ያሳየነው ተነሳሽነትና የፈጠርነው አቅም ግን ብዙ ርቀን እንድናስብ ያደርገናል።

ለምሳሌ ያህል አሁን ለቦረናው ድርቅ በጥቂት ግለሰቦች በጣም በአጭር ቀን ትልቅ ነገር መፍጠር ከቻልን እንደ ቦረና ላሉ አካባቢዎች ችግሮች ባይፈጠሩም ቀደም ብለን ውሃ ማቆር የሚቻልበትን ነገር ተረባርበን መፍጠር ብንችል ብዙ ታሪኮችን መቀየር እንችላለን። ትምህርት ቤት ለሌላቸው ትምህርት ቤት፣ ሆስፒታል ለሌላቸው ሆስፒታል ወዘተ መፍጠር ብንችል ስንት ሸክም ማቅለል እንደሚቻል ማሰብ ነው። እኛ ጋር ያለው ልምድ ግን ተቃራኒ ነው፣ ትምህርት ቤት ወይም ሆስፒታል የምንገነባው ወይ በጦርነት አልያም በሌላ ምክንያት ሲፈርሱ ነው። በእርግጥ አንዳንድ ችግሮችን ለመቅረፍ ቀድመን የማንገኘው ከመረጃ ማጣት ሊሆን ይችላል። ለዚህም ይመስላል አንድን ማህበረሰብ ለመርዳት የግድ ችግሮች ወደ ሚዲያ እስኪወጡ የምንጠብቀው።

አንዳንዶቻችን ደግሞ ቅን ልቦናና አቅም ኖሮን ለችግሮች ቀድመን ለመድረስ የሚያነሳሳን እንፈልጋለን። በእርግጥ የሚያነሳሳን ካገኘን እንኳን ለችግሮች ለመንግስት የልማት ጥሪዎችም እጃችንን ወደ ኪሳችን ለመስደድ ወደ ኋላ እንደማንል ብዙ ማሳያዎችን መደርደር ይቻላል። በተለይም አገራዊ ለሆኑ ግዙፍ የልማት ፕሮጀክቶች እጃችንን ለመዘርጋት በቅርብ አመታት ውስጥ እንኳን ታሪክ የማይረሳው አሻራ አኑረናል። የታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ለዚህ አንድ ማሳያ ሊሆን ይችላል። በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ አማካኝነት ገበታ ለአገር በሚል ተነሳሽነት በአንድ ምሽት የእራት ፕሮግራም ምን መስራት እንደተቻለም እናውቃለን።

እነዚህ የመንግስት ሰፋፊ ፕሮግራሞች ሊሆኑ ይችላሉና ወደ ጎን እንተዋቸው። ታዋቂ ሰዎችና ተፅእኖ ፈጣሪዎች ከዚህ ያልተናነሱ በርካታ የማህበረሰብ ችግሮችን ከተፈጠሩም በኋላ ይሁን ከመፈጠራቸውም በፊት መቅረፍ የሚችሉበት ትልቅ አቅም አላቸው። ችግሩ ማን ተነሳሽነቱን ይውሰድ ነው። ተነሳሽነቱን የሚወስድ ካለ የብዙዎችን ተራራ የሚያህል ችግር በጥቂት ቀናት መናድ ይቻላል። ለአብነት ያህል መቄዶኒያን እንመልከት፣ መቄዶንያ ዛሬ ላይ በሺዎች የሚቆጠሩ የበርካታ ዜጎች መከታ የሆነው አንድ ሰው በወሰደው ተነሳሽነት ነው። ምናልባትም ቢኒያም በብሩህና ቅን ልቦናው ይህን ነገር ባይጀምር በርካቶች የእሱን አርአያ ተከትለው ለተቀደሰው ተግባር ባልተረባረቡ ነበር። ልክ እንደ መቄዶንያ ሁሉ የልብና የኩላሊት ሕመምተኞችን ለመርዳት የተደረገው ጥረትም የብዙዎችን ሸክም እንዳቀለለ መናገር ለቀባሪው ማርዳት ይሆናል።

ከነዚህ በጎ ተግባራት የምንረዳው ነገር ቀድመን የማሰብ እንጂ እጃችንን የመዘርጋት ችግር እንደሌለብን ነው። ቀድመን የአንድ ሰውንም ይሁን የአንድን ማህበረሰብ ችግሮች ማወቅና ለመፍትሄው መረባረብ የሚጀምረው ደግሞ እያንዳንዳችን በቅርባችን ከምናየው ወይም ከሚገጥመን ነገር ነው። መቼም አይነቱ ይለያይ እንጂ የተቸገረ ሰው በዙሪያችን የለም የምንልበት ሁኔታ ላይ እንደማንገኝ ልቦናችን ያውቀዋል። ስለዚህ ይህን የመረዳዳት ባህላችንን በተሻለ ሁኔታ ለማጎልበት ቅድሚያ ከራሳችን እንጀምር። ቅንነት ለዘላለም ይኑር!!

## ነፃ ሃሳብ

# ዓድዋ ዛሬ ነው ዓድዋ ትናንት....

ክብረአብ በላቸው

ወርሃ የካቲት በኢትዮጵያ ታሪክ ጉልህ ሥፍራ አለው፡፡ የኢትዮጵያውን የነፃነት ተጋድሎ ታሪክ በደም እና በአጥንት አሻራ የተፃፈበት ነው፤ ከእነዚህ አበይት የታሪክ ክስተቶች አንዱ የዓድዋ ድል ነው፡፡ የዓድዋ ድል የኢትዮጵያ ብሔራዊ ክብር ማኅተም፤ የጥቁር ህዝቦች የነፃነት ተጋድሎ ቀንዲል ነው፡፡ የመላው ዓለም ተፈጥሯዊ ግብር እና ሰብአዊ ክብር የታደሰው፤ በእውነት በፍትህ እና በህልውና ላይ የተቃጣው ጥቃት ድባቅ የተመታው በዓድዋ የጥቁር ህዝቦች ታላቅ ድል ነው፡፡

የካቲት 23 ቀን 1888 ዓ.ም በግሩም ስነስርዓት የተደራጀ ግዙፍ የኢትዮጵያ ሠራዊት የማይታሰበውን ፈጽሟል። ወራሪው የጣሊያን ኃይል ላይ ድባቅ በመምታት ድልን ተቀዳጅቷል። ስግብግብነት በተጠናወተው የአውሮፓውያን መስፋፋት፤ ኢትዮጵያ ነጻነቷን በተሳካ መልኩ አስጠብቃለች ሲሉ ያነሳሉ፤ ዝነኛው የታሪክ ፕሮፌሰር ራይሞንድ ዮናስ፡- «የዓድዋ ጦርነት፤ በዘመነ ቅርምት የአፍሪቃ ድል» በተሰኘው መጽሐፋቸው።

ሃያ ዘጠኝ ሺህ ፈረሰኞችን ጨምሮ ከመቶ ሺህ እስከ መቶ ሃያ ሺህ የሚገመት አንድ ሺህ ኪሎ ሜትር በባዶ እግሩ የተጓዘ የኢትዮጵያ የገበሬ ሠራዊት፤ በወታደራዊ አካዳሚ የሠለጠነውን የአውሮፓ ወራሪ ጦር የካቲት 23 ማለዳ አሥራ አንድ ሰዓት ግድም ገጥሞ ከረፋዱ አራት ሰዓት ላይ ማሸነፉን አረጋግጧል ይለናል የታሪክ ተመራማሪው ጆርጅ በርክሌይ፡፡ የዓድዋ ጦርነትና ዳግማዊ አፄ ምኒሊክ በተሰኘና ዳኘው ኃይለሥላሴ ወደ አማርኛ በተረጎሙት መጽሐፍ ላይ፤ የኢትዮጵያ ገበሬ ሠራዊት ፈረሱ ላይ ሆኖ የጋሻውን እምብርት መሬት ላይ እያጠቀሰ ጐራዴውን አየር ውስጥ እየቀዘፈ በተቆጣና በቆረጠ መንፈሥ በጀግንነት ተዋግቷል፡፡

ጦርነቱ በተጀመረ ከአምስት ሰዓት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ሃምሣ ስድስቱም የኢጣሊያ መድፎች ሙሉ ለሙሉ ተማርከዋል፡፡ የቅኝ ገዢውን ወራሪ ሠራዊት ከመሩት ጀኔራሎች ጄኔራል አልቤርቶኒ ሲማረክ የሠራዊቱ ዋና አዛዥ ጄኔራል ባራቴሪ ከጥቂት አጃቢዎቹና በሽንፈት ከተበታተኑ የጣሊያን ወታደሮች ጋር ሸሽቷል፡፡

በዚህ ድብልቅልቅ ያለ ውጊያ ከሃምሣ ስድስቱ የጣሊያን መድፎች በተጨማሪ ብዙ ሺህ ቀላልና ከባድ መትረየሶች እንዲሁም የነፍስ ወከፍ ጠመንጃዎች በአሥር ሺዎችና በመቶ ሺዎች ከሚቆጠሩ መሰል ጥይቶቻቸው ጋር ተማርከዋል፡፡ በአጠቃላይ ምርኮው ወደ አዲስ አበባ የተጓጓዘው በአምስት መቶ አጋስሶች ተጭኖ ነው፡፡

ታላቁ የጥቁር ህዝቦች ድል የዓድዋ ድል በመላው ዓለም ፖለቲካ ላይ ከፍተኛና ዋነኛ ለውጦች አምጥቷል፡፡ የእንግሊዝ ጋዜጦች በዓድዋ ድል ማግስት የዓለም ታሪክ ተገለበጠ ታላቅ የትውልድ ኃይል በአፍሪካ ተቀሰቀሰ ... ብለው ፃፉ፡፡ ዘመናዊት ኢትዮጵያን የፈጠሩ የተባሉት ዳግማዊ አፄ ምኒልክ በሌሉበት እና በአካል ባልተገኙበት የነፃነት ተጋድሎ መሪዎች ጉባኤ የአፍሪካ ብሎም የመላው ዓለም ጥቁር ህዝቦች የነፃነት ተጋድሎ መሪ ተደርገው ተመረጡ፡፡

ኢትዮጵያ በዓድዋ ጦርነት ወቅት በዋናው የጦር ግንባር ገጥማ በፍልሚያ ድል ማድረግ ብቻ ሳይሆን፤ በአጠቃላይ በአራት መስክ ሠለጠነች በምትባለው አውሮፓዊት ሀገር ጣሊያን ላይ ድል ተቀዳጅታለች፡፡ ይኸውም፡- በጦርነት እና በወታደራዊ መረጃ (Military Security intellegence) ፤ በዲፕሎማሲና በፖለቲካ ጥበብ ነው፡፡

ለጦርነቱ መጀመር መነሻ የሆነው የውጫሌ ውል ነው፡፡ የውጫሌ ውል አንቀጽ አሥራ ሰባት የጣሊያንኛው፡- ኢትዮጵያ ከአውሮፓ መንግሥታት ጋር ማድረግ የምትፈልገውን ግንኙነት በጣሊያን መንግስት በኩል ማድረግ አለባት ሲል፤ አማርኛው ደግሞ ኢትዮጵያ ከአውሮፓ መንግሥታት ጋር ማድረግ የምትፈልገውን ግንኙነት በጣሊያን መንግሥት በኩል ማድረግ ትችላለች ይላል፡፡

> **ዛሬም ድረስ በኩራት የሚነሳው ያለፈው የአባቶች የትኛውም ታሪክ የአሁን ዘመን ትውልድ አስተዋፅኦ የለበትም፡፡ የአሁኑ ትውልድ ራሱ የሚነሳበትን የሚያኮራ ታሪክ መፃፍ አለበት፡፡ ይህ ትውልድ የእነዛን ዘመን የኢትዮጵያ አባቶችን ውለታ የሚከፍለው፤ የኢትዮጵያን አንድነት በማስጠበቅ እና ኢትዮጵያን በማበልፀግ መሆን አለበት**

የአማርኛው የኢትዮጵያን ሉአላዊነትና ልዕልና ያከብራል፤ የጣሊያንኛው የኢትዮጵያን ሉአላዊነትና ልዕልና መድፈር ብቻ ሳይሆን ብሔራዊ ክብሯንና ጥቅሟን ይነካል፡፡ ይሄን የተገነዘቡት የኢትዮጵያ መሪዎች የውሉ አንቀጽ አሥራ ሰባት የጣሊያንኛ ትርጓሜ የኢትዮጵያን ክብርና ጥቅም በማይነካና ሉአላዊነቷን በሚያከብር መልኩ እንዲስተካከል በተደጋጋሚ ወተወቱ፡፡ መወትወቱ ውጤት ሳያመጣ ሲቀር፤ ጣይቱ ለምኒልክ ‹‹መዘግየት አደገኛ ነው›› አሉ፤ ስለዚህ ጉዞ ወደ ወሳኙ ጦርነት ማድረግ የግድ ሆነ፡፡

የኢትዮጵያን ሀገራዊ ክብርና ጥቅም ህልውናና ልዕልና ቢሆን በውድ፤ ካልሆነ ደግሞ ሳይወድ በግድ ማስከበርና ማስጠበቅ የመንግሥት ዋነኛ ግዴታና ኃላፊነት ነው፡፡ ስለዚህ ኢትዮጵያውን ጦር እንግተም በወታደራዊ መረጃ (Military Security intellegence) ብልጫ፤ ሠለጠነ የተባለውን የአውሮፓ ኃይል አሸንፈው ጣሊያኖች ባልፈለጉት ቦታና ባልመረጡት ጊዜ ወደ ጦርነት እንዲገቡ አደረጉ፡፡

በወታደራዊ ሣይንስ (Military Science) አገባብ ለጦርነት የተንቀሳቀሰ አንድ ሠራዊት ወዲያውኑ ወደ ጦር ግንባር መግባት አለበት፤ ይሄ አንድ ነጥብ ነው፡፡ ሌላው ነጥብ አንድ ለግዳጅ የተንቀሳቀሰ ሠራዊት ለመሰናዶም ሆነ ለመከላከል ውጊያ በአንድ የመከላከያ ወረዳ ከሠፈረ በዚያ መከላከያ ወረዳ ከስድስት ወራት በላይ መቆየት የለበትም፡፡ በአንድ ቦታ ላይ ከስድስት ወራት በላይ ከቆየ ሊደርስ የሚችል የወታደራዊ ሥነልቦና ጉዳት ከፍተኛ ነው፡፡ የመሸገበትን የመከላከያ ወረዳ እየተለመማመደ ሲሄድ ስለሚዘናጋና የውጊያ ስሜቱ እየቀነሰ ወይም እየቀዘቀዘ ስለሚመጣ አሸናፊ ሆኖ ጦርነትን ማጠናቀቅ ከባድ ነው። ከሎጂስቲክ አኳያ የውጊያ ዝግጁነቱም አደጋ ላይ ስለሚወድቅ በሌላ አነጋገር ስንቅ እየጨረሰ ስለሚሄድ በእነዚህ ምክንያቶች በአፋጣኝ ወደ ጦርነት መግባት ለሠራዊቱ ድል አድራጊነት ትልቅ ጥቅም ነበረው።

በዛን ጊዜ ኢትዮጵያ ሠላም ሲሆን፤ ገበሬ በጦርነት ጊዜ ጀግና ተዋጊ እንጂ ዘመናዊ ወታደራዊ መሠረት Professional Army አልነበራትም። በዚያ ዘመን ለአንድ መቶ ሃያ ሺህ ሠራዊት የሎጂስቲክ አገልግሎት እየሰጡ ለረጅም ጊዜ መቆየት አስቸጋሪ ነበር፡፡ ስለዚህ የጀግንነት ግለት ሳይበርድ የሎጂስቲክ (ስንቅ ትጥቅ መድሃኒት) አቅም ሳይዳከም በፍጥነት ጦር መግጠም እጅግ አስፈላጊ ሆነ፡፡ የኢትዮጵያ ሠራዊት ጦርነቱን ፈጥኖ ለመግጠም ጣሊያኖች ወደ ዓድዋ መምጣት አለባቸው፤ ወይም ደግሞ የእኛ ሠራዊት ጣሊያኖች ወደመሸጉበት የኤርትራ ከፍተኛ ቦታዎች መሄድ አለበት፡፡ ከነዚህ ሁለት ሁኔታዎች የአንደኛው መሆን የግድ ነበር። ወደ ጣሊያኖች መሄድ ከፖለቲካ ሁኔታዎች ባሻገር ከወታደራዊ ሳይንስ አንፃር የሚመረጥ አይደለም።

በወታደራዊ ሣይንስ ደግሞ ወታደራዊ መረጃ ለወታደራዊ ግዳጅ አፈፃፀም ዋነኛና ወሣኝ ጠቀሜታ አለው፡፡ በዓለም ላይ ከተደረጉ አብዛኞቹ ጦርነቶችም ድል አድራጊዎች ድላቸውን የሚቀናጁት የወታደራዊ መረጃ ብልጫ የነበራቸውና ፍትህና እውነትን ፖለቲካዊ መሠረት ያደረጉት ናቸው፡፡ ኢትዮጵያ ሁለቱም ነበራት፤ ኢትዮጵያዊያን ዓላማቸው የሀገራቸውን ጥቅምና ክብር እንዲሁም ህልውና እና ልዕልና ማስከበር፤ ነፃነታቻውን ማስጠበቅ ነበር፡፡ ይህ ደግሞ የፍትህና የእውነት ጥያቄ ነው፡፡ ኢትዮጵያ በረጅም ዘመን ታሪኳ ከውጪ ወራሪዎች ጋር ባደረገቻቸው ጦርነቶች ሁሉ፤ እውነትና ፍትህን መሠረት አድርጋለች። ስለዚህ ድልን ተቀናጅታለች። በዓለም አደባባይ ደምቃ ታይታለች፡፡ ይህንን ታሪክ ተክለፃዲቅ መኩሪያን የመሳሰሉ ኢትዮጵያውያን የታሪክ ተመራማሪዎችና የውጪ ሀገር ዜግነት ያላቸው ፀሃፊያንና ተመራማሪዎች በተለያዩ መጻሕፍቶቻቸው ይሄንን እውነት ጽፈውታል፡፡

ድሉን ተከትሎ የድሉን ትርጉም ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ለመጀመሪያ ጊዜ የተከበረው በሰባተኛ ዓመቱ በ1895 ዓ.ም (እ.ኤ.አ በ1903) አዲስ አበባ አሁን ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን ያለበት ሥፍራ ምኒልክ አደባባይ ላይ ነው። ዲፕሎማቶችና የውጭ ሀገር መንግሥታት ተወካዮች አርበኞች የመንግስት ባለሥልጣናት በድል በዓሉ ላይ እየተገኙ ሲከበር መቆየቱን ጳውሎስ ኞኞ የኢጣሊያና የኢትዮጵያ ጦርነት በተሰኘ መጽሐፉ ላይ ጽፎአል፡፡ እንዲሁም ከዛ ጊዜ ጀምሮ የድል በዓሉ በተለያዩ ኩነቶች እየተዘከረ ዛሬ ላይ ተደርሷል፡፡ ዘንድሮም 127ኛው የድል በዓሉ በድምቀት ይዘከራል፡፡

አከባበሩም ኢትዮጵያውያን ነጻ የወጣንበት ብለው ሳይሆን በኩራት የድል ቀናችን እያሉ በልዩ ሁኔታ የሚያከብሩት ታላቅ ቀን ነው። የዓድዋ ድል ኢትዮጵያውያን ከጥግ እስከ ጥግ ቀፎው እንደተነካበት ንብ ተምመው በአንድ ጥላ ስር እንዲሰባሰቡ ያደረገ ታሪካዊ ክስተት በመሆኑ የኢትዮጵያውያንን ትብብር እና አንድነት ከማሳየቱም በላይ ለመላው የጥቁር ህዝብ የነፃነት ምልክት መሆናችንን ማሳያ ነው፡፡ ታድያ ዛሬ ላይ የአሁን ትውልድ የጋራ ታሪክ ያለን ህዝቦች መሆናችንን አውቆ፤ቀደምት አባቶቻችን በጊዜው በተለያየ ምክንያት የነበሩ ልዩነቶችን እና አለመግባባቶችን ወደ ጎን በመተው ባሪያ አድርጎ በቅኝ ግዛት ለመግዛት የመጠን ወራሪ ሀይል እንዴት በአንድነት ድል ማድረግ እንደቻሉ በእውን ሊገነዘበው ይገባል፡፡

በእርግጥ ኢትዮጵያውያን የተለያየ ባህል እና ቋንቋ ያለን ህዝቦች ነን፡፡ ብዝሃነትን ውበት አድርገን በመቀበል አንድ አድርጋ በምታቅፈን ኢትዮጵያ ጥላ ስር ተሰበሰበን እንደ ቀደምት አባቶች ይህ ትውልድም ዓድዋን ማክበር ብቻ ሳይሆን፤ ኢትዮጵያ ልትረታው የሚገባውን መጥፎ ሰንኮፍ ድህነት እና ኋላቀርነትን መንግሎ መጣል አለበት፡፡

ዛሬም ድረስ በኩራት የሚነሳው ያለፈው የአባቶች የትኛውም ታሪክ የአሁን ዘመን ትውልድ አስተዋፅኦ የለበትም፡፡ የአሁኑ ትውልድ ራሱ የሚነሳበትን የሚያኮራ ታሪክ መፃፍ አለበት፡፡ ይህ ትውልድ የእነዛን ዘመን የኢትዮጵያ አባቶችን ውለታ የሚከፍለው፤ የኢትዮጵያን አንድነት በማስጠበቅ እና ኢትዮጵያን በማበልፀግ መሆን አለበት ባይ ነኝ። ሰላም!

ኢኮኖሚ

# ግብርና

# ድርቅ በተከሰተባቸው አካባቢዎች የዝናብ ውሃን ለመያዝ እየተደረገ ያለ ዝግጅት

ስምስም መንግሥቱ

የቦረና አርብቶ አደር ለእለት ጉሩሱና ልብሱ፣ ለሰርግ ጥሎሹ የሚያውለው፤ የሁሉ ነገሩ መገለጫውና መመኪያው የሆነውን ከብቱ አይኑ እያየ እየሞተበት ነው፡፡ ኢትዮጵያ በቁም እንስሳት ሀብት ስሟ ተጠቃሽ እንዲሆን አስተዋጽኦ ካበረከቱት አካባቢዎች አንዱም ይኸው የቦረና አካባቢ መሆኑ ይታወቃል፡፡

ቦረናና አካባቢው በወሳኝ የዝናብ ወቅቶች ዝናብ ካጣ ሶስት አመታት አለፈ፡፡ ድርቁ ተባብሶ የአካባቢውን ማህበረሰብ ከብቱን ሸጦና ለውጦ ኑሮውን የሚመራውን የቦረና ህዝብ ለእርዳታ ጠባቂነት ዳርጎታል፡፡

በኦሮሚያ ክልል ቦረና ዞን በተከሰተው ድርቅ ከ807ሺ ያላነሰ ህዝብ እርዳታ እንደሚያስፈልገውና ከነዚህ ውስጥ ደግሞ 167ሺ የሚሆኑት አስቸኳይና ተከታታይ ድጋፍ የሚፈልጉ መሆናቸውን የቦረና ዞን ዋና አስተዳዳሪ አቶ ጀርሶ ቦሩ ሰሞኑን ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ መግለጻቸው ይታወሳል፡፡ ዋና አስተዳዳሪው በድርቁ የተነሳ ከሁለት ሚሊዮን በላይ ከብቶች ማለቃቸውንም ጠቁመዋል፡፡

በዞኑ በአሁኑ ወቅት የሰው ሕይወት የማትረፍ ሥራ እየተካሄደ ይገኛል፡፡ መንግሥት፣ የተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎች፣ ማህበራት፣ አርቲስቶች፣ ተቋማትና በተለያየ ሙያ ውስጥ የሚገኙ ለቦረና ማህበረሰብ ለመድረስ እየተረባረቡ ይገኛሉ፡፡ ርብርቡ ጥሩ ነው፤ ከዚህም በላቀ መልኩ መፈጸም ይኖርበታል፤ ይህ ግን ጊዜያዊ መፍትሄ ነው፡፡ አርብቶ አደሩ ለእንስሳቱ መኖ፣ ከፊል አርብቶ አደሩም የእርሻ ሥራውን ለማከናወን የሚያስችለው ዘላቂ መፍትሄ ያስፈልጋል፡፡

አሁን የበልግ ወቅት ነው፡፡ በዚህ ወቅት ደግሞ ዝናብ ከሚጠበቅባቸው የሀገሪቱ አካባቢዎች ቦረና አንዱ ነው፡፡ ጠብ የምትለውን ዝናብ ይዞ ለሚፈለገው ልማት በማዋል እንስሳቱንና ሰውን ለመታደግ ዝግጅት ማድረግ ይጠበቃል፡፡

በበልግና ቀጣይ የክረምት ወቅቶች ላይ የሚጠበቀውን ዝናብ በመያዝ በድርቅ የተጎዱ አካባቢዎችን ለመታደግ እየተከናወነ ስላለው የቅድመ ዝግጅት ሥራ እንዲሁም ስለወቅታዊው የዝናብ ሁኔታ መረጃ የኦሮሚያ ክልል የመስኖና ቆላማ አርብቶ አደሮች ቢሮ ኃላፊ ኢኒጅነር ግርማ ረጋሣ እንደሚናገሩት፤ ቢሮው በዋናነት የውሃ አቅርቦት ላይ ይሰራል፡፡ እንደ አንድ መፍትሄ የተያዘውም በመደበኛነት የሚጥለውን ዝናብ ጨምሮ በጎርፍና በተለያየ መንገድ አልፎ የሚሄደውን ውሃ መያዝ ነው። ለዚህም የግድብ ሥራ በፕሮጀክቶች ተቀርጾው እየተከናወኑ ይገኛሉ፡፡ በዝናብ እጥረቱ ምክንያት የደረቁ አነስተኛ ወንዞችም ወደ ሌላ አቅጣጫ እንዳይሄዱ ተጨማሪ ሥራ ተሰርቷል፡፡

በዚህ መልኩ በተለይም ዝናብ አጠር በሆኑ እንደ ቦረና ባሉ የአርብቶ አደር አካባቢዎች በልዩ ትኩረት የሚከናወኑ ሥራዎች ተጠናክረዋል፡፡ በዚህ መንገድ የተጠራቀመው ውሃ አርብቶ አደሩ ለከብቶቹ የሚውል መኖ እንዲያለማ፣ ከፊል አርብቶ አደሩም የእርሻ ሥራውን እንዲያከናውንና ለመጠጥ አገልግሎትም እንዲጠቀም ያስችላል፡፡

እንደ ኢንጂነር ግርማ ማብራሪያ፤ የፕሮጀክት ሥራው ከአምና ጀምሮ እየተከናወነ ሲሆን፣እስካሁን በተሰራው ሥራም ውሃ መያዝ የሚችሉ 12 ፕሮጀክቶች ተጠናቅቀው ዝግጁ ሆነዋል፡፡ በአጣዳፊ ሁኔታ ሥራ በሚያስፈልጋቸው አካባቢዎች ደግሞ ጥልቅ የውሃ ጉድጓድ በመቆፈር ለችግሩ መፍትሄ ለመስጠት ጥረት እየተደረገ ነው፡፡ እስካሁን የተከናወኑት ሥራዎች ለእንስሳት መኖ እና ለግብርና ሥራ እንዲሁም ለመጠጥ የሚውል ውሃ ለማግኘት ምቹ ሁኔታ መፍጠር አስችለዋል፡፡

በተለያየ አቅጣጫ የሚገኘውን ውሃ ለመያዝ እንዲያስችሉ ተብለው የተሰሩት ግድቦች 16 ሜትር ከፍታና ሰፋ ያለ ርዝመት ያላቸውና በሚሊዮን ሜትሪክ ኪዩቢክ የሚገመት ውሃ የመያዝ አቅም ያላቸው ናቸው። እነዚህ የቅድመ ዝግጅት የግድብ ፕሮጀክት ሥራዎች ቦረና ላይ ትኩረት ያደረጉ ቢሆኑም፣ ስራው በተለይ በቆላማውና አርብቶ አደር የሚበዛባቸውን አካባቢዎች (ምሥራቅና ምእራብ ባሌ፣ ሐረርጌ) አካቶ ነው እየተከናወነ የሚገኘው፡፡

> **በተለያየ አቅጣጫ የሚገኘውን ውሃ ለመያዝ እንዲያስችሉ ተብለው የተሰሩት ግድቦች 16 ሜትር ከፍታና ሰፋ ያለ ርዝመትና በሚሊዮን ሜትሪክ ኪዩቢክ የሚገመት ውሃ የመያዝ አቅም ያላቸው ናቸው፡፡ እነዚህ የቅድመ ዝግጅት የግድብ ፕሮጀክት ሥራዎች ቦረና ላይ ትኩረት ያደረጉ ቢሆኑም፤ ስራው በተለይ በቆላማውና አርብቶ አደር የሚበዛባቸውን አካባቢዎች (ምሥራቅና ምእራብ ባሌ፣ ሐረርጌ) አካቶ ነው እየተከናወነ የሚገኘው**

የጉድጓድ ቁፋሮ ሥራን በተመለከተ ኢንጅነር ግርማ ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት ምላሽ፤ የጉድጓድ ውሃ ስራው ችግሩ የከፋባቸው በአካባቢያቸው በጉድጓድ ውሃ እንዲጠቀሙ የተከናወነ መጠነኛ ሥራ መሆኑን ጠቅሰው፣ ስራውን በሁሉም አካባቢዎች በስፋት ለማከናወን ከፍተኛ የገንዘብ አቅም ይጠይቃል ብለዋል፡፡

በዘላቂነት የአካባቢውን የውሃ ችግር በመፍታት መፍትሄ ያስገኛል ተብሎ የሚጠበቀው ግን በፌዴራል መንግሥት የሚመራውና «ቦረና ኔት ወርክ» በሚል በአፍሪካ ልማት ባንክ የገንዘብ ድጋፍ እየተከናወነ የሚገኘው የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክት መሆኑን ጠቅሰው፣ ፕሮጀክቱ ግዙፍ እንደሆነና ሥራውም ከተጀመረ መቆየቱን ጠቁመዋል፡፡

የግድብ ሥራ ቅድመ ዝግጅቱ በበልግና በመደበኛ የሚጠበቀውን የዝናብ ውሃ ለመያዝ በመሆኑ የአየር ትንበያ መረጃን መከታተልና መረጃው ከሚሰጠው አካል ጋር የተናበበ ሥራ መሥራት ይገባል፡፡ በዚህ ረገድ እየተደረገ ስላለው ጥረትም ኢንጅነር ግርማ እንደሚገልጹት፤ከኢትዮጵያ ብሄራዊ ሚትዮሮሎጂ ኢንስቲትዩት ጋር ያለው የእለት ተእለት ግንኙነት እንደተጠበቀ ሆኖ፤አፋጣኝ ምላሽ የሚሰጥ «ኢመርጀንሲ ሪስፖንስ» በሚል የቅድመ ማስጠንቀቂያ ዳታዎች (መረጃዎች) ተሰብስበው ለፌዴራል መንግስት ጭምር የሚላክበት አሰራር በቢሮው በኩል ተዘርግቷል ብለዋል፡፡ ባለው ተሞክሮ ከየካቲት አጋማሽ ጀምሮ ቦረና ላይ ዝናብ ይጥላል፤አሁንም እንደሚጥል ትንበያዎች ያሳያሉ፤እየተጠበቀ ነው ይላሉ፡፡

ያለፈውን ክስተትና ወደፊት የሚጠበቀውን የዝናብ ሁኔታ በተመለከተ በኢትዮጵያ ብሄራዊ ሚትዮሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዮሮሎጂ ትንበያና ቅድመ ማስጠንቀቂያ መሪ ሥራ አስፈጻሚ ዶክተር አሳምነው ተሾመ እንዳብራሩት፤ ከነበረው የደመና ሽፋንና ክምችት በመነሳት አብዛኞቹ የሀገሪቱ አካባቢዎች ከቀላል እስከ መጠነኛ ዝናብ አግኝተዋል፡፡ በጥቂት የሀገሪቱ አካባቢዎች ደግሞ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ለአብነትም ያለፈው ቅዳሜ ሳምንት በድሬዳዋ 33፣ በሊሙ ገነት 32፣ በጅንካ 30 በጅማ 27 ሚሊ ሊትር የዝናብ መጠን በ24 ሰዓታት ጊዜ ውስጥ ተመዝግቧል፡፡ በተለይም በምሥራቅ አማራ፣ በመካከለኛውና የምሥራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቧል፡፡

ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆነው የሀገሪቱ አካባቢዎች በምሥራቅ አማራ፣ በመካከለኛውና በምሥራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ባለፉት ቀናት በተለያየ መጠን የጣለው ዝናብ የበልግ የግብርና ሥራ እንቅስቃሴን ለማከናወን ምቹ ሁኔታን እንደሚፈጥርም ነው የጠቆሙት፡፡ በደቡብ አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍል ከመጋቢት አጋማሽ በኋላ ጥሩ የሆነ የተጠናከረ የደመና ሽፋንና በተለያየ መጠን ዝናብ እንደሚኖር የትንበያ መረጃዎች እንደሚያሳዩም ነው የጠቆሙት፡፡

የኢትዮጵያ ብሄራዊ ሚትዮሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚሰጠውን መረጃ መሠረት በማድረግ የሚኖረውን የአየር እርጥበትና ዝናብ ወደ ጥሩ አጋጣሚ በመቀየር በአግባቡ ጥቅም ላይ ለማዋል ዝግጁ መሆን ያስፈልጋል፡፡

በደቡብ ኦሮሚያ በቦረናና በሌሎችም አካባቢዎች በልግ ዋና የዝናብ ወቅታቸው በጋ ደግሞ ሁለተኛው የዝናብ ወቅታቸው እንደሆነ የጠቆሙት ዶክተር አሳምነው፤ በአካባቢዎቹ ላይ የተከሰተው ድርቅ በ2013 እና በ2014 የበጋና የበልግ እንዲሁም በ2015 የበጋ ወቅቶች የነበረው ከመደበኛ በታች የሆነ የዝናብ ስርጭት ያመጣው ተጽእኖ እንደሆነ አስረድተዋል፡፡

ከ2013 የበጋ ወቅት ጀምሮ በአካባቢዎቹ ከመደበኛ በታች የሆነ የዝናብ ስርጭት እንደሚኖር በወቅቱ የትንበያ መረጃ በኢንስቲትዩቱ እንዲደርስ መደረጉንም ዶክተር አሳምነው አስታውሰዋል፡፡ ችግሩን የሚያስከትለው ወቅያኖስ ላይ ያለ የአየር ክስተት እንደሆነ ጠቅሰው፣ የባህር ወለል መቀዝቀዝና መሞቅ በኢትዮጵያ በበጋ፣ በበልግና በክረምት አሉታዊና አዎንታዊ ተጽእኖ ሊያሳድር እንደቻለም ጠቁመዋል፡፡ በየጊዜው የሚተነተነው መረጃ የሚያሳየው በአጠቃላይ ከአየር መዋዠቅ ጋር በተያያዘ በበልግ የሚጠበቅ ዝናብ እየተዳከመና እየቀነሰ መሆኑንም ገልጸዋል፡፡

እንደ ዶክተር አሳምነው ገለጻ፤ በኢትዮጵያ የዝናብ ወቅቶች ክረምት፣ በልግና በጋ ሲሆኑ፣ እያንዳንዳቸው አራት ወራት ጊዜያቶች አሏቸው፡፡ በተለይ አመታዊ የዝናብ መጠኑ እስከ 85 በመቶ የሚደርሰው ከሰኔ እስከ መስከረም ባለው የክረምት ወቅት ነው፡፡ በዚሁ መሰረት አብዛኛው የሀገሪቱ አካባቢዎች የክረምት ዝናብ ተጠቃሚዎች ሲሆኑ፣ የደቡብ አጋማሽ አካባቢዎች ደግሞ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አይደሉም፡፡ ከእነዚህ አካባቢዎችም በደቡብ ኦሮሚያ ቆላማ አካባቢ የሚገኙት ጉጂና ቦረና፤ በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል የሚገኙት ጋሞ ዞን፣ ኮንሶ፣ ጅንካ አካባቢዎች እንዲሁም ሶማሌ ክልል ይጠቀሳሉ፡፡

ሁለተኛው የበጋ ወቅት ከጥቅምት እስከ ጥር ያሉት ወራቶች ናቸው፣ በነዚህ ወቅቶችም አብዛኛው የሀገሪቱ አካባቢ ደረቅና ነፋሻ የአየር ሁኔታ የሚስተዋልበት ነው፡፡ የመኸር ሰብልን ለመሰብሰብ ምቹ ሁኔታን የሚፈጥር ወቅት ነው፡፡ በአንጻሩ ደግሞ በደቡብ አጋማሽ ለሚገኙ የሀገሪቱ ክፍሎች ለደቡብ ኦሮሚያ ጉጂ፣ ቦረና ቆላማ አካባቢዎች፣ ለሲዳማ እና ደቡብ ብሄር ብሄረሰቦች ክልል፣ ለሶማሌ ክልሎች እንደ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው ሲሆን፤ እነዚህ አካባቢዎች ከአመታዊ የዝናብ መጠን እስከ 30 በመቶ ዝናብ የሚደርሳቸው በነዚህ ወቅቶች ነው፡፡

ሶስተኛው የበልግ ወቅት ከየካቲት እስከ ግንቦት ጊዜ ያሉትን ወራት ያጠቃልላል፡፡ እነዚህ ወራት ለደቡብ ኦሮሚያ ጉጂ፣ ቦረና ቆላማ አካባቢዎች፣ ለሲዳማ እና ደቡብ ብሄር ብሄረሰቦች፣ ለሶማሌ ክልሎች ዋና የዝናብ ወቅቶቻቸው ናቸው፡፡ ከአመታዊ የዝናብ መጠንም እስከ 55 በመቶ የሚሆነውን ድርሻ ያገኛሉ፡፡ ምሥራቅ አማራ፣ ሐረርና ድሬዳዋን ጨምሮ ለመካከለኛ የሀገሪቱ ክፍሎች ደግሞ በልግ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው ነው፡፡

የኢትዮጵያ ብሄራዊ ሚትዮሮሎጂ ኢንስቲትዩትም እነዚህን ወቅቶች መሠረት ያደረገ ሥራ እንዲሰራ ቀድሞ መረጃ ይሰጣል፡፡ የግንዛቤ ሥራም ይሰራል፡፡ ኢንስቲትዩቱ በ2015 በጀት አመት ስለሚጠበቀው የአየር አዝማሚያ የትንበያ ሁኔታ ጥር 2015 ዓ.ም ባለድርሻ አካላትን ያሳተፈ መድረክ አካሂዷል፡፡

እንደ ዶክተር አሳምነው ማብራሪያ፤ ኢንስቲትዩቱ ወቅታዊውን በተለይም የበልግ ወቅትን ትንበያ በሚያዘጋጅበት ጊዜ የምሥራቅና መካከለኛው የፓስፊክ ውቅያኖስ ከመደበኛ በታች መቀዝቀዝ ወይንም ደግሞ ላሊና በሚባለው የአየር ሁኔታ ክስተት ውስጥ ነበር፡፡ በሂደት ግን ከመጋቢት ወር አጋማሽ በኋላ ከመደበኛው ጋር የተቀራረበ የአየር ጠባይ ሊኖር እንደሚችል በትንበያው ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በሁለተኛው ምዕራባዊ የህንድ ውቅያኖስ ክፍል ደግሞ ከመደበኛ በታች የሆነ መቀዝቀዝ መታየቱና በሂደት ለውጥ እንደሚመጣ ተለይቷል፡፡

እነዚህንና ሌሎችንም የአየር ሁኔታ ገጽታዎች ከግንዛቤ ውስጥ ያስገባ የወቅቱ ትንበያ በኢንስቲትዩቱ በኩል ይፋ ተደርጓል፡፡ በትንበያው መሠረት የአየር ሁኔታ ክስተቶቹ ወደ መደበኛ እስኪመለሱ ድረስ በወቅቱ የዝናብ አጀማመር ላይ አሉታዊ ተጽእኖ እንደሚኖራቸው ወይንም መጠነኛ የሆነ መዘግየት ሊፈጠር እንደሚችል ኢንስቲትዩቱ መረጃ ሰጥቷል፡፡

የትንበያ መረጃውን መሠረት ያደረገው በደቡብ አጋማሽ የሀገሪቱ አካባቢዎች እንደሆነና በአንጻሩ ግን አካባቢዎቹ ከመጋቢት አጋማሽ ጀምሮ ሚያዚያና ግንቦት ወራት ላይ ጥሩ የሆነ የዝናብ መጠንና ስርጭት ሊያገኙ እንደሚችሉ ትንበያው ያመለክታል ያሉት ዶክተር አሳምነው፣ በተለይም በልግ ዋነኛ ወቅታቸው የሆኑ የሀገሪቱ አካባቢዎች ማለትም በደቡብ ኢትዮጵያ አጋማሽ ሶማሌ፣ ጉጂ፣ ቦረና፣ ሲዳማ፣ የደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል 15 በመቶ ከመደበኛ በላይ የሆነ የዝናብ ስርጭት እንደሚኖራቸው ጠቁመዋል፡፡ 50 በመቶ የሚሆነውን የዝናብ መጠን የሚያገኙት የደቡብ የሀገሪቱ አካባቢዎች ከመደበኛው ጋር የተቀራረበ ዝናብ እንደሚያገኙ እንዲሁም 35 በመቶ ደግሞ ከመደበኛ በታች የሆነ የዝናብ መጠን ሊያገኙ እንደሚችሉ በትንበያው መለየቱን አስረድተዋል፡፡ በአንጻሩ ደግሞ የሀገሪቱ ሰሜን አጋማሽ አካባቢዎች መደበኛና ከመደበኛ በላይ እንዲሁም የምዕራብ አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎችም ከመደበኛ በላይ የሆነ የዝናብ ስርጭት እንደሚኖራቸው ጠቁመዋል፡፡

ማህበራዊ

# አስኳላ

# «አድማጭም አስቀማጭም ናችሁ»

-ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ

ጽጌረዳ ጫንያለው

የወላጅ ተስፋ ነገ በተባለች በልጆቹ የቀን ሰማይ ላይ ርቃ የተሰቀለች ዳቦ ናት። በአብራኩ ክፋይ መማር ላይ የዛሬን ፈተና የሚሻገር እልፍ ወላጅ አለ። አሳዳጊ ልጅን አስተምሮ ለወግ ለማብቃት የሚወጣው እልፍ ዳገት የሚወርደው የትዬለሌ ቁልቁለት አለው። በለጸግን የሚሉ ሀገራት ከእነሱ ያነሱት ላይ የሚኩራሩት በቁጥራቸው አለያም ባላቸው ጥሪት ሳይሆን በአፈሩዋቸው ምሁራን መሆኑን ማንም አያጣውም፡፡ ለዚህም ነው መማር ከልክ የሚልቅ መለኪያ ነው የሚባለው። ብቸኛ ባይሆንም የሀገርን ልዕልና ያስከብራል፡፡ መሠረት ጣይ ከዋኜም ነው፡፡

በዘመናችን ሰው በመሆን ልኬት ውስጥ መማር የአንበሳውን ድርሻ ይወስዳልም። መማር በኩራት በአደባባይ አንገትን ቀና አድርጎ መቆሚያ ዘውድ ነው፡፡ ምክንያቱም ሰው የእውቀት አድማሱን ሲያሰፋ ዓለምን ለእርሱ መኖሪያነት ምቹ ያደርጋታል፡፡ ለዚህ ደግሞ ተፈትኖ ማለፍ ግድ ነው፡፡ በፈተና ላይ ደግሞ ተፈታኝ፣ አላፊና ወዳቂ የማይቀሩ ነገሮች ናቸው። ፈተና ያወቀውን ካላወቀው፤ ብቁውን ካልበቃው አንጥሮ የሚለይ ወንፊትም ነው። በዚህም ወደ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ለማለፍ ከወንፊቱ ወጥቶ ማለፍ ግድ ነው፡፡ በተለይም የዘንድሮውን ፈተና ማለፍ እጅግ ብዙ ጥረትን የሚጠይቅ እንደሆነ ማንም ይረዳዋል፡፡ ምክንያቱም ኮሮና እና ጦርነት በብዙ መልኩ ሲያንገላታቸው ነው የቆዩት፡፡ ይህም ሆኖ እጅ ያልሰጡ ተማሪዎች እንደነበሩ በሀገር አቀፍ ሽልማቱ ላይ አይተናል፡፡

ከእነዚህ መካከል ተማሪ ሚኪያስ አዳነ አንዱ ሲሆን፤ የይሁኔ ወልዱ መታሰቢያ ደሴ ልዩ አዳሪ ትምህርት ቤት ተማሪ ነው፡፡ ትምህርት ቤቱ የ12ኛ ክፍል ሀገር አቀፍ ፈተናን ሲወስድ ለመጀመሪያ ጊዜው ሲሆን፤ ለውጤቱ የተማሪዎች ትጋት የመጀመሪያ ነበር። ምክንያቱም ቀጠናው የጦርነት በመሆኑ ለስድስት ወር ያህል ትምህርት መማር አልቻሉም። በኮሮና ምክንያትም እንዲሁ ግማሹን መንፈቀ ትምህርት ( ሴሚስተር ) አልተማሩም። ከዚህ በተጨማሪም ትምህርት ቤቱ ጥቃት ከደረሰባቸው መካከል ነው። እናም በያሉበት ቦታ እየተዟዟሩ ባያነቡ ኖሮ ለዚህ ድል አይበቁም ነበር፡፡

ተማሪ ሚኪያስ፤ መምህራኑና ትምህርት ቤታቸውም እጅግ ይመሰገናል፡፡ ምክንያቱም ጦርነቱ ፋታ ሲኖረው ግብዓቶችን በልመና ጭምር አሟልተው ተማሪዎችን ከያሉበት ሰብስበው ለማስተማር ይጥራሉ፡፡ ትምህርት ቤት እንኳን በማይመስል ውስጥ ተምረውም ለዚህ እንደበቁ ያነሳል፡፡ ሆኖም እውቀት መጨበጥ የአንድ ቀን ስራ ባለመሆኑ ሁሉም ተማሪዎች በከፍተኛ ውጤት እንዲያልፉ ሆነዋልም ይላል፡፡

ተማሪ ሚኪያስ በአመጣው ውጤት እጅግ ደስተኛ ነው፡፡ አሁን በጠቅላይ ሚኒስትሩ የተገባላቸው ቃልም ከምንም በላይ አስደስቶታል፡፡ እውቅናው በራሱ ልዩ ትርጉም ሰጥቶታል፡፡ እናም የበለጠ ለመሥራት ተነስቷል፡፡ አሁን የገባው አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ሲሆን፤ በአስትሮኖሚ ዘርፍ መማር እንደሚፈልግ ነግሮናል፡፡

ሰማይ የተደፋ ያህል ከባድ በመሰለው የውጤት ናዳ መሐል ብቅ ያለችው ሌላኛዋ ተማሪ መቅደላዊት እምሩም ናት፡፡ መቅደላዊት በኮተቤ ሳይንስ ሼር ካምፓስ የተፈጥሮ ሳይንስ ተማሪ ስትሆን፤ ያመጣችው ውጤት ደግሞ 636 ነው፡፡ በዚህም ለሁለተኛ ጊዜ እውቅናን አግኝታለች፡፡ ላፕቶፕም ተሸልማለች። ከዚያ ባሻገር ደግሞ ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንዳሉት የውጪ የትምህርት እድል ከአገኙት መካከል ሆናለች።

እውቅና በሁሉም መልኩ ስኬታማነትን የሚያቀዳጅ ነው፡፡ በተለይም ለተማሪዎች ጥሩ ብርታት የሚሰጥ ነው፡፡ ትውውቅን ያጠነክራል፤ የበለጠ መስራትን ያመጣል፡፡ አሁን ያስመዘገብነው ውጤት ቁጥር ብቻ ሆኖ እንዳይቀርም አደራ የሚሰጠን ነው።




አደራው ደግሞ ችግር ፈቺነታችንን እንድንለምድበት ያደርገናል ያለችን ደግሞ በተፈጥሮ ሳይንስ ትምህርት መስክ 645 ያመጣችው፤ ሽልማቱንና እውቅናው ለሁለተኛ ጊዜ ያገኘችው ተማሪ ሄዋን ጥላዬ ነች፡፡

የፈተናው በየጊዜው መራዘም ለውጤታማነቱ እንዳገዘውና በቂ የጥናት ጊዜን እንዳገኘበት የሚናገረው ሌላው ተሸላሚ ደግሞ ሄኖክ ሀብታሙ ነው፡፡ ያመጣው ውጤት 602 ሲሆን፤ ከተፈጥሮ ሳይንስ ትምህርት ዘርፍ ነው፡፡ ሽልማቱ እጅግ የሚያነቃቃውና ለበለጠ ሥራ የሚያዘጋጀው እንደሆነ ያነሳል፡፡ ይህ ሽልማት ከሽልማትነቱ ባሻገር የውጪ የትምህርት እድልንም የሰጠኝ በመሆኑ ከምንም በላይ ተደስቼበታለሁ፡፡ በቀጣይ ሀገሬንም የማስጠራ እሆናለሁ፡፡ ማጥናት የምፈልገው የትምህርት ዘርፍ ጤና ላይ ነው፡፡ እናም ችግር ፈቺ እንደምሆን እምነት አለኝም ብሎናል፡፡

በየትኛውም ዘርፍ ላይ ጥሩ ውጤት ያስመዘገበ ማንኛውም አካል መሸለምና እውቅና ማግኘት ይኖርበታል፡፡ ምክንያቱም አርአያነቱና ትርፋማነቱ የትየለሌ ነው፡፡ ተማሪዎች፣ ቤተሰብ ማህበረሰብ ብሎም ሀገር ይኮራበታልና፡፡ በተለይም በዘንድሮው ሀገር አቀፍ ፈተና የመጣው ውጤት ሲታይ እጅግ የሚገርምና የሚያስደነግጥ ነው፡፡ ምክንያቱም እንደሀገር በመደበኛ ደረጃ ካስፈተኑ 2ሺ 959 ትምህርት ቤቶች ውስጥ ከ50 በመቶ በላይ ያመጡና ተማሪዎቻቸውን ያሳለፉት 1ሺ798 ሲሆኑ፤ ምንም ያላሳለፉት ደግሞ 1ሺ161 ትምህርት ቤቶች ናቸው። ስለሆነም ሙሉ ለሙሉ ተማሪዎቻቸውን ያሳለፉ 20 የሚደርሱ ትምህርት ቤቶች እንደሀገር እውቅናን አግኝተዋል፡፡ ከእነዚህ መካከል ደግሞ የይሁኔ ወልዱ መታሰቢያ ደሴ ልዩ አዳሪ ትምህርት ቤት አንዱ ነው።

ከሰባት መቶ 666 ያህሉን መመለስ በቻለው በተማሪ ሚኪያስ አዳነ አማካኝነት የዘንድሮውን የከፍተኛ ትምህርት ተቋም መግቢያ ፈተና ትልቁን ውጤት በእጁ ጨብጧል። ከ20 በላይ የሚሆኑት የትምህርት ቤቱ ተማሪዎች ውጤትም ከ600 በላይ እንዲያመጡም አድርጓል፡፡ ስለዚህም እንደሀገር መመስገን ይገበሃል ተብሎ ሽልማቱን ተቀብሏል፡፡

ሀገር አቀፍ ሽልማቱ ላይ በመገኘት እውቅናውንና ሽልማቱን ለተማሪዎቹና ለትምህርት ቤቶቹ ያስረከቡት ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ በወቅቱ እንደተናገሩት፤ እናንተ በትምህርት ቆይታቸው የላቀ አድማጭ እና አስቀማጭ ናችሁ፡፡ መምህራኖቻችሁ ያስተማሯችሁን በትክክል ማየት የቻላችሁ፤ በአደመጣችሁት ልክ የሰራችሁና ለትምህርታችሁ ትኩረት የሰጣችሁ ናችሁ፡፡ በዚህም ሽልማትና እውቅና ብቻ ሳይሆን ከፍ ያለ ነገር ያስፈልጋቸዋል በማለት ለሁሉም የውጪ የትምህርት እድል መዘጋጀቱን አብስረዋቸዋል።

ለ273 የላቀ ውጤት ያመጡ ተማሪዎች የተባበሩት አረብ ኤምሬቶች መንግስት ሙሉ ወጪ የውጪ ትምህርት እድል እንደተሰጣቸው ያነሱት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ተማሪዎቹ እጅግ ዘመናዊ በሆኑ ዩኒቨርሲቲዎች ትምህርታቸውን እንደሚከታተሉ ጠቁመዋል፡፡ ለተማሪዎቹ የተሰጣቸውን ፈተና በአግባቡ መስራት በመቻላቸው ኢትዮጵያን የሚያግዙ 273 ተማሪዎች ተገኝተዋል በማለት እርሳቸውም ደስተኛ እንደሆኑ ተናግረዋል፡፡ ለኢትዮጵያ እና አፍሪካ የሚደርሱ እንዲሆኑም ጥሪ አቅርበዋል፡፡

የማድመጥና የአስቀማጭነት አቅማችሁን ተጠቅማችሁ ነገሮችን ወደ እውቀት በመቀየር ተጠቀሙበት በማለት ለተማሪዎች የመከሩት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ በቀጣይ በሚኖራችሁ የትምህርት ቆይታም እውቀትን ብቻ ሳይሆን ጥበብን አብዝታችሁ የምትፈልጉ መሆን ይኖርባችኋል። ምክንያቱም ጥበብን የያዘ ሰው ሁልጊዜ ያሸንፋል። የተሻሉትን ያያል፤ ለሌሎችም መትረፍ ይችላል፡፡ ሀገሩን ለመለወጥም ጊዜ አይወስድበትም፡፡ ስለሆነም ለእውነትና ለእውቀት መቆም ይኖርባቸዋል በማለት አሳስበዋል፡፡

“ አሁን ያለነው በትውልዶች ግንባታ ላይ ነው፤ ያለፈው ትውልድ አልፏል፡፡ አሁን ያለው ትውልድም አነሰም በዛም ለሀገሩ እየለፋ ነው፤ እናንተ ግን ገና ከምንጩ ለሀገራችሁ የምትጠቅሙ እንድትሆኑ ከሰፈራችሁ ወጣ ብላችሁ ለሀገር እንድታስቡና ቀድሞ የነበሩ ስመጥር ኢትዮጵያውያን ምሁራን ከእናንተ ውስጥም እንዲወጡ አደራ እንላችኋለን” በማለትም ተማሪዎችም ሆኑ ቤተሰቦች ለሀገራቸው ከዚህ በላይ እንዲለፉ ጠይቀዋል፡፡

እናንተ ስትጠየቁም ከተጠየቀበት አውጥታችሁ ማሳየት የቻላችሁ ናችሁ፡፡ ክፍል ውስጥ ስትሆኑ በዚያ መኖራችሁን፤ መጽሐፍ ስታነቡም እንዲሁ ከመጽሐፉ ጋር ያላችሁና የማትረበሹ መሆናችሁን አረጋግጣችኋል ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ፤ ትምህርት ቤቶቻቸውንም፤ መምህራኖቻቸውንም አመስግነዋል።

በሽልማት ስነስርዓቱ ላይ ንግግር ያደረጉት የትምህርት ሚኒስትሩ ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ፤ እንደ መንግስትና ትምህርት ሚኒስቴር የተጀመረው ለውጥ የፈተናዎችን ቅቡልነት ማረጋገጥ ላይ ነው፡፡ ነገር ግን ሥራው መሆን ያለበት በሁሉም መስኮች የሚስተዋሉ የትምህርት ስብራቶችን መጠገንና በሁሉም መመዘኛ ብቁ ማድረግ ነው፡፡ ብቁ የሆኑ ተማሪዎችንና ጠንካራ ዜጎችን መፍጠርም ነው፡፡ ለዚህ ደግሞ ዘወትር ጥረት ይደረጋል ብለዋል፡፡

የዛሬው የዕውቅና መርሀ ግብር በነበራቸው ያልተቋረጠ ጥረት ውጤታማ የሆኑ ተማሪዎችን በማበረታታት ሌሎች ተማሪዎች ላይ ከፍተኛ መነቃቃትን እና መንፈሳዊ ቅናትን መፍጠር ነው። ለውጤቱ መምጣት ኃላፊነታቸውን ለተወጡ መምህራን ወላጆችና በየደረጃው ለሚገኙ ባለድርሻ አካላት ምስጋናም የሚሰጥ ነው፡፡ ምክንያቱም በዚህ የለውጥ ሂደት ተጠቃሚውም ተጎጂውም ህብረተሰቡ ነው፡፡ ብቁ ተማሪዎችን የመፍጠሩ ሂደትና የትምህርት ጥራትን የማረጋገጥ ስራ ተጠናክሮ ከቀጠለ ተጠቃሚውን ማስፋት ይቻላል፡፡ ማህበረሰቡ በልጆቹ እንዲኮራና ሀገርም እንድታድግ ይሆናል በማለት በፈተናው ከፍተኛ ውጤት ያመጡ ተማሪዎችን አመስግነዋል፡፡

እውቅና የተሰጣቸው ተማሪዎች በተፈጥሮ ሳይንስ ትምህርት መስክ ከ700 ድምር ውጤት ከ600 በላይ ያመጡ 263 ተማሪዎች እና በማህበራዊ ሳይንስ ትምህርት ዘርፍ ከ600 ድምር ውጤት ከ500 በላይ ያመጡ 10 ተማሪዎች መሆናቸው በሽልማቱ ወቅት የተጠቀሰ ሲሆን፤ ለሁሉም ተማሪዎች ላፕቶፕ ተበርክቶላቸዋል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ኃላፊ ዶክተር ዘላለም ሙላቱ በከተማዋ የላቀ ውጤት ያመጡ ተማሪዎችን በሸለመበት ጊዜ እንዳሉትም፤ በ2014 ዓ.ም የ12ኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና ከተፈተኑ ተማሪዎች መካከል 20 በመቶ ያህል ተማሪዎች 50 እና ከዚያ በላይ አምጥተዋል፡፡ በሀገር አቀፍ ደረጃ ከፍተኛ ውጤት ካስመዘገቡ 20 ትምህርት ቤቶች መካከል አስሩ አዲስ አበባ የሚገኙ ናቸው፡፡

ህይወት የተሟላ ትርጉም የሚሰጠው መኖራችን በትውልድ ላይ ትርጉም ያለው ተጨባጭ ለውጥ ሲፈጥር ብቻ ነው፡፡ ከትውልድ ትውልድ የሚተላለፍ ተጨባጭ አስተሳሰብ ፣ የአኗኗርና የአሰራር ስርዓት ለውጥ ደግሞ የሚመጣው እንደነዚህ የነጠሩ ተማሪዎችን ስንፈጥር ነውና ይህ ቅቡልነት ያለው አሰራር የዛሬ ብቻ ሳይሆን የነገም ባለራዕዮች የሚፈጠሩበት ይሁን በማለት ለዛሬ የያዝነውን አበቃን፡፡

# ወቅታዊ

# ‹‹ግብርና እንደሌሎች የሥራ መስኮች አዋጭና ትርፋማ ሆኖ አርሶ አደሩን በተለይም ወጣቱን መሳብ ይኖርበታል››

*- ዶክተር አዱኛ ዋቅጅራ*
*በግብርና ምርምር መሪ ተመራማሪ*



ፎቶ፡- ፀሐይ ንጉሤ

አስቴር ኤልያስ

**ግብርና ለኢትዮጵያ ኢኮኖሚ የጀርባ አጥንት ስለመሆኑ አያጠያይቅም:: ይህም ከግንዛቤ በመግባቱ መንግሥት የበኩሉን በማድረግ ከዘርፉ ውጤት ለማግኘት ደፋ ቀና ሲል ይስተዋላል:: በተለይም ግብርናውን ለማዘመን እየተሄደበት ያለው ርቀት በመጠኑም ቢሆን የተስፋ ጭላንጭል እያሳየ ይገኛል:: ከዚሁ ከግብርና ሥራ ጋር በተያያዘ ከአምስት ዓመት በፊት የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩትን በምክትል ዋና ዳይሬክተርነት ያገለገሉትንና አሁን በጡረታ ላይ ያሉትን መሪ ተመራማሪ ዶክተር አዱኛ ዋቅጅራን አነጋግረናቸዋል፡ ፤ ዶክተሩ፣ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን በዕጽዋት ሳይንስ፣ ሁለተኛና ሦስተኛ ዲግሪያቸውን ደግሞ በተልባ ላይ አጥንተው ሲያገለግሉ ቆይተዋል:: በደቡብ አፍሪካና በካናዳ ትምህርታቸውን የተከታተሉ ሲሆን፣ በቆይታቸውም በአብዛኛው የሠሩት የቅባት ሰብሎች ላይ ነው:: አዲስ ዘመን ጋዜጣ ከእኚህ መሪ ተመራማሪ ጋር በግብርናው ዘርፍ እስካሁን በምግብ ራስን መቻል ያቃተው ለምንድን ነው? የተጀመረው የከተማ ግብርና የሚሳካውስ እንዴት ነው? በሚሉና በሌሎችም ጉዳዮች ዙሪያ ቆይታ አድርጎ እንደሚከተለው አጠናቅሮታል::**

**አዲስ ዘመን፡- በምግብ ራሳችንን መቻል ያቃተን ለምንድን ነው ከሚለው ጥያቄ ቃለ ምልልሳችንን እንጀምር?**

**ዶክተር አዱኛ፡-** በእኔ ግንዛቤና እይታ የግብርና ችግሮች የሰነበቱ፣ ሰፊ፣ ውስብስብ እና የሚለያዩ (complex & diversified) ስለሆኑ ነው:: በቴክኖሎጂ እና እውቀት አቅርቦት ብቻ በአጭር ጊዜ የሚፈቱ ችግሮች አይደሉም:: እነዚህም ችግሮች ከበርካታ የአገሪቱ የፖሊሲ፣ የኢኮኖሚ፣ ማህበራዊ፣ ባህላዊ፣ መሠረተ ልማቶች ችግሮችም ጋር ይያያዛሉ:: በእርግጥ እስከዛሬ የሚወጡት ቴክኖሎጂዎች እና እውቀቶች በብዛት፣ በጥራት፣ በወቅቱና በየቦታው ደርሰው፣ አርሶ አደሩ መግዛት በሚችለው አቅም መቅረብ ነበረባቸው:: አርብቶ እና አርሶ-አደሩ ስለ ቴክኖሎጂ አሠራር፣ አጠቃቀም፣ ስለ ቁጠባ (የሀብት/ የቤተሰብ) ዘዴዎች... ወዘተ መማር፣ መገንዘብ እና መተግበር መቻል ነበረበት:: በእርግጥ ደግሞ እነዚህ ነገሮች በሒደት የሚመጡ እንጂ እኛ እንደምንፈልገው በአንዴ ሊሆኑ አይችሉም::

በጥቅሉ አርሶ አደሩን ጨምሮ የሁላችንም የሥራ ባህል፣ የአጠቃቀምና የአሠራር ሥልት፤ ከአንድ የኑሮ ደረጃ ወደ ተሻለ የመሸጋገር ዘይቤ (business skills) መፈተሸ ይኖርበታል:: እነዚህን ሁሉ ለማከናወን የግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ በቂ የፖሊሲ ትኩረት፣ የበጀት ምደባ፣ ተገቢ እውቀትና ልምድ ያለው ሙያተኛ፣ አግባብነት ያለው የአፈጻጸም፣ የክትትልና ድጋፍ ሥርዓት ተዘርግቶ መከታተል ያስፈልጋል:: አርሶ አደሩ ላይ ከአቅሙ በላይ ቀረጥ ሊጣልበት አይገባም:: በተፈጥሮም ሆነ በሰው-ሰራሽ አደጋ ኪሣራ ሲያጋጥመውም አሁን እንደተጀመረው ዋስትና ያስፈልገዋል::

ከነዚህ አንጻር ያለፉትን የኢትዮጵያ መንግሥታት የልማት ታሪኮች ስንመለከታቸው፣ በአብዛኛው ከቃል ሙገሳና ማስመሰል እምብዛም አላለፉም:: በጥቅሉ የተሰራው ሥራ በቂ አልነበረም ማለት ነው:: ተጨባጭ ማሳያው ሊሆን የሚችለው የበጀት አመዳደቡ ነው:: ግብርናው አጠቃላይ የአገሪቱ የእድገት ሀብት (GDP) ከ50 በመቶ በላይ እያበረከተ፤ እሱን መልሶ ለማልማት የሚመድበው በጀት እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ከ14 በመቶ አላለፈም ነበር። ስለዚህ የትኩረት ቦታዎችና ሁኔታዎችን በመለየት ከአመራረት እስከ አመጋገብ ያሉትን ሰንሰለቶች መደገፍ እጅግ አስፈላጊ ነው::

ግብርና የኢኮኖሚና እና የህልውናችን መሠረት ስለሆነ በደንብ መደገፍ ግዴታችን ነው:: ሁላችንም በግብርና ላይ ያለን ኋላቀር አስተሳሰብና አመለካከት ሊቀየር ይገባል:: አሁን ባለንበት ሁኔታ ግብርናን ንቀነው አሊያም ሳንደግፈው ቀርተን ከረሃብ እና ከድህነት መውጣት አንችልም::

ግብርና እንደሌሎች የሥራ መስኮች አዋጭና ትርፋማ ሆኖ አርሶ አደሩን በተለይም ወጣቱን መሳብ ይኖርበታል:: እንደዚህ የሚሆነው ደግሞ የተሻሻሉ የሥራ መሣሪያዎች ለአብነት (ትራክተሮች፣ ማጨጃ እና መውቂያ /ኮንባይነሮች...ወዘተ) አርሶ አደሮች በቅርበት በግዥም ሆነ በኪራይ ሊያገኙ ሲችሉ ነው:: በመሆኑም አርሶ አደሩን በማደራጀት እንዲህ ዓይነቱን አገልግሎት ማመቻቸት የግድ ነው:: ዓመቱን በሙሉ ለማረስ እና ለመሰብሰብ እንዲችሉ የመስኖ አገልግሎት ወሳኝ ነው::: ምርጥ ዘር፣ ማዳበሪያ፣ ፀረ-ተባይ /በሽታና ሌሎች ግብአቶችን መግዛት ለማይችሉት አርሶ አደሮች የብድር አገልግሎትና ልዩ ድጋፍ (subsidy) ያስፈልጋል:: የአመራረት ዘዴዎችን ብቻ ሳይሆን የግብይት፣ የትርፋማነት፣ የአጠቃቀም፣ የቁጠባ ባህሎች... በትምህርትና በውይይት መዳበር አለባቸው:: በአጠቃላይ በምግብ ራስን መቻልና ለቀጣይ እድገቶች ግብርናው በተከታታይ የፖሊሲ፣ የቴክኖሎጂ፣ የትምህርት፣ የእውቀት እና የልምድ ግብአቶች ማዳበር ያስፈልጉታል::

አነጋጋሪው /አከራካሪው የመሬት ፖሊሲን ጨምሮ ለግብርናው ግብአትና አገልግሎት የሚሠጡ የግብይት፣ የትራንስፖርት፣ የኢንዱስትሪ፣ የኢነርጂ፣ የኤክስፖርት... ወዘተ ሴክተሮች ተጽዕኖዎች እየተፈተሹ ችግሮቹ መስተካከል ይኖርባቸዋል:: በአጠቃላይ የሁሉም እቅዶቹና አፈጻጸም በቅርበት እየታዩ ክትትልና ድጋፍ ያስፈልጋቸዋል ባይ ነኝ::

**አዲስ ዘመን፡- የምርምር ተቋማት የሚጠበቅባቸውን ድርሻ ለመወጣት ምን ያህል ጥረዋል? ራሳችንን ከመመገብ በዘለለ በስንዴ በኩል ያለውን ተስፋ እንዴት ይገልጹታል?**

**ዶክተር አዱኛ፡-** ከላይ ለመግለጽ እንደሞከርኩት የምርምር ተቋሙ በነበሩት መንግሥታት ፖሊሲ፣ ሥርዓት፣ አደረጃጀት፣ አሠራር፣ አመራር እና እውቀት ውስጥ ሆኖ ከሦስት ሺህ በላይ ቴክኖሎጂዎችና እውቀቶችን በማቅረብ፤ መነሻ የቴክኖሎጂ ዘሮችን በማባዛት እና በማሰራጨት ትልቅ ሥራ ሠርተዋል:: በሠርቶ ማሣያዎች የቅድመ-ሥርጭት ሥራዎችን በመፈጸምም የበኩላቸውን ጥረት አድርገዋል:: ከሌሎች መሰል ድርጅቶች ጋር በመሆንም የበኩላቸውን ሞክረዋል:: በመሆኑም ተቋሙ ሲመሠረት ከነበረው ወደ 25 ሚሊዮን የሕዝብ ቁጥር አሁን ያለው 110 ሚሊዮን ሕዝብ በትንሹም ቢሆን ለመመገብ ተሞክሯል:: ሆኖም ይህ በቂ እንዳልሆነ ሁላችንም እናምናለን::

የብዙዎቹ ሰብሎች ለምሳሌ ስንዴ፣ ገብስ፣ በቆሎ፣ ማሽላ እና ሌሎች ምርታማነት ከእጥፍ በላይ በሚያስችል ሁኔታ እስከ አምስት እጥፍ አድጓል:: ለአብነት የስንዴ አማካይ ብሔራዊ ምርታማነት ከዛሬ 50 ዓመት በፊት የነበረውና ዛሬ ያለው በእጅጉ ይለያያል:: የሞዴል አርሶ-አደሮች እና በመስኖ የሚመረተው ቁጥሩ ከፍ ያለ ስለመሆኑ የአደባባይ ምስጢር ነው:: ስለዚህ በክረምት እና በበጋው መስኖ እንዲመረት አስፈላጊዎቹ ግብአቶች በተለይም ምርጥ ዘር፣ ማዳበሪያ እና ፀረ-አረም /ዋግ/ በተመጣጣኝና አርሶ አደሩ መግዛት በሚችለው ዋጋ በወቅቱ ከቀረበላቸው በስንዴ ራስን መቻል ይቻላል ብዬ አምናለሁ:: በተጨማሪም የትራክተር እና ኮምባይነር ኪራይ እንዲያገኙ እና ከአመራረት እስከ አመጋገብ ባሉት ዋና ዋና የእሴት ሰንሰለቶች ላይ አምራቾች ሊታገዙ ይገባል እላለሁ:: ከታገዙ እና ትርፋማ ከሆኑ ራሳችንን ከመመገብ አልፈን ወደውጭ መሸጥ ይቻላል የሚል እምነት አለኝ:: በአጠቃላይ ግብርናው እንደሌላው የንግድ እና ሌሎች ሴክተሮች አዋጭና ትርፋማ እንዲሆን አስፈላጊዎቹ እገዛና ድጋፍ ከተደረገለት ሁላችንንም የሚያረኩ ውጤቶች ይገኙበታል፤ በጣም ሰፊ እና በርካታ ዕድሎች እንዲሁም ተስፋዎች እንዳሉትም ይታዩኛል::

**አዲስ ዘመን፡- የሰላሙ ሁኔታ ምርምሩን እንዴት አድርጎታል? በዚህ ጉዳይ እንደ አንድ አንጋፋ ተመራማሪነትዎ ምንስ ይመክራሉ?**

**ዶክተር አዱኛ፡-** አዎ ሁላችንም እንደምናውቀው

**ግብርና የኢኮኖሚና እና የህልውናችን መሠረት ስለሆነ በደንብ መደገፍ ግዴታችን ነው:: ሁላችንም በግብርና ላይ ያለን ኋላቀር አስተሳሰብና አመለካከት ሊቀየር ይገባል**

# ወቅታዊ



**እኔ ግብርናው ሳለመቀየሩ እንደ ትልቅ እንቅፋት የማየው የትምህርት ሥርዓታችንን ነው:: እውነት ለመናገር የትምህርት ሥርዓታችን ችግር አለበት**

የልማቱ ሥራ ውጤታማ እና ስኬታማ መሆን የሚችለው የሚከናወኑ እንቅስቃሴዎች ሁሉ ሰላማዊ ሲሆኑ ነው:: የሠላም እና ጸጥታ መኖር፣ የሕግ በላይነት እና የፍትህ መስፈን፣ የዴሞክራሲ እና እኩልነት መኖር፣ በአጠቃላይ የአገርና የሥራ አካባቢዎች ሠላም መሆን ከሁሉ በላይ ወሳኝ ሚና አለው:: ስለዚህ ከሁሉም ነገሮች ቅድሚያ ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገቡ ጉዳዮች ናቸው:: እንደ ትምህርት እና የምርምር ተቋማት ያሉት የቴክኖሎጂና እውቀት ምንጮች በሰከነ መንፈስ በጥንቃቄ ሊሠሩ የሚገባቸው ሥራዎች ናቸው::

በመሆኑም የተመራማሪዎችና የልማት ሠራተኞች ደህንነት እና ዋስትና፣ የምርምር ማዕከሎችና ንዑስ-ማዕከላት ሠላም መሆን፣ የቤተ-ሙከራዎች፣ የንብረት፣ የማሳዎችና የልማት የሥራ መሣሪያዎች ደህንነትና ጥበቃ፣ በጥቅሉ የሰዎችና የሥራ አካባቢዎች ሠላም መሆን እጅግ ወሳኝ ሚና አላቸው:: በተለይም የእኛ ተቋም በየክልሉ ውስጥ ማዕከላትና ንዑስ-ማዕከላት አለን:: ከነዚያ በመነሳት በየገበሬው ማሳዎች ላይ ተሳትፏዊ የምርምርና ልማት ስንሠራ ጥንቃቄና ጥበቃ ካልተደረገላቸው ለረጅም ዓመታት በብዙ ሚሊዮን የገነባናቸውን በጣም ውድ ሀብቶች በቀላሉ እንዳይጠፉ/እንዳይባክኑ ያሰጋል:: ጉዳዩ የሚመለከታቸው ኃላፊዎች እና ሌሎችም ወገኖች ልዩ እንክብካቤና ጥበቃ ሊያደርጉላቸው ይገባል:: በአጭሩ ያለ ጠንካራ የትምህርትና የምርምር ተቋማት ያደገ፣ የተለወጠና የተሻሻለ አገር በዓለም ላይ የለም:: በተለይም በዚህ የእውቀት ዘመን ያለእነሱ ብቁ ተወዳዳሪ ሆኖ መቀጠልም ሆነ መኖር ስለማይቻል እንደ ዓይናችን ብሌን መጠበቅና መንከባከብ ይኖርብናል የሚል ምክር ለሁሉም ማስተላለፍ እወዳለሁ::

**አዲስ ዘመን፡- የከተማ ግብርና በተለያዩ አካባቢዎች ተጀምሯል፤ ፋይዳው እንዴት ይገለጻል?**

**ዶክተር አዱኛ፡-** ሰው ሁሉን ነገር የሚያየው በጎሪጥ መሆኑ ነው እንጂ የከተማ ግብርና ከፍተኛ ጥቅም ያለው ነው:: እኔ ለምሳሌ ለስንዴ የተደረገውን ትኩረት እና አርሶ አደሮችን አስተባብሮ ማዳበሪያ፣ ትራክተር፣ ኮምባይነርና ሌሎች ግብዓት አቅርቦ መርዳት መቻሉ ሊደገፍ የሚገባ ነገር ነው::

ይህም የከተማ ግብርና በየቀበሌውና በየአስተዳደሩ እንዲሠራ መበረታታቱ በጣም መልካም ነገር ነው፤ እኔ ለምሳሌ በጊቢዬ ካሉኝ ነገሮች ውስጥ አንዱ እንጆሪ ነው፤ እንጆሪ መድኃኒት ነው፤ ካንሰርን መከላከሉ በዋናነት ተጠቃሽ ነው:: ስለዚህ ብዙ ወጪ የማናወጣባቸውን ምርቶች ነገር ግን ደግሞ ከፍተኛ ጠቀሜታ ያላቸው በመሆናቸው በእያዳንዳችን ግቢ በማምረት ለመገልገል ብንሞክር ፋይዳው ከፍ ያለ ነው:: ከምንም በላይ ደግሞ ጤናማ የአመጋገብ ሥርዓት እንዲኖረን ስለሚያደርግ በየቤቱ ባለን አነስተኛ ቦታ ሁሉ ለመጠቀም የመንግሥትን ግፊት ከመጠበቅ ይልቅ በራሳችን ሠርተን ለመጠቀም ብንጥር መልካም ነው::

ለምሳሌ አንድ የአቮካዶ እግር ዛፍ ቢኖረን በብዙ ስለሚያፈራ ምርቱን ከውጭ የመግዛት ሐሳብ አይኖረንም:: ይህ ሲሆን የከተማ ግብርና በምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ ከሚደረገው ጥረት ጎን ለጎን የከተማውን የአየር ጸባይ መልካም በማድረግም በኩል አቻ የለውም:: ከዚህ በተጨማሪ ባለችን አነስተኛ ቦታ ሠርተን ውጤት ማሳየት ስንጀምር ልጆቻችንም የእኛኑ ፈለግ ተከትለው ይሠራሉ:: እግረ መንገዳችንም የሥራ ባህል እናወርሳቸዋለን:: ለመሥራት መንቀሳቀሱም ጤናን በማስጠበቁ በኩል ተመራጭ ነውና ዘርፈ ብዙ ፋይዳ አለው ማለት ይቻላል::

ሌላው ቀርቶ አንዳንዴ በሳምንቱ የሥራ ቀን መጨረሻ ላይ ጫማን አውልቆ በባዶ እግር ከመሬቱ ጭቃ ጋር አካልን ማነካካቱ በሰውነታችን ውስጥ ተጠራቅሞ እንደመብረቅ በሽታ የሚሆንብንን የኤሌክትሪክ ኃይል ለማስወገድም የሚያግዝ ነው:: በዚህም የከተማ ግብርና የምግብ ዋስትናችንን ከማረጋገጥ በዘለለ ጤናማ እንድንሆንም የሚያደርገን ነውና ትልቅ ጸጋ ነው:: ከዚህ ጎን ለጎን በመሸጥ ደግሞ ሌሎች ወጪያችንን ለመሸፈንም የሚረዳ ነው:: ይህ የከተማ ግብርና የመንግሥት ትኩረት ሲሆን፣ ሰውም ተበረታትቶ መጠቀም ይችላልና ተጠቃሚ ይሆናል:: ሁሉም የየራሱን ምግብ ከደጁ ማግኘት ቢችል ይበልጥ መልካም ነው::

በከተማ ግብርና እየተንቀሳቀስን ያለነው እኛ ብቻ ሳንሆን ደቡብ ኮሪያ፣ ቻይና እንዲሁም ያደጉ አገሮች ሁሉ እየተጠቀሙበት ያለ ሥራ ነው፤ በአሁኑ ወቅት የመሬት ጥበትና የሕዝብ ብዛትም ስላለ የከተማን ግብርና መሬት ላይ ብቻ ሳይሆን በጣሪያ ጭምር እየሠሩት ነው:: ከዚህም የተነሳ ጣሪያው ሁሉ ምግብ ነው ማለት ይቻላል:: ይህን ተከትሎ ለከተማ ግብርና የሚሆኑ ግብዓት ከማቅረብ አኳያ ራሱን የቻለ የሥራ ዕድል መሆን የሚችልም ነው::

የከተማ ግብርና መሠራት ያለበት ግን በእውቀት ነው:: ከዘር ጀምሮ እስከ ማሳደግ ድረስ የራሱ የሆነ እንክብካቤ የሚሻ ነው:: ከዚህ ጋር ተያይዞ የምርምር ጣቢያዎች መነሻ ዘር የሚያቀርቡ ከሆነና ዘሩን የሚያባዛ አካል ካለ ሥራው የበለጠ ውጤታማ መሆን ይችላል::

**አዲስ ዘመን፡- ትኩረት አድርገው የሠሩት ተልባ ላይ ነው በምርቱ ምን ያህል ውጤታማ መሆን ተችሏል?**

**ዶክተር አዱኛ፡-** ከካናዳ አስር ያህል የተልባ ዝርያዎችን አምጥቼ ከዚያ ውስጥ አስር ያህሉ ለአገራችን ተስማሚ በመሆናቸው ወጥተው ለአርሶ አደሩ መሰራጨት ችሏል:: እነዚህም ዝርያዎች የተፈተሹት በአዴት፣ በሆለታ እንዲሁም በሲናና ምርምር ማዕከላት ውስጥ ነው::

**አዲስ ዘመን፡- ግብርናው በአሁኑ ወቅት በአሠራሩም ሆነ ውጤት በማምጣቱ ረገድ እየተቀየረ መጥቷል ማለት ይቻላል?**

**ዶክተር አዱኛ፡-** እየተቀየረ መጥቷል ቢባልም የተፈለገውን ያህል ነው ማለት አይቻልም:: የተለያዩ ችግሮች አሉ:: እነዚህ ችግሮች ደግሞ በአስተዳደርም ሆነ በአመራር የነበሩ ናቸው፤ አሁንም እንዳይቀጥሉ ግን ባለድርሻዎች ከወትሮው በበለጠ መሥራት ይጠበቅባቸዋል:: ግብርና የተፈለገውን ያህል ለመቀየር ከተፈለገ ደግሞ የሚያስፈልገውን ዋጋ መክፈል የግድ ይላል::

እኔ ግብርናው ላለመቀየሩ እንደ ትልቅ እንቅፋት የማየው የትምህርት ሥርዓታችንን ነው:: እውነት ለመናገር የትምህርት ሥርዓታችን ችግር አለበት:: የተማረ ሰው የተሻለ ሲለብስና የተሻለ ደመወዝ ሲያገኝ ብሎም የተሻለ ኑሮ ሲኖር አይተን እኛም ገባንበት እንጂ የትምህርት ሥርዓቱ አገር በቀል ሳይሆን ከሌላ ተወስዶ ነው የተቀመጠው ማለት ይቻላል:: ይኸውም ከአውሮፓ እና ከአሜሪካ ነው:: እኛ የተቃኘነው በእነርሱ የትምህርት ሥርዓትና ፍላጎት ነው:: ለምሳሌ አሁንም በእንግሊዝኛ እንድንማር እንገደዳለን:: ከዚያ በዚሁ እንግሊዝኛ ከተማርን በኋላ የምናገለግለው ማንን ነው ጥያቄው:: ሕዝባችን እንደሆነ እንደሌላው አገር በቅኝ ባለመገዛቱ እንግሊዝኛን አያውቅም:: ሌላው ቀርቶ ሐሳባችንን እንኳ በቅጡ ለመግለጽ እንቸገራለን፤ ነገር ግን አንዳንዱ ምንም ግንዛቤው ስለሌለን በንግግራችን ውስጥ እንግሊዝኛ ጣልቃ እናስገባለን:: ይህ ግን ስህተት ነው::

የሚያስፈልገን አገር በቀል ትምህርት እንዲሁም አገር በቀል ባህላዊ አስተዳደር ነው:: ለዚህ አባባሌ ምክንያቱ የተማረው ሲያገለግል የሚታየው ለፈረንጁ ነው:: ፈረንጁን ለማገልገል አገር በቀል ትምህርት ሊያስቸግረን ይችላል:: የራሳችንን ወገን ለማገልገል ግን ጠቃሚ ነው:: እርግጥ ነው እንግሊዝኛ ማወቁ መልካም ቢሆንም የራስን ነገር እርግፍ አድርጎ መሆን የለበትም ባይ ነኝ፤ ለምሳሌ ቻይና፣ ጃፓን፣ ደቡብ ኮሪያ፣ ሲንጋፖር ልጆቻቸውን የሚያስተምሩት በራሳቸው ቋንቋ ነው:: ዓለም አቀፍ ቋንቋውን የፈለገ ሰው በኋላ ላይ እንዲያስተምር የሚፈለግ ከሆነ የእንግሊዝኛ ትምህርት ቤቶች ስላሉ ዕድሉን ሙሉ በሙሉ ስለማይዘጉበት የማስተማር መብቱ እንዲጠበቅ ያደርጋሉ:: ነገር ግን ዋናውና የማይቀረው ነገር ግን በራስ ቋንቋ የመማሩ ጉዳይ ነው::

ስለዚህ እኛ ኢትዮጵያውያን ወደ አገር በቀሉ እውቀት መለስ እስከምንል ድረስ ይህ ችግር አይለቀንም:: ምክንያቱም አብዛኛው የትምህርት ዝግጅታችን የሚያሳየው ለሌላው ማገልገል እንደሚያስችለን እንጂ ሕዝባችንን አይደለም:: ለማደግ የራስን የግብርና አሠራር እውቅና ሰጥቶ መነሳት አለበት::

የትምህርት ሥርዓት አገር በቀል ሆኖ እስካልመጣ ድረስ አሁንም ቢሆን ማገልገል የምንችለው አገራችንን ሳይሆን ሌሎች ያደጉ አገሮችን ነው ማለት ያስደፍረኛል:: መማራችን ግን ሕዝባችንን ለማገልገልና ኑሮውን ለማሻሻል መሆን አለበት::

እንደዚያም ሆኖ የውጭው የትምህርት ሥርዓት መቶ በመቶ አያስፈልግም ማለት አይደለም:: በሒሳቡም ሆነ በሳይንሱ በሌላውም መውሰድ የሚገባንን መውሰድ እንችላለን:: ያንን ያገኘነውን እውቀት ግን በራሳችን ለራሳችን እንዲስማማ አድርገን አገራችንን ተጠቃሚ ማድረግ ግን የሚያጠያይቅ አይደለም የሚል አተያይ አለኝ:: እንግሊዝኛን ጨምሮ የትኛውንም ቋንቋ አረብኛም ሆነ ፈረንሳይኛ ማወቁ መልካም ነው::

ለምሳሌ የእኔን ተሞክሮ ለማስቀመጥ ገና ተመርቄ ወደ መልከወረር በጀማሪ ተመራማሪነት ስመደብ የአፋርን ባህል ባለማወቄ እንግዳ ሆኜ ቆይቻለሁ:: አስር ዓመት ሙሉ በአፋር ስቀመጥ እንግዳ የመሆኔ ምስጢር አገር በቀሉን ባህል ያለማወቄ ነው:: በወቅቱ ከከፍተኛ ትምህርት ተቋም ተመርቄ ወጣሁ እንጂ በጉዳዩ ዙሪያ አንድም ያስገነዘበኝ ሰው የለም:: አፋር በወቅቱ አርብቶ አደር ማኅበረሰቡ የበዛ ስለሆነ እንዲሠራለት ወይም በምርምር እንዲገኝለት ቅድሚያ የሚሰጠው እኛ ከያዝነው እቅድ በተቃራኒ ነበር፤ ለዚህም ነው ለአገር በቀሉ ዕውቀት ቅድሚያ መስጠት ተገቢ ነው የምለው:: እኛ ስለሰሊጥና ስለኑግ ስናወራ እሱ ቅድሚያ በሰጠው እቅድ ውስጥ ስላልገባን ሊረዳን አልቻለም:: ስለዚህ ከራስ ማንነት መነጠል ውጤታማ ሊያደርግ አይችልም:: በመሆኑም የልማት አቅጣጫው ሕዝብ ከሚፈልገው ጋር ሊጣጣም ያስፈልጋል::

**አዲስ ዘመን፡- ስለሰጡን ማብራሪያ ከልብ አመሰግናለሁ::**

**ዶክተር አዱኛ፡-** እኔም አመሰግናለሁ::

# ዓለም አቀፍ

## ኬንያ ከሜዳሊያ ይልቅ ጸረ ዶፒንግ ላይ ትኩረት ሰጥታ እንደምትሠራ አስታወቀች

**በጋዜጣው ሪፖርተር**



አዲስ አበባ፡- የኬንያ አትሌቲክስ የስፖርት አበረታች መድኃኒቶች (ዶፒንግ) ችግር በቅድሚያ እልባት መሰጠት እንዳለበት ጠቅሶ ሜዳሊያ ማሸነፍ «ከአሁን በኋላ ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ» አይደለም ብሏል። በባለፈው ዓመት በዓለም አቀፍ ደረጃ ምርመራ ተደርጎላቸው በዶፒንግ ምክንያት 40 በመቶ አትሌቶቿ ታግደዋል።

በእርግጥም ሁኔታው በጣም አስከፊ ከመሆኑ የተነሳ አገሪቷ ከመላው ዓለምአቀፍ ውድድር እንድትታገድ የዓለም አትሌቲክስ ሃሳብ ሰንዝሯል።

ይህንንም ተከትሎ የኬንያ ስፖርት ሚኒስትር ባለፈው ኅዳር በሮም በተደረገው የምክር ቤቱ ስብሰባ ተጨማሪ ጊዜ እንዲሰጠው ተማጽኗል።

ኬንያ ለጊዜው ከዓለምአቀፉ ውድድር መታገዱን ብታመልጥም በምሥራቅ አፍሪካ አትሌቲክስ ስመ ጥር የሆነችው አገር ዓለምአቀፍ ገጽታዋን ለመገንባት ቀላል አይሆንላትም።

በአሁኑ ወቅት በነሐሴ ወር ሃንጋሪ ለሚካሄደው የዓለምአቀፉ አትሌቲክስ ሻምፒዮና ውድድር የተለያዩ ዝግጅቶች እየተደረጉ ሲሆን፣ የኬንያ አትሌቲክስም በጥንቃቄ እያየው ይገኛል። አገሪቷ ሜዳሊያዎችን የማግኘት ሳይሆን በተለየ መልኩ ትሳተፋለች ብሏል።

«በሻምፒዮናው ላይ ውጤት ቅድሚያ የምንሰጠው አይደለም» በማለት የኬንያ የአትሌቲክስ የወጣቶች ልማት ዳይሬክተር ባርናባስ ኮሪር ለቢቢሲ ስፖርት አፍሪካ ተናግረዋል።

«ፌዴሬሽኑ በዋነኝነት ትኩረት ያደረገው አበረታች መድኃኒቶችን የማይጠቀሙ ንፁህ አትሌቶችን በመጠበቅ ላይ ነው። ፍትሃዊና በትክክለኛ መልኩ እያሸነፉ ያሉ አትሌቶች አሉን» ብለዋል።

አክለውም «ደካማ ተብለው የሚታሰቡ ሯጮችን ብንወስድ እንመርጣለን፤ አበረታች ቅመሞችን ሳይወስዱ እስከተወዳደሩ ድረስ ውጤቱ ምንም አይመስለንም» ሲሉ ተናግረዋል።

«ከእንግዲህ ሜዳሊያዎችን በማግኘት ላይ ብቻ ማተኮር አንችልም።» ብለዋል።

የኬንያ መንግሥት ስፖርቱን ከአበረታች መድኃኒቶች ለማጽዳት 25 ሚሊዮን ዶላር በጀት ይዟል።

የስፖርት ሚኒስትሩ አባቡ ናምዋምባ የኬንያ አትሌቲክስ እና የብሔራዊ ፀረ-አበረታች መድኃኒቶች ኤጀንሲ ለዚህ ተግባር የተመደበላቸውን በጀት በአግባቡ ጥቅም ላይ ስለማዋላቸው የሚቆጣጠር ኮሚቴ ያቋቁማሉ ተብሎ ይጠበቃል።

ባርናባስ እንደሚሉት ኬንያ ይህንን ችግር መፍታት ካልቻለች አገሪቱን ብዙ ያስከፍላታል።

«ዓለምአቀፋዊ ገጽታችንን መልሰን ለመገንባት የተወዳዳሪዎችን ቁጥር በእጅጉ መቀነስ አለብን» ሲሉም አክለዋል።

ኬንያ የዶፒንግን ጉዳይ በሚመለከተው በገለልተኛው የአትሌቲክስ ኢንተግሪቲ ዩኒት ከፍተኛ የአበረታች መድኃኒት ስጋት ደቅናለች በሚል በፌዴሬሽን ደረጃ ከተፈረጁ ሰባት አገራት መካከል አንዷ ነች። ይህም ማለት ከአንድ ትልቅ ውድድር በፊት ባሉት 10 ወራት ውስጥ ቢያንስ ሦስት ብሔራዊ ምርመራዎችን ካደረገች በኋላ ነው አትሌቶችን ለመወዳደር ብቁ የሚሆኑት።

ቢቢሲ እንደዘገበው፤ «በከፍተኛ ዶፒንግ ዝርዝር ምድብ "ኤ" ለአምስት ዓመታት ቆይተናል። እናም ዋነኛ ትኩረታችን በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት ከዚህ ምድብ መውጣት ነው» ሲሉ በርናባስ ተናግረዋል።

«የዓለም አትሌቲክስ በዚህ አመት በኬንያ ፀረ አበረታች መድኃኒቶችና ንጥረ ነገሮች ኤጀንሲ በኩል ቢያንስ 3,000 ምርመራዎች እንድናካሂድ አዞናል። ይህ በተቀረው ዓለም በሚደረጉ ውድድሮች እንድንሳተፍ ከፈለግን ነው» ብለዋል።

ኬንያ ከሁለት ሳምንታት በፊት በተደረገው ሁለተኛው የአትሌቲክስ ሩጫ ውድድር ከ1 ሺህ 500 በላይ አትሌቶችን አሳትፋለች።

«በተለመደው ሁኔታ የአገር ውስጥ ውድድሮች ዋና አላማ ተሰጥኦ ያላቸውን መለየት ነው፤ ነገር ግን በአሁኑ ወቅት እነዚህን ውድድሮች በመጠቀም አትሌቶችን ወደ አትሌቲክስ ኢንተግሪቲ ዩኒት ምርመራ ዝርዝር ውስጥ እናካትታቸዋለን» ብለዋል በርናባስ።

በርናባስ እንደሚሉት አገሪቷ መጠነ ሰፊ ምርመራ እያደረገችም ትገኛለች።

በጥር ወር የዓለም አትሌቲክስ ሊቀ መንበር ሰባስቲን ኮ ስለ ሁኔታው ለመወያየት ኬንያን በጎበኙበት ወቅት በመንግሥት የተደገፈ ሽፋን የመስጠት አዝማሚያ እንደሌለ እርግጠኛ መሆናቸውን ተናግረዋል።

በርናባስ አገሪቷ ከዶፒንግ ጋር ከምታደርገው ትግል ወደኋላ እንደማትል ቃል ገብተዋል።

«ሥርዓቱን በማጭበርበር እናልፋለን ብለው የሚያስቡ ምርጥ አትሌቶች እንኳን ከአመቱ መጨረሻ በፊት ይባረራሉ» ብለዋል።


**ከኢፌዴሪ ትምህርት ሚኒስቴር ጋር በመተባበር በየሳምንቱ ሰኞና ዓርብ የሚታተም**

# ሀገራዊ እውቅና ለሀገር እንቁዎች

**በስጦሻቸው ልዑልሰገድ**

በሰው ልጆች በእውቀት ላይ የተመሰረተ የእለት ተዕለት ኑሮ ትምህርት ትልቁን ሚና ይጫወታል። መማር በኩራት በአደባባይ ላይ አንገትን ቀና አድርጎ መቆሚያ ዘውድ ነው፡፡ ለዚህ ደግሞ ተፈትኖ ማለፍ ግድ ነው፡፡ በፈተና ጠንካራው በርትቶ የሚያልፍበት ደከም ያለው ደግሞ የሚቀርበት የትግል ሜዳ ነው፡፡ ፈተና ያወቀውን ካላወቀው፤ ብቁውን ካልበቃው አንጥሮ የሚለይ ወንፊትም ነው። ወደ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ለመግባትም ከዚህ ወንፊት ውስጥ ሾልኮ ላለመውደቅ መጣር ግድ ነው፡፡

በየትኛውም ዘርፍ ላይ ጥሩ ውጤት ያስመዘገበ ማንኛውም አካል መሸለምና እውቅና ማግኘት ይኖርበታል፡፡ ምክንያቱም አርአያነቱና ትርፋማነቱ የትየለሌ ነው፡፡ ተማሪዎች፣ ቤተሰብ፣ ማህበረሰብ ብሎም ሀገር ይኮራበታልና፡፡ በተለይም በዘንድሮው ሀገር አቀፍ ፈተና የተመዘገበው ውጤት ሲታይ እጅግ የሚገርምና የሚያስደነግጥ ነበር፡፡ ምክንያቱም እንደሀገር በመደበኛ ደረጃ ተማሪዎችን ለፈተና ካቀረቡ ሁለት ሺ 959 ትምህርት ቤቶች ውስጥ አንድ ሺ 798ቱ ተማሪዎቻቸው ወደ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የገቡላቸው ሲሆን አንድ ሺ 161 ትምህርት ቤቶች ደግሞ ያስፈተኗቸው ተማሪዎች ወደ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መግባት አልቻሉም፡፡ ሙሉ ለሙሉ ተማሪዎቻቸውን ያሳለፉ 20 የሚደርሱ ትምህርት ቤቶች እንደሀገር እውቅናን አግኝተዋል። ከእነዚህ መካከል ደግሞ የይሁኔ ወልዱ መታሰቢያ ደሴ ልዩ አዳሪ ትምህርት ቤት አንዱ ነው። የትምህርት ቤቱ ተማሪ የሆነው ሚኪያስ አዳነ ከሰባት መቶ 666 በማግኘት የዘንድሮውን የከፍተኛ ትምህርት ተቋም መግቢያ ፈተና ከፍተኛውን ውጤት በእጁ አስገብቷል። ከ20 በላይ የሚሆኑት የትምህርት ቤቱ ተማሪዎች ውጤት ከ600 በላይ ነው፡፡



ፎቶ፦ ዳኜ አበራ

ሀገር አቀፍ ሽልማቱ ላይ በመገኘት እውቅናውንና ሽልማቱን ለተማሪዎቹና ለትምህርት ቤቶቹ ያስረከቡት ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አህመድ በወቅቱ እንደተናገሩት፤ እናንተ በትምህርት ቆይታችሁ የላቀ አድማጭ እና አስቀማጭ ናችሁ፡፡ መምህራኖቻችሁ ያስተማሯችሁን በትክክል ማየት የቻላችሁ፤ ባዳመጣችሁት ልክ የሰራችሁና ለትምህርታችሁ ትኩረት የሰጣችሁ ናችሁ፡፡ በዚህም ሽልማትና እውቅና ብቻ ሳይሆን ከፍ ያለ ነገር ያስፈልጋቹኋል በማለት ለሁሉም የውጭ የትምህርት እድል መዘጋጀቱን አብስረዋቸዋል፡፡ ለ273 የላቀ ውጤት ያመጡ ተማሪዎች የተባበሩት አረብ ኤምሬቶች መንግስት ሙሉ ወጪ የውጪ ትምህርት እድል እንደተሰጣቸው ያነሱት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ተማሪዎቹ እጅግ ዘመናዊ በሆኑ ዩኒቨርሲቲዎች ትምህርታቸውን እንደሚከታተሉ ጠቁመዋል፡፡ ተማሪዎቹ የተሰጣቸውን ፈተና በአግባቡ መስራት በመቻላቸው ኢትዮጵያን የሚያግዙ 273 ተማሪዎች ተገኝተዋል በማለት እርሳቸውም ደስተኛ እንደሆኑ ተናግረዋል፡፡ ከራሳቸው አልፈው ለኢትዮጵያ እና አፍሪካ የሚደርሱ እንዲሆኑም ጥሪ አቅርበዋል፡፡

የማድመጥና የአስቀማጭነት አቅማችሁን ተጠቅማችሁ ነገሮችን ወደ እውቀት በመቀየር ተጠቀሙበት በማለት ለተማሪዎች የመከሩት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ በቀጣይ በሚኖራችሁ የትምህርት ቆይታም እውቀትን ብቻ ሳይሆን ጥበብን አብዝታችሁ የምፈልጉ መሆን ይኖርባቹኋል፡፡ ጥበብን የያዘ ሰው ሁልጊዜ ያሸንፋል፤ የተሻሉትንም ያያል፤ ስለሆነም ለእውነትና ለእውቀት መቆም ይኖርባቸዋል በማለት አሳስበዋል፡፡

"አሁን ያለነው በትውልዶች ግንባታ ላይ ነው፤ ያለፈው ትውልድ አልፏል፡፡ አሁን ያለው ትውልድም አነሰም በዛም ለሀገሩ እየለፋ ነው፤ እናንተ ግን ገና ከምንጬ ለሀገራችሁ የምትጠቅሙ እንድትሆኑ ከሰፈራችሁ ወጣ ብላችሁ ለሀገር እንድታስቡና ቀድሞ የነበሩ ስመጥር ኢትዮጵያውያን ምሁራን ከእናንተ ውስጥም እንዲወጡ አደራ እንላችኋለን" በማለት ለሀገራቸው ከዚህ በላይ እንዲለፉ ጠይቀዋል፡፡

በሽልማት ስነስርዓቱ ላይ ተገኝተው ንግግር ያደረጉት የትምህርት ሚኒስትሩ ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ፤ እንደ መንግስትና ትምህርት ሚኒስቴር የተጀመረው ለውጥ የፈተናዎችን ተቀባይነት በማረጋገጥ ላይ ነው፡፡ ነገር ግን ሥራው መሆን ያለበት በሁሉም መስኮች የሚስተዋሉ የትምህርት ስብራቶችን መጠገንና በሁሉም መመዘኛ ብቁ ማድረግ ነው፡፡ ብቁ የሆኑ ተማሪዎችንና ጠንካራ ዜጎችን መፍጠርም ነው፡፡ ለዚህ ደግሞ ዘወትር ጥረት ይደረጋል።

የዛሬው የዕውቅና መርሀ ግብር በነበራቸው ያልተቋረጠ ጥረት ውጤታማ የሆኑ ተማሪዎችን በማበረታታት ሌሎች ተማሪዎች ላይ ከፍተኛ መነቃቃትን እና መንፈሳዊ ቅናትን መፍጠር ነው፡፡ ለውጤቱ መምጣት ኃላፊነታቸውን ለተወጡ መምህራን ወላጆችና በየደረጃው ለሚገኙ ባለድርሻ አካላት ምስጋናም የሚሰጥ ነው፡፡ ምክንያቱም በዚህ የለውጥ ሂደት ተጠቃሚውም ተጎጂውም ህብረተሰቡ ነው፡፡ ብቁ ተማሪዎችን የመፍጠሩ ሂደትና የትምህርት ጥራትን የማረጋገጥ ስራ ተጠናክሮ ከቀጠለ ተጠቃሚውን ማስፋት ይቻላል፡፡ ማህበረሰቡን በልጆቹ እንዲኮራና ሀገርም እንድታድግ ያደርጋል በማለት በፈተናው ከፍተኛ ውጤት ያመጡ ተማሪዎችን አመስግነዋል፡፡

እውቅና የተሰጣቸው ተማሪዎች በተፈጥሮ ሳይንስ ትምህርት መስክ ከ700 ድምር ውጤት ከ600 በላይ ያመጡ 263 ተማሪዎች እና በማህበራዊ ሳይንስ ትምህርት ዘርፍ ከ600 ድምር ውጤት ከ500 በላይ ያመጡ 10 ተማሪዎች መሆናቸው በሽልማቱ ወቅት የተጠቀሰ ሲሆን፤ ለሁሉም ተማሪዎች ላፕቶፕ ተበርክቶላቸዋል። በ2014ዓ.ም የ12ኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና ከተፈተኑ ተማሪዎች መካከል 20 በመቶ ያህል ተማሪዎች 50 እና ከዚያ በላይ አምጥተዋል፡፡ በሀገር አቀፍ ደረጃ ከፍተኛ ውጤት ካስመዘገቡ 20 ትምህርት ቤቶች መካከል አስሩ አዲስ አበባ የሚገኙት ናቸው፡፡

# ስፖርት




## ፌዴሬሽኑ የታዳጊ ፕሮጀክቶችን በትምህርት ቤቶች አቅፎ ለመስራት አቅዷል

አስማማው ገዛሀው

የአንድን አገር ስፖርት ውጤታማና ቀጣይነት ያለው ለማድረግ መሰረቱ በታዳጊዎች ላይ ትኩረት አድርጎ መስራት መሆኑን ባለሙያዎች ደጋግመው ያነሳሉ፡፡ ለዚህ ደግሞ ትምህርት ቤቶች ትክክለኛው ቦታ ናቸው፡፡ ምክንያቱም ታዳጊዎች በትክክለኛ እድሜያቸው የሚገኙት ትምህርት ቤቶች ላይ ከመሆኑ በተጨማሪ፣ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራ እንዲሁም ባለሙያዎች በአንድነት የሚገኙትም በትምህርት ቤቶች በመሆኑ፡፡ ይህንን በመገንዘብ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአትሌቲክስ ፌዴሬሽን ትምህርት ቤቶችን ማዕከል በማድረግ የታዳጊ ፕሮጀክቶች ላይ በስፋት በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል፡፡




ለዚህም የአዲስ አበባ ከተማ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን በጃንሜዳ እና አበበ ቢቂላ ስታዲየም ታቅፈው ለሚገኙ የታዳጊ ፕሮጀክቶች ድጋፍ እያደረገ ይገኛል፡፡ የከተማ አስተዳደሩ ፌዴሬሽን በህጻናት ፓይለት ፕሮግራሞች በወንድራድና በስብስቴ ነጋሲ አንደኛ ደረጃ ትምርህርት ቤቶች የሚገኙትን ፕሮጀክቶችን እየደገፈ መሆኑንም ጠቁሟል፡፡ በቅርቡም በፕሮጀክቱ የሚካተቱ ታዳጊዎች ምልመላ በትምህርት ቤት ደረጃ ውድድር ለማዘጋጀት ማቀዱን ፌዴሬሽኑ አስታውቋል፡፡

በትምህርት ቤት ደረጃ የታዳጊ ፕሮጀክቶችን ለማብዛት የሚደረገው ውድድር መጋቢት/2015ዓም መገባደጃ ላይ የሚደርግ ሲሆን፤ በምልመላው የተገኙ ብቃት ያላቸው ታዳጊዎች በፕሮጀክቶች ታቅፈው የሚሰለጥኑበት እድል እንደሚመቻችም ታውቋል። ለዚህ የሚሆኑትን አራት ፕሮጀክቶች ፌዴሬሽኑ በራሱ በጀት ለመያዝ በዝግጅት ላይ እንደሚገኝም ጠቁሟል።

በትምህርት ቤቶች ወድድር የሚለዩትም ከ13፣ ከ15 እና ከ17 ዓመት በታች ባሉ የዕድሜ እርከኖች ሲሆን፤ በዚህ መሰረት የሚለዩት ታዳጊዎችም ወደ ስልጠናው የሚገቡ ይሆናል፡፡ የከተማ አስተዳደሩ ወጣቶችና ስፖርት በስልጠና ክፍሉ ከዚህ ቀደም አራት ከ15 ዓመት በታች ፕሮጀክቶችን የያዘ ሲሆን፤ ፌዴሬሽኑም የሙያ ድጋፍና ክትትል እያደረገላቸው ይገኛል፡፡ ፕሮጀክቶቹን በትምህርት ቤት ደረጃ እንዲያሰለጥኑ ለስፖርት ሳይንስ መምህራን የአሰልጣኞች ስልጠናን ለመስጠትም ዝግጅቶች በመጠናቀቅ ላይ ይገኛሉ።

እንደ ከተማ አትሌቲክሱን በፕሮጀክት ደረጃ ለመያዝ ክፍለ ከተሞች ፍቃደኛ መሆን ባለመቻላቸው ፌዴሬሽኑ ክፍተቱን ለመሸፈን ትምህርት ቤት አካባቢ ፕሮጀክቶችን በማስፋፋት አዲስ አበባን የሚወክሉ አትሌቶችን ለማፍ ራት እንደወሰነም ጠቁሟል፡፡

የከተማ አስተዳደሩ በፕሮ ጀክቶች ውድድር ውጤታማ የነበረ ሲሆን፤ በአጠቃላይ ውጤትም የሶስተኝነት ደረጃን በመያዝ ነበር ያጠናቀቀው። በእድሜ ተገቢነት ረገድም ተገቢውን የእድሜ እርከን ይዞ በመቅረቡ ምንም ዓይነት ችግር እንዳልገጠመው ፌዴሬ ሽኑ አስታውቋል። ለዚህም ምክንያት የሆነው ታዳጊዎቹ ወደ ስልጠና ከመግባታቸው አስቀድሞ በህክምና ባለሙያ ዎች እገዛ ትክክለኛ ዕድሜያቸው ተጣርቶ ወደ ስልጠና በመግባታቸው መሆኑ ተገልጿል፡፡ ለሚቀጥለው የትምህርት ቤቶች ፕሮጀክት እድሜ ምልመላም ተመሳሳይ ሂደትን እንደሚከተልም ፌዴሬሽኑ ጠቁማል፡፡

ስልጠና ያለውድድር ውጤታማ አይሆንምና ፌዴሬሽኑ ከተማ አቀፍ ውድድሮችን ለማዘጋጀት ቢያቅድም ብቁ የሆነ የመወዳደርያ ስፍራ አለመኖር ትልቅ እንቅፋት ሆኖበታል፡፡ ፌዴሬሽኑ በውድድር ዓመቱ አስር ውድድሮችን ለማድረግ ያቀደ ሲሆን፤ የትምህርት ቤቶች፣ የማራቶን እና የክፍለ ከተሞች እንዲሁም የገቢ ማሰባሰቢያ ውድድሮችን በቀጣይ የሚያከናውን ይሆናል፡፡ ይሁንና አዲስ አባባ ስታዲየም በእድሳት ላይ በመሆኑ እንዲሁም በአበበ ቢቂላ ስታዲየም የሜዳ ተግባር መወዳደሪያ ባለመኖሩና መሙ አስፈላጊውን መስፈርት ባለመጠበቁ ተወዳዳሪዎች ለጉዳት እንዳይዳረጉ ስጋት ስላለባቸው ውድድሮችን ማካሄድ አዳጋች እንደሆነበት ፌዴሬሽኑ ገልጿል፡፡ ያለው አማራጭ የኢትዮጵያ ስፖርት አካዳሚ በመሆኑም ውድድሮቹን እዚያ ለማድረግ መገደዱን ጠቁሟል፡፡

የአዲስ አበባ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ጽሕፈት ቤት ኃላፊ ወይዘሮ እታፈራው ገብሬ፣ ስፖርቱ ከመንግስት ተላቆ ወደ ህዝብ እንዲገባ በተቀመጠው አቅጣጫ መሰረት ድጋፎችን ለማሰባሰብ ስራዎች እየተሰሩ መሆኑንም ተናግረዋል፡፡ ፌዴሬሽኑ በራሱ ገቢ ለመመራት የሚያደርገውን ጥረት አጠናክሮ ለመቀጠል ከጎኑ ሆኖ በተለያዩ ወጪዎች ድጋፍ በማድረግ ላይ የሚገኘው ሞሃ ለስላሳ መጠጦች ፋብሪካ እንደሆነ ገልፀው፤ ተጨማሪ ስራዎችን ለመስራት የተለያዩ ድርጅቶች ድጋፍ እንዲያደርጉ ያቀረበው ጥያቄ ምላሽ እንዳላገኘ አስረድተዋል፡፡ አትሌቲክስ የአገር ምልክት ከመሆኑ አኳያ ባለሃብቱ ድጋፉን እንዲያደርግም መልእክት አስተላልፈዋል፡፡ በከተማዋ ብዙ ባለሃብት ከመኖሩ አኳያ አንዱ ባለሃብት አንድ ፕሮጀክት ቢይዝ ከተማዋን በአትሌቲክስ ውጤታማ ማድረግና ማስጠራት እንደሚቻል የጠቆሙት የፅህፈት ቤት ኃላፊዋ፣ በዚህም የማዘውተሪያ ስፍራን ችግር ለመፍታት ባለሃብቶች ከአሸዋ ሜዳዎች ስራ ጀምሮ ከፌዴሬሽኑ ጎን እንዲቆሙና እንዲደግፉ ጥሪ አቅርበዋል፡፡


## ለመጀመሪያ ጊዜ የወጣ የዶዘር ማሽን ኪራይ አገልግሎት ግዥ

### ግልጽ ጨረታ ማስታወቂያ

### የግዥ መለያ ቁጥር-ሲ/መ/ባ/019/2015

የሲዳማ መንገዶች ባለሥልጣን ለ2015 በጀት ዓመት በክልሉ ውስጥ የመንገድ ግንባታ ሥራ ለማሠራት 8 (ስምንት) ዶዘር የኮንስትራክሽን ማሽነሪ መስፈርቱን ከሚያሟሉ አቅራቢዎች በግልጽ ጨረታ አውዳደሮ መከራየት ይፈልጋል፡፡

**በዚሁ መሠረት፡-**

1.ተጫራቾች አግባብነት ያለውን የዘመኑ የታደሰ የንግድ ሥራ ፍቃድ፣ የንግድ ምዝገባ ምስክር ወረቀት፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ ሰርተፍኬት፣ የግብር ከፋይነት መለያ ቁጥር ሰርተፍኬት እና የዘመኑን ግብር የከፈሉበትን ታክስ ክሊራንስ እንዲሁም የአቅራቢዎች ዝርዝር ውስጥ ስለመመዝገባቸው የሚያሳይ ሰርተፍኬት ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

2.ተጫራቾች የጨረታውን ሰነድ የማይመለስ ብር 300.00 (ሦስት መቶ ብር) ብቻ በመክፈል ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ለ15 (አስራ አምስት) ተከታታይ ቀናት ከባለሥልጣኑ መ/ቤት ግዥ የፋይናንስና ንብረት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ቢሮ ቁጥር -5 ቀርበው መግዛት ይችላሉ፡፡

3.ማንኛውም ተጫራች የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና በባንክ በተረጋገጠ የክፍያ ማዘዣ (CPO) ወይም ከታወቀ ባንክ የቀረበ የጨረታ ማስከበሪያ በሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ ዋስትና (Unconditional Bid) ከጠቅላላው ዋጋ 1% ሆኖ ከ500,000 ሺህ ብር በላይ የሚበልጥ ከሆነ ብር 500,000 ሺህ ብር ብቻ CPO ወይም ባንክ ጋራንቲ በማሠራት ለብቻው በማሸግ ከመጫረቻ ሰነዳቸው ጋር ማቅረብ ይኖርባቸዋል። ከባንክ የሚቀርበው የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና (Bid Bond) ለ180 ቀናት ፀንቶ የሚቆይ መሆን ይኖርበታል፡፡

4.የሚቀርቡ ማሽነሪዎች በሙሉ የፈረስ ጉልበታቸው፣ የስሪት ዘመናቸው እና ሌሎች መጫረቻ ሰነዱ ላይ የተገለጹ መስፈርቶችን የሚያሟሉ መሆን አለባቸው፡፡

5.የሚቀርቡ ማሽነሪዎች ወደ ሥራ በሚሰማሩበት ጊዜ እና ከአንዱ ፕሮጀክት ወደ ሌላ ፕሮጀክት ማሽነሪዎችን ማንቀሳቀስ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ አሸናፊው ድርጅት በራሳቸው ወጪ አጓጉዘው ወጪው በባለሥልጣኑ መ/ቤት የሚሸፈን ይሆናል፡፡

6 .የሚቀርቡ ማሽነሪዎች የኢንጂን ሠዓታቸው እና የነዳጅ ኦዲዮሜትር በትክክል የሚሠራ መሆን አለበት፡፡

7. ከዚህ በፊት ከሲዳማ መንገዶች ባለሥልጣን ጋር ውለታ ገብቶ በአፈጻጸም ችግር ምክንያት ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶት ማሽነሪዎችን ወደ ሥራ ያላስገባና ውላቸው የተቋረጠ የማሽነሪ አከራይ ድርጅት የጨረታ ሰነዱን መግዛትም ሆነ መወዳደር አይችልም፡፡

8. የጨረታ ሰነዱ በተጫራቾች መመሪያ መሠረት ተሞልቶ ጨረታ ማስከበሪያ /Bid Security/፣ ፋይናንሽያል አንድ ዋና (ኦርጅናል) እና ሁለት ኮፒዎችን እንዲሁም ቴክኒካል አንድ ዋና (ኦርጅናል) እና ሁለት ኮፒ ሰነዶችን በተለያየ ፖስታ በሰም በማሸግ ለየብቻቸው ታሽጎ በአንድ እናት ፖስታ ውስጥ ተካተውና በሁሉም ዶክመንት ላይ ስምና አድራሻ በመጻፍ ህጋዊ የሆነ ማህተም በመምታት ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ16ኛው ቀን ከጠዋቱ 4፡00 ሰዓት እስከ 6፡00 ሰዓት በሲዳማ መንገዶች ባለሥልጣን በግዥ ፋይናንስና ንብረት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ክፍል ለዚሁ አገልግሎት በተዘጋጀ ሳጥን ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል፡፡ የጨረታ ማስከበሪያው ከቴክኒካል ሠነድ ጋር አብሮ መታሸግ አለበት፡፡

ከላይ የተጠቀሰው ጨረታው የሚከፈትበት ቀን የእረፍት ወይም የሕዝብ በዓል ቀን ሆኖ ከዋለ በቀጣይ በሥራ ቀን በተመሳሳይ ሰዓትና ቦታ የሚከፈት ይሆናል፡፡

9 .በጨረታ ሰነድ ላይ የተጠቀሱትን የጨረታ መመሪያ እና ህጎች አለማክበር በመጫረቻ ሰነዶቻቸው በሁሉም ገጽ ላይ ማህተምና ፊርማ ያለማድረግ እና ያልተፈረመበት ስርዝ ድልዝ ያለበት የመጫረቻ ሰነድ ተቀባይነት የለውም፡፡

10. ጨረታው ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ከላይ የጨረታ መክፈቻ ተብሎ በተጠቀሰው ቀንና ቦታ ከቀኑ 6፡00 ሰዓት ላይ ተዘግቶ ከቀኑ 8፡30 ሰዓት ላይ በባለሥልጣኑ መ/ቤት አዳራሽ ይከፈታል፡፡

**ማሳሰቢያ፡-** ባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን ሙሉ በሙሉ ሆነ በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

**ስልክ ቁጥር፡- 046-2-128-446**

## ሲዳማ መንገዶች ባለሥልጣን